አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# የአገው (አዊ) ብሔረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ፋይዳ

በ

ትዕግስት አለማየሁ

2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መታሰቢያነቱ

ለህይወቴ ምስጢር እናቴ ያለምዘርፍ ጎንደር እና ደጉ አባቴ አለማየሁ ጊዮን ይሁንልኝ !

# ምስጋና

በቅድሚያ ጽሁፌን በማረምና በማስተካከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉልኝ አማካሪዬ ጋሼ ዘሪሁን አስፋውን በጣም አመሰግናለሁ። በመቀጠልም አቶ አብርሃም አለሙ በጥናቱ መነሻ ላይ ከርእስ መረጣ ጀምሮ ጥናቱ አቅጣጫ እንዲይዝ ስላደረገልኝ ከልብ ለማመስገን እወዳለሁ።

የመረጃ አቀባዮቼ ያለ እነሱ መረጃ ጥናቱ ጥናት አይሆንም ነበር። ስለዚህ ስለሰጡኝ መረጃ አመሰግናለሁ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ለጥናት ማካሄጃ ገንዘብ ስለረዳኝ ምስጋና ይገባዋል።

ዶክተር ባይለየኝ ጣሠው ላደረጉልኝ የሃሳብና የቁሳቁስ እገዛ ከልብ አመሰግናለሁ። ከዚህ በተጨማሪም ወንድሞቼ እንዳለ አለማየሁ፣ እሄነው አለማየሁ፣ ምንይችል አለማየሁ፣ እህቴ ስመኝ አለማየሁ፣ አያቴ ስሌ ሞገስ፣ የቅርብ ወዳጁ መልዓክ ጸጋዬ እንዲሁም ጓደኛዬ ሮዚና አለሙ ላደረጉልኝ የገንዘብ እና የሀሳብ እገዛ አመሰግናለሁ።

# አጠቃሎ


በዚገም ወረዳ የአዊ ብሔረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጥናት በሚል የተደረገው ይህ ጥናት ዋና አላማው በወረዳዋ የሚኖሩ የአዊ ብሔረሰብ አባላት የሚተርኳቸውን የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ይህ ጥናት በዋናነት በወረዳዋ የሚኖሩ የአዊ ብሔረሰብ አባላት ስለራሳቸው ማንነት ምን እንደሚያስቡ የማሳወቅ ጠቀሜታ ሲኖረው በወረዳዋ እና በብሔረሰቡ አባላት ዙሪያ ምርምር ለማድረግ ለሚያስቡ ተመራማሪዎችም የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

በሰላሳ ሁለት ቀናት የመስክ ቆይታ ወቅት መረጃዎች ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተሰበሰቡ ሲሆን ከእዚህ በተጨማሪ የተለያዩ የጽሁፍ መረጃዎችም ከቤተ መጽሀፍት ከኢንተርኔት እና ከተለያዩ ግለሰቦች እጅ በመሰብሰብ ለዚህ ጥናት ግብዓትነት ውለዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ፋይዳ መመርመር በመሆኑ ተግባራዊ ንድፍ ሀሳብ /Functional Approach/ በዋና መተንተኛነት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

የመረጃ ትንታኔዎች ውጤት መሰረት የአዊ ብሔረሰብ አባላት የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን ጥንተ አመጣጣቸውን ለመግለጽ፣ አሠፋፈራቸውን ለማሣየት፣ ሌሎች ማህበረሰቦች ከሚያሳድሩባቸው ስነ ልቦናዊ ጫና ለማምለጥ፣ ታዋቂ የታሪክ ግለሠቦች ከእነሡ ብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመግለፅ ሀያልነታቸውን ለማሣየት እንደሚጠቀሙባቸው በዚህ ጥናት ታይቷል፡፡

# የአማራ ክልል ካርታ




ምንጭ ፡- የአማራ ክልል ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


መታሰቢያነቱ ..... I

ምስጋና ..... II

አጠቃሎ ..... III

የአማራ ክልል ካርታ ..... IV

1. መግቢያ ..... 1
   1.1 የጥናቱ ዳራ ..... 2
   1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ..... 3
   1.3 የጥናቱ ዓላማዎች ..... 4
   1.4 የጥናቱ ወሠን ..... 5
   1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች ..... 5
   1.6 የአጠናን ዘዴዎች ..... 5
      1.6.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ..... 5
      1.6.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ..... 7
      1.6.3 መረጃ አተናተን ዘዴ ..... 8
   1.7 የመስክ ተሞክሮ ..... 8
      1.7.1 ቅድመ ዝግጅት ..... 8
      1.7.2 የመስክ ክንውን ..... 9
   1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች ..... 11

2. ክለሳ ድርሳን ..... 13
   2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ..... 13
      2.1.1 ቃላዊ ዝርው ተረክ ..... 14
      2.1.2 ቃላዊ ዝርው ተረክና ማንነት ..... 18
      2.1.3 ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ..... 21
   2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 23
      2.2.1 በጭብጥ ላይ የተመሰረቱ ጥናቶች ..... 24
      2.2.2 በምደባ ላይ የተመሰረቱ ጥናቶች ..... 25
      2.2.3 ተረኮችና ባህላዊ ስርአቶች የተጣመሩባቸው ጥናቶች ..... 28

3. የዚገም ወረዳ ህዝብ እና መልክዓ ምድራዊ ገፅታ ..... 30
   3.1 ጥንተ አመጣጥ ..... 30

3.2 መልክዓ ምድራዊ ገፅታ ........ 32
3.3 ቋንቋ ........ 33
3.4 የህዝብ ብዛት እና ኢኮኖሚ ........ 35
3.5 ሀይማኖት ........ 35
4. የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና ........ 36
4.1 ጥንተ አመጣጣቸውን ለመግለጽ የተተረኩ ተረኮች ........ 38
4.2 የአሰፋፈራቸውን ሁኔታ ለማሳየት የተተረኩ ተረኮች ........ 44
4.3 ዚገም ........ 47
4.3 ሌሎች ማህበረሰቦች የሚያሳድርባቸውን ጫና ለመቋቋም የሚተርኳቸው ተረኮች ........ 51
4.3.1 ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ---›› ........ 52
4.3.2 "አገው ጆሮ በላ" ........ 54
4.3.4 "አገው ሲሰለጥን በጨረቃ ጥላ ይዞ ይሄዳል" ........ 55
4.4 አገውና ታዋቂ ነገስታት ........ 57
4.4.1 አገው እና አፄ ላሊበላ ........ 57
4.4.2 አገው እና አፄ ቴዎድሮስ ........ 58
4.5. ቋንቋ ........ 58
5 ማጠቃለያ ........ 61
6. ዋቢ ጽሁፎች ........ 64
7. አባሪ 1፡- የተረኮች ስብስብ ........ 69
8. አባሪ 2፡- የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር ........ 87
9. አባሪ 3 የመረጃ አቀባዮች ፎቶ በከፊል ........ 90

# 1. መግቢያ

በአማራ ክልል፤ አዊ ዞን በዚገም ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ የአዊ ብሄረሰብ አባላት እምነታቸውን፣ልማዳቸውን፣ታሪካቸውን፣ፍልስፍናቸውን፣ስለአለም ያላቸውን አመለካከት የሚያስተላልፉባቸው ማንነታቸውን የሚገልጹባቸው፤በአጠቃላይ ባህላቸውን ከትውልድ ትውልድ የሚያስተላልፉባቸው የተለያዩ ስነቃሎች አሏቸው። ይህ ጥናትም በወረዳዋ የሚኖሩ የአዊ ማህበረሰብ አባላት ስለራሳቸው የሚተርኳቸውን ቃላዊ ዝርው ተረኮች በመሰብሰብ ፋይዳቸውን በመመርመር ላይ የሚያተኩር ሲሆን በአምስት ክፍሎች ተደራጅቷል።

የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱን አቅጣጫ የሚያመለክቱ ስምንት ንዑሳን ርዕሶች ተካተውበታል። እነዚህም የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች የጥናቱ ዓላማዎች፣የጥናቱ ወሰን ፣የጥናቱ ጠቀሜታዎች ፣የአጠናን ዘዴ፣ የመስክ ተመክሮ እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች ናቸው፡

ክፍል ሁለት ደግሞ ከጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ምሁራን ያነሷቸው ንድፈ ሀሳቦች እንዲሁም ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበዋል። እነዚህም ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል።

ክፍል ሦስት ስለ ተጠኚ ወረዳው ትውውቅ የሚደረግበት ምዕራፍ ነው። ትውውቁ የሕዝቡን ጥንተ አመጣጥ፣የወረዳዋን መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ፣ቋንቋ፣ኢኮኖሚና ሀይማኖት ምን እንደሚመስል ያሳያል።

ክፍል አራት የተመረጡ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በመውሰድና ፋይዳቸውን መሠረት በማድረግ ትንተና የተሰጠበት ምዕራፍ ነው። በመጨረሻም በክፍል አምስት ማጠቃለያ ቀርቧል።

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

‹‹አዊ›› በአማራ ክልል፣አዊ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ ለሚኖሩ አገዎች መጠሪያ ነው፡፡ እነዚህን የአዊ ዞን አገዎች የተለያዩ ሰዎች በተለያየ ስያሜ ይጠሯቸዋል፡፡ ከእነዚህ መጠሪያዎች መካከል ‹‹አገው››፣ ‹‹አዊ››፣«የመካከለኛው ኩሽ»፣«አዋዋ»እና «አዊያ» እንዲሁም ‹‹የደቡብ አገው›› የሚሉት ይገኙበታል፡፡

‹‹አገው›› የሚለው መጠሪያ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ የተለያዩ ስፍራዎች ውስጥ የሚኖሩ የአገው ህዘቦች የጋራ መጠሪያ ነው፡፡ እነዚህም ብሌን፡ ኤርትራ ውስጥ ቦጎስ በተባለው ስፍራ ውስጥ የሚኖሩ አገዎች፣ ህምጤ፡ ከዋግ በስተሰሜን የሚኖሩ አገዎች፣ ቅማንት፡ ጭልጋ ውስጥ የሚኖሩ አገዎች እና አዊ አገው ምድር ጎጃም ውስጥ የሚኖሩ አገዎች ናቸው (Uhlig 2003፡ 139)፡፡ ጎጃም አገው ምድር ውስጥ የሚኖሩ አገዎች ከሌሎች አንጻር አካባቢያዊ አቀማመጣቸው ሲታይ በስተደቡብ ስለሚገኙ የደቡብ አገዎች ሊባሉ ችለዋል (Zelalem 2011:6)፡፡ ‹‹የሠባት ቤት አገው›› የሚለው መጠሪያ የብሄረሰቡ አባላት ጥንተ አመጣጣቸውን ከላስታ ወደ አገው ምድር መጡ ከሚባሉት ሰባት ወንድማማቾች ጋር አያይዘው ስለሚያምኑ የተሰጣቸው ስያሜ ነው፡፡ ‹‹አዋዋ›› እና ‹‹አዊያ›› የሚሉት መጠሪያዎች ደግሞ የአገውኛ ቃላት ሲሆኑ ‹‹አዋዋ›› ማለት አገዎች ማለት ሲሆን Melakneh (1990፡9) እንደሚገልጹት ‹‹አዊያ›› ማለት ደግሞ የአገው ልጅ ማለት ነው፡፡ ‹‹አዊ›› የሚለው የመጣው ‹‹አዋ›› ከሚለው የአገውኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ጸሀይ ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ‹‹አዊ›› የሚለው ስያሜ በአማራ ክልል በአዊ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ አገዎች ሁሉ በጋራ የሚጠሩበት የአገውኛ ቃል ነው፡፡ ከነዚህ መካከል የዚገም ወረዳ አንዷ ናት፡፡

ዚገም ወረዳ ራሷን የቻለች ወረዳ ሆና የተቋቋመችው ሐምሌ 30 ቀን 2003 ዓ.ም ነው፡፡ ከዚያ በፊት በጓንጓ ወረዳ ስር ትተዳደር ነበር፡፡ ወረዳዋ በአራት ቀጠናዎች ማዕከል እና በአስራ አራት ቀበሌዎች የተከፋፈለች ናት፡፡ የአብዛኛው ሕዝቦቿ የኢኮኖሚ መሠረት የእርሻ ሥራ ነው፡፡ ብዙውን ቁጥር የሚሸፍን የክርስትና እምነት ተከታይ ሕዝብም በወረዳዋ ውስጥ ይኖራል፡፡

በወረዳዋ ውስጥ የሚኖሩ የአዊ ማህበረሰብ አባላት ስሜታቸውን፣እውቀታቸውን ፣እምነታቸውን፣ ሃሳባቸውን፣ የሕይወት ልምዳቸውን በአጠቃላይ ባህላቸውን የሚገልጹበት ሰፊ የስነ-ቃል ሀብት አላቸው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ሰፊ የስነቃል ሀብቶቻቸው መካከል አንዱ በሆነው ቃላዊ ዝርው ተረክ ዙሪያ ጥናት በማድረግ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ይህ ጥናትም የወረዳዋ ህዝብ በቃላዊ ዝርው ተረኮቹ አማካይነት ማንነቱን እንዴት እንደሚገልጽ ያሳያል፡፡

የተለያዩ ምሁራንም በተረክ ማንነትን ምፍጠር እና መግለጽ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህ ምሁራን መካከል Sims (1968:168) ቃላዊ ዝርው ተረኮች የግለሠቦችንም ሆነ የአንድን ማህበረሰብ የጋራ ማንነት ይገልጻሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ Dundes (1986:9) በበኩላቸው ደግሞ ጠቅለል አድርገው ፎክሎር የአንድን ማህበረሰብ ማንነት በተለያየ መልኩ ሊገልጽ ይችላል በማለት ሃሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡

ይህ ጥናት የወረዳዋ የብሄረሰቡ አባላት ስለማንነታቸው የሚተርኳቸውን ተረኮች ፋይዳ ከማሳወቅ በተጨማሪ በአዲስ ወረዳነት የተቋቋመችውን ዚገም ወረዳን ከማስተዋወቅ አንጻር ላቅ ያለ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ይህ የወረዳዋን ህዝብ ለማወቅ ለሚፈልግ ሰው ያለው ጠቀሜታ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች አካዳሚያዊ ጠቀሜታዎችም ይኖሩታል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሡኝ ሁለት አበይት ምክንያቶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በክፍል ውስጥ "Theoretical and Critical Understanding of Folklore" ያተሰኘውን ኮርስ በምንማርበት ወቅት የማንነትን እና የተረክን ግንኙነት በጥልቀት በመረዳቴ በዚህ ርዕሠ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት የማድረግ ሀሣብ አደረብኝ፡፡ ጊዜው ደርሶ ርዕስ እንድናስገባ ሲነገረኝ የምሠራበትን አካባቢ ብቻ ለመወሰን ቀድሜ አስብ የነበረውን ርዕስ ልመርጥ ቻልኩ፡፡

ሌላውና ሁለተኛው ምክንያቴ ሐምሌ 30፣2003 ዓ.ም እንደ አዲስ ወረዳ በተቋቋመቺው ዚገም ዙሪያ ጥናት ማድረግ በአቅሜ የማበረክተው አንድ አስተዋጽኦ ሆኖ ስለተሰማኝ ነው፡፡ አዲስ ወረዳ መሆኗ ብቻ ግን ለጥናት እንድመርጣት አላደረገኝም፡፡ ከዚህ በፊት በወረዳዋ አይዋህ በተሰጠኝ የገጠር ቀበሌ ውስጥ የሚኖሩትን አያቶቼን ልጠይቅስሔድ ማህበረሰቡ ስለራሱ የሚተርካቸው ተረኮች አሁን ላይ ሆኜ ትዝ ሲሉኝ በርዕስ ጉዳዩ ላይ መስራትን እንድገፋበትና እንድወስን አደረገኝ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዚገም ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ የአዊ ብሄረሰብ አባላትን የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ሰብስቦ ፋይዳቸውን መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎችም አሉት፡፡

- በማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች የሚተላለፈው መልዕክት ምን እንደሆነ መመርመር
- ተራኪዎች ለሚተርኳቸው የማንነት ተረኮች ያላቸው አመለካከት ምን እንደሆነ መግለጽ
- ለተረኮቹ መፈጠር፣መተረክና እስካሁን መቆየት ምክንያት ምን እንደሆነ መመርመር

ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ጥያቄዎች በጥናቱ ይመለሳሉ፡፡

- በወረዳ ውስጥ የሚኖሩ የብሄረሰቡ አባላት በቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው አማካይነት ማንነታቸውን እንዴት ይገልጻሉ? የእዚህ ተረኮችስ ፋይዳ ምንድን ነው?
- በተረኮቹ አማካይነት ምን ምን ቁም ነገሮች ይነሳሉ? ወይንም የማህበረሰቡ ዓባላት በተረኮቻቸው ውስጥ ለምን አይነት ነገሮች ትኩረት ይሰጣሉ?
- ለተረኮቹ መፈጠር፣ መተረክ እና መቆየት ምክንያት ምንድን ነው?
- ተጠኚው ብሄረሰብ ተረኮቹ የሚሰጡት ትርጉም ምንድን ነው?

## 1.4 የጥናቱ ወሠን

ይህ ጥናት የዚገም ወረዳ የአዊ ብሔረሰብ አባላት ከሚተርኳቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮችን መካከል የብሄረሰቡ አባላት ስለራሳቸው የሚተርኳቸውን ተረኮች በመውሰድ ፋይዳቸውን በመመርመር ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በመሆኑም የተሰበሰቡት ተረኮች ሁሉ በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም ነገር ግን የብሔረሰቡ አባላት ‹‹እንዲህ ነን›› እና ‹‹እንዲህ አይደለንም›› በማለት ስለራሳቸው የሚተርኳቸው ተረኮች ብቻ የዚህ ጥናት አካል ናቸው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ የሚካሔድበት አካባቢያዊ ወሰን የዚገም ወረዳ ብቻ ሲሆን ለመረጃነት የሚወሰዱት ደግሞ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ብቻ ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በመመርመር ብሄረሰቡ ስለራሱ ምን እንደሚሰማው ለማወቅ ያስችላል፡፡
- በተጠኚ ወረዳዋ እና ብሄረሰቡ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልግ ተመራማሪ መነሻ ይሆናል፡፡
- የአጥኚዋ የመስክ ተሞክሮ ሌሎች የመስክ ጥናት ለማድረግ ለሚያስቡ ተመራማሪዎች ይረዳል፡፡
- እነዚህ ተረኮች ተሰብስበው መጠናታቸው ለፎክሎር ጥናት ዘርፍ አንድ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

## 1.6 የአጠናን ዘዴዎች

ከዚህ ቀጥሎ የዚህ ጥናት የመረጃ አሰባበስበ ዘዴ፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ እንዲሁም የመረጃ አተናተን ዘዴ ምን እንደሚመስል ይገለጻል፡፡

### 1.6.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የዚህን ጥናት ዓላማዎች ለማሳካት እንዲሁም የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የጥናቱ አላማዎችና

የምርምር ጥያቄዎች በደንብ ከተለዩ በኂላ ከጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የታተሙ እና ያልታተሙ ጽሁፎች ከቤተ መጽሐፍት እና ከተለያዩ ግለሰቦች እጅ እንዲሁም ከኢንተርኔት ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህም ለጥናቱ ግብዓትነት የዋሉ እና በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረኝ አደረጉ ካልዓይ ምንጮች ናቸው፡፡

ቀዳማይ ምንጮች ደግሞ ከመስክ መረጃ አቀባዮች በቀጥታ የተገኙት መረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህን መረጃዎች ለመሰብሰብ ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት የመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴዎች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ቃለ መጠይቅ ይህን ጥናት ለማካሄድ በዋና የመረጃ መሠብሰቢያነት ያገለለ ዘዴ ነው፡፡ በዚህም ዘዴ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ጠንቅቀው ያውቃሉ የተባሉ ግለሰቦችን በመምረጥ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

መሪ የሆኑና የታቀዱ ጥያቄዎችን በመጠቀም መደበኛ ቃለ መጠየቅ እንዲሁም ሁኔታው በፈቀደ መጠን ኢመደበኛ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቃለ መጠይቁ ሂደት ተከናውኖል፡፡ በዚህም መሠረት አስራ ዘጠኝ የሚሆኑ መረጃ አቀባዮችን በማግኘት ስልሳ አንድ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ተሰብስበዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ሰባቱ ቁልፍ አቀባዮች ናቸው፡፡ ቃለ መጠይቅ የተካሄደው መቅረጸ ድምጽ እና ቪድዮ ካሜራን በመጠቀም ሲሆን ማስታወሻ የመውሰድ ተግባርም ነበር፡፡ Goldstein (1964:104-113 እና ፈቃደ (1991፣96-970)ም ቃለ መጠይቅ ስነ ቃሎችን ከመስክ ለመሰብሰብ ተመራጭ ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ቃለመጠየቅ እና ምልከታ እርስ በእርሳቸው ተደጋጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች እንደሆኑም ይገልጻል፡፡

በዚህ ጥናትም ምልከታ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የሚከውኑበትን አውድ ለመገንዘብ እና በመስክ ቆይታ ወቅት የማህበረሰቡን አኗኗር ሁኔታ ለመቃኘት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

የቡድን ውይይቱ ደግሞ አስራ አንድ የሚሆኑ ቁልፍ እና ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮችን በማሳተፍ የተካሄደ ነው፡፡ በዚህም ስለ አዊ ማንነት የተረኳቸውን ተረኮች አስመልክቶ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ፤በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ለተረኮቹ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለመረዳት የተካሄደ ነበር፡፡ መረጃዎቹም መቅረጸ ድምጽን እና ቪዲዮ ካሜራን በመጠቀም የተሰበሰቡ ሲሆን ማስታወሻም ተወስዷል፡፡

ሌላውና ዋናው ጉዳይ ይህ መረጃ የተሰበሰበበት ቋንቋ ነው፡፡ የወረዳዋ የአዊ ማህበረሰብ አባላት በአብዛኛው ከአገውኛ በተጨማሪ አማርኛ መናገር ይችላሉ፡፡ (ለዚህ ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል የተለያዩ የታሪክ ምሁራን የሰጡት ማብራሪያ በክፍል ሶስት ውስጥ ቀርቧል፡፡) ይህንን መሰረት በማድረግ ተረኮቹን በአማርኛ እና በአገውኛ ቋንቋዎች ልሰበስብ ችያለሁ፡፡ ይህ ማለት መረጃ አቀባዮቹ መረጃዎቹን በአማርኛ ቋንቋ በሚሰጡኝ ወቅት በቀጥታ የወሰድኩኝ ሲሆን በአገውኛ ቋንቋ የተሰጡኝን መረጃዎች ደግሞ በረዳቴ ባይሞት ምንይሉ ረዳትነት በመተርጎም ለዚህ ጥናት ግብአትነት ተጠቅሜያለሁ፡፡

### 1.6.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የመረጃ አቀባዮች የተመረጡት በታላሚ የናሙና አመራረጥ ስልት (purposive sampling method) ነው፡፡ ለጥናቱ የሚያግዙ መረጃዎችን የሚሰጡ ሰዎች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ ታላሚ የናሙና አመራረጥ ስልትን በመከተሌ ማሳያ ነው፡፡ መረጣው የተካሔደው ለወረዳዋ የባህልና ቱሪዝም ሠራተኞች እና በአካባቢው ማህበረሰብ ጥቆማ አማካይነት ነው፡፡ የባህልና ቱሪዝም ሠራተኞች የጠቆሙኝ ሰዎች ራሳቸው ሌሎች እነሱ የሚያውቋቸውን ሰዎች የጠቆሙኝ አጋጣሚም ነበር፡፡ የተጠቆምኳቸውን ሰዎች በሙሉ አግኝቼ ያነጋገርኳቸው ሲሆን ከነዚህ ሰዎች መካከል ፈቃደኛ ያልሆኑ ወይንም መረጃቸውን ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና የሌላቸውም ይገኙበት ነበር፡፡ በዚህም መሠረት መረጃቸው ለዚህ ጥናት ግብአትነት የዋሉ አስራ ዘጠኝ የመረጃ አቀባዮች የተገኙ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ሰባቱ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ «ቁልፍ» የተሰኙበት ምክንያት በሰጡኝ መረጃዎች ብዛት እንዲሁም ስለ ተረኮች ከሰጡኝ ማብራሪያዎች በመነሳት ነው፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች ብዙዎቹ ወንዶች ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

### 1.6.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በቅድሚያ ከመስክ ቀን በመቅረጸ ድምጽ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ማታ በማስታወሻ ደብተር ላይ የማስፈር ሂደት ተከናውኗል።የመረጃ ክፍተት ካለ እና ግርታን የሚፈጥር ነገር ከተገኘ በቀጣዩ ቀን ወደ መረጃ አቀባዮች በመሔድ ክፍተቱን የመሙላት ስራ ተሠርቷል።

መረጃ የመሰብሰብ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ትንተና ተካሂዷል። ትንተናውን ለማካሄድ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የመስኩ ምሁራን የሰጧቸውን ሀሳቦች በመስክ ከተገኙ መረጃዎች ጋር የማመሳከር ተግባር ተፈጽሟል። የተረኮችን ማህበራዊ ፋይዳ ለመመርመር ደግሞ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ /Functional Approach/ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ዋና መተንተኛ ንድፈ ሃሳብ ሆኖ ሊመረጥ ችሏል።

## 1.7 የመስክ ተሞክሮ

### 1.7.1 ቅድመ ዝግጅት

ለጥናቱ የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሠብሠብ ወደ መስክ ከመወጣቱ በፊት የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶች ተደርገዋል። የመጀመሪያው ዝግጅት ለመረጃ መሠብሠቢያ መሳሪያነት የሚያገለግሉ ቁሶችን በውስት እና በግገር ማሟላት ነበር። እነዚህ መሣሪያዎችም መቅረጽ፣ዲጂታል ካሜራ፣ ማስታወሻ ደብተሮች፣ እስክርቢቶዎች፣ ወረቀቶች እና የእርሳስ መቅረጫዎች ናቸው።

ከዚህ በመቀጠል የድጋፍ ደብዳቤዎች ከትምህርት ክፍሉ የማግኘት ተግባር ተከናውኗል። ይህም ጥናት በሚካሔድባቸው ስፍራዎች እና መስሪያ ቤቶች ሲገባ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ ታቅዶ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የሌሎች አጥኚዎችን የመስክ ተሞክሮዎች የመቃኘት ተግባርም ተካሒዷል። እነዚህ ዝግጅቶች በመስክ ስራ ወቅት በቅድመ ዝግጅት ማነስ ምክንያት የሚከሠቱት ችግሮች እንዳይከሰቱ አድርገዋል።

### 1.7.2 የመስክ ክንውን

ለመስክ ስራ የሚሆኑ ቅድመ ዝግጅቶች ከተጠናቀቁ በኋላ ጥር 26 ቀን 2004 ዓ.ም ወደ አማራ ክልል ዋና ከተማ ባህር ዳር ገባ ተደርጓል፡፡ በቀጣዩ ቀን ወደ ክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ የጽሁፍ መረጃዎች ካሉ ተጠይቆ የክልሉ ካርታ እና በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ዞኖች እና ወረዳዎችን ዝርዝር የያዘ ወረቀት ብቻ ተገኝተዋል፡፡ ሌሎች ቀሪ መረጃዎችን ከዞኑ እና ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች መጠየቅ እንደሚሻለኝ ጥቆማ ሰጥተው አሰናብተውኛል፡፡

ጥር 29 ቀን 2004 ዓ.ም በዞኑ ዋና ከተማ እንጅባራ ውስጥ ወደ ሚገኘው አዊ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ የተለያዩ መረጃዎችን አግኝቻለሁ፡፡ በቀጣዩም ቀን ቻግኒ ከተማ ሄጄ አደርኩ ወደ ዚገም ወረዳ ለመሄድ ከቻግኒ ከተማ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ መያዝ ግድ ነበር፡፡

የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም ዚገም ወረዳ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ገደማ ገባሁ፡፡ ወደ አምስት ሰዓት አካባቢ ወደ ወረዳው ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ሄድኩ፡፡ መረጃ ወደምፈልግባቸው ስፍራዎች እና ግለሰቦች በምሄድበት ወቅት ሁልጊዜ በቅድሚያ ራሴን የማስተዋወቅ እና የመጣሁበትን ዓላማ በግልጽ የማሳወቅ ተግባር አከናውኛለሁ፡፡ የባህልና ቱሪዝም ሰራተኞችን አላማዬን ከተረዱ በኋላ ምን አይነት መረጃዎችን ከማን ላገኝ እንደምችል ጠቁመውኝ እነሱ ያላቸውን መረጃዎችም በወረዳዋ በቆየሁባቸው ጊዜያት ሁሉ ማግኘት እንደምችል ነግረውኛል፡፡ ስለዚህ በመስክ ቆይታዬ ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ቢሯቸው በተለያዩ ቀናት እሄድ ነበር ያላቸውን መረጃ ያለ ምንም ማንገራገር ይሰጡኝ እና ከሌሎች ቢሮዎችም ይጠይቁልኝ ነበር፡፡

በዚገም ወረዳ ውስጥ የሚገኙ መስሪያ ቤቶች (ትምህርት ቤትን፣ጤና ጣቢያን፣ፖሊስ ፣ ግብርና ቢሮን ጣቢያን ሳይጨምር) በአንድ ቅጥር ግቢ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ይህ የሆነበት ምክንያት ወረዳዋ አዲስ ወረዳ ሆና የተቋቋመችው ገና ሐምሌ 30 ቀን 2003 ዓ.ም በመሆኑ እያንዳንዱን መስሪያ ቤት ራሱን አስችሎ ለማቋቋም ጊዜ ስለሚጠይቅ ነው፡፡

ስለዚህ ቀጣዩ ተግባር መረጃ አቀባዮችን ማግኘት ነበር፡፡ ይህንን ለማድረግ የረዳኝ ባይሞት ምናሉ የተባለው ወጣት ነው፡፡ ይህ ወጣት በወረዳዋ ዋና ከተማ የሚገኘው ብቸኛ የቦኖ ውሃ አስቀጂ ሰራተኛ በመሆኑ ብዙ የቅላጅ ከተማ ነዋሪዎች ያውቁታል፡፡ ስለዚህ ወደ ተጠቆምኩባቸው መረጃ አቀባዮች ስሄድ ከእርሱ ጋር በመሆኑ በአብዛኛው መልካም አቀባበልን አግኝቻለሁ፡፡ ከረዳቴ ባይሞት ምናሉ በተጨማሪ መረጃ የመሰብሰብ ሂደቱን እና ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ያለውን ግኙነት ቀላል ያደረገልኝ አያቴ የዚያው አካባቢ ተወላጅ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ብዙ መረጃ አቀባዮች አያቴን ያውቁታል፡፡

ሁሉም መረጃ አቀባዮች ይገኙበታል ወደተባለበት ስፍራ ሁሉ በመሄድ ራሴንና የመጣሁበትን ዓላማ በመግለጽ ቀጠሮ በመያዝ ሲያመች በዚያው ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከየካቲት 3 ጀምሮ በወረዳዋ ቆይታ ተድርጓል፡፡ የካቲት 3 የመጀመሪያ መረጃ አቀባይ አባ ወሬኛ ዘውዴን ያገኘሁበት ቀን ነው፡፡

ከወረዳዋ ዋና ከተማ ቅላጅ በተጨማሪ ዲሂ፣ ግምር እና አይዋህ የተሰኙ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥም መረጃዎችን የመሰብሰብ ሂደት አከናውኛለሁ፡፡ እነዚህ የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ስለወረዳዋ የአዊ ብሄረሰብ አባላት ጠንቅቀው ያውቃሉ የተባሉ ግለሰቦች እንዳሉ መረጃውን ከተለያዩ ሰዎች ስላገኘሁ ወደዚያ በመሄድ መረጃዎችን ልሰበስብ ችያለሁ፡፡ ሌላው ጥሩ አጋጣሚ ደግሞ እኔ ለመስክ ስራ ከመውጣቴ ጥቂት ቀደም ብሎ የአዊ ዞን አገዎች እና የዋግህምራ አገዎች ትውውቅ ያደረጉበት ዝግጅት የተካሄደበት ወቅት ነበር፡፡ ትውውቁ የዋግህምራ አገዎች ተወካዮች በአዊ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች (ዚገምን ጨምሮ) ውስጥ በመዘዋወር የጎበኙበትና እርስበእርስ የተዋወቁበት ወቅት ነበር፡፡ ለመስክ ስራ በወጣሁበት ወቅት የነበረው ድባብ አልቀዘቀዘም ነበርና ስለአዊ ብሄረሰብ በሰፊው የሚወራበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህና በየእለቱ በሚያጋጥሙ የተለያዩ ሁነቶች ውስጥ በመቆየት መረጃዎች ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች ተሰብስበዋል፡፡

መረጃ የመሰብሰቡ ሒደት ከተገባደደ በኋላ የቡድን ውይይቱ የካቲት 29፣ 2004 ዓ.ም ተካሒዷል፡፡ በኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮች ዘንድ ቀኑ የባለእግዚአብሄር ወርሃዊ በዓል

የሚሆንበት ቀን ስለሆነ ስራ ስለማይሰራ ከቅዳሴ በኋላ ከአራት ሰዓት ጀምሮ ለቡድን ውይይቱ ቀጠሮ በመያዝ ሊከናወን ችሏል፡፡

በቡድን ውይይቱ ወቅት አንድ አስገራሚ ነገር ገጥሞኝ ነበር፡፡ አደመ ተስፋ የተባሉት መረጃ አቀባይ ከቡድን ውይይቱ በፊት ባሉት ቀናት መረጃ ልቀበላቸው በመኖሪያ ቤታቸው ስሔድ ረዳቴን ብቻ ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጥተውት እኔን አስተዋውቆኝ እኔም የመጣሁበትን ቦታ እና አላማ ብቻ ተናግሬ መረጃ ተቀብያቸው ነበር፡፡ በቡድን ውይይቱ ወቅት ግን ቢተውሽ አዳነ የተሰኙችው መረጃ አቀባይ ‹‹እሷ'ኮ የአለማየሁ ጊዮን ልጅ ናት›› ስትላቸው እኚሁ መረጃ አቀባይ አንገቴን አንቀው ከሳሙኝ በኋላ ለረዥም ሰዓት አልቅሰው አብረዋቸው የነበሩትን ሰዎች እንዲሁም እኔን ካስለቀሱኝ በኋላ ለአባቴ አጎቱ እንደሆኑ እና እሳቸው ቤት እስከ አራተኛ ክፍል እንደተማረ ነገሩኝ፡፡ በዚህ አጋጣሚ አንድ የስጋ ዘመዴን ተዋወቅኩ፡፡

በአጠቃላይ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ብዙ መረጃ አቀባዮቼ በቀናነት ተቀብለው መረጃዎችን ሰጥተውኛል፡፡

በወረዳዋ ለሰላሳ ሁለት ቀናት መረጃዎችን ስሰበስብ ቆይቼ መጋቢት 4 ቀን 2004 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ፡፡

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች

ይህን ጥናት በማከናወን ሂደት ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ችግሮች ገጥመውኝ የተለያዩ መፍትሔዎችን ወስጃለሁ፡፡

የመጀመሪያው ችግር የዚገም ወረዳን በተመለከተ የጽሁፍ መረጃ እና ካርታ ማግኘት ያለመቻል ችግር ነበር፡፡ ይህ ችግር የተከሰተው ወረዳዋ አዲስ ወረዳ ከሆነች ገና አንድ ዓመት ያልሞላት በመሆኑ የጽሁፍ መረጃዎችን ለማግኘት ባለመቻሉ ነው፡፡

ለዚህ ችግር እንደ መፍትሄ የወሰድኩት የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የሚሰጡኝን የቃል መረጃዎች መጠቀም ነው፡፡ ስለዚህ ስለ ወረዳዋ አጠቃላይ ገጽታ አቶ

ወንዳየሁ ምናሉ የወረዳዋ ሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ በቃል የሠጡኝን መረጃ ለዚህ ጥናት ግብዓትነት ልጠቀም ችያለሁ፡፡

ሁለተኛው ችግር ደግሞ ድሂ ወደሚባለው የገጠር ቀበሌ ለመሄድ ከቻግኒ ዚገም የሚመላለሰውን አውቶብስ መጠበቅ ግድ ነው፡፡ አውቶብሱ ደግሞ በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ደርሶ መልስ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ መረጃዎችን ሰብስቤ የምጨርስበት ሰዓት አውቶብሱ የሚያልፍበት ሰዓት ጋር ስለማይገጣጠም ሊያመልጠኝ ይችላል፡፡

ለዚህ ችግር እንደ መፍትሄ ስወስድ የነበረው በድንገት የሚያልፉ የጭነት መኪናዎችን በመጠበቅና በመለመን ከተፈለጠ እንጨት ወይንም ከእህል ጋር በመጫን ወደ ማረፊያዬ መመለስን ነበር፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቃላዊ ዝርው ተረክ እንዲሁም የቃላዊ ዝርው ተረክንና ማንነትን ግንኙነት በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸውን ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡ ለጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች መተንተኛነት የተመረጠው ንድፈ ሀሳብም ቀርቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችን በመዳሰስና አንድነታቸውን በማሳየት ለዚህ ጥናት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መግለጽ እንዲሁም ልዩነታቸውን በመጠቆም ደግሞ ጥናቱ የሚሞላውን ክፍተት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ፎክሎር በጣም ሰፊ እና ዘርፈ ብዙ በመሆኑ በተለያየ መልኩ ከፋፍሎ ማጥናት የተሻለው አማራጭ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ Sims (1968:12) ፎክሎርን ቃላዊ (verbal) ፣ቁሳዊ (material) እና ልማዳዊ (customary) በማለት ሲከፋፍሉት Dorson 1971:4 ደግሞ ፎክሎርን በአራት የጥናት መስኮች ከፋፍለዋቸዋል፡፡ እነዚህም ቃላዊ ፎክሎር (oral Folklore)፣ ሃገረሰባዊ ልማድ (social folk custom)፣ ቁሳዊ ባህል (material culture) እንዲሁም ሀገረሰባዊ ጥበብ (Folk art) ናቸው፡፡ ፈቃደ (1990:11) ይህን የዶርሰንን ሃሳብ መሰረት በማድረግ ቃላዊ ፎክሎር በቃላት አማካይነት በሚፈጠሩት በተረት፣ በሌጀንድ፣በሚት፣ በቃል ግጥም፣ በምሳሌያዊ ንግግር፣ እንቆቅልሽ፣ በእንካ ሰላንቲያ እና የመሳሰሉትን ስለሚያጠቃልል ስነ ቃል ብለን ልንጠራው እንደምንችል ይገልጻሉ፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረክ አንዱ የስነ ቃል ዘርፍ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስለ ቃላዊ ዝርው የተለያዩ ምሁራን የሰጧቸውን ብያኔዎች እና ጽንሰ ሃሳቦች አቀርባለሁ፡፡

### 2.1.1 ቃላዊ ዝርው ተረክ

በቃላዊ ዝርው ተረክ ላይ ትኩረታቸውን አድርገው ጥናት ከደረጉ ምሁራን መካከል ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት Jacob Grimm እና Wilhelm Grimm የተሰኙ ጀርመናውያን ወንድ ማማቾች ናቸው። (Dorson 1972፡1) ።

እንደ ወንድማማቾቹ አገላለጽ ዝርው ተረኮች የጥንታውያን ህንድ ጀርመን ሚቶች ቅሬቶች ናቸው። ስለ አማልክት እና ጀግኖች የሚተረኩ ተረኮች ከእነዚህ ቅሬቶች ከመነሳት እንደገና የተጠሩ ሲሆኑ የአስማት ተረቶችም ቢሆን በእነዚሁ ኢንዶ ጀርመኖች ተፈጥረው በስደት እና በሌሎች የባህል ግንኙነቶች አማካይነት ወደ ተለያዩ ማህበረሰቦች የተሰራጩ ናቸው። ከእነሱ በኋላ በአርያን ሚቶች ላይ ጥናቱን ያደረገው Muller ደግሞ ተረኮች በአርያኖች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የተፈጠሩ መሆናቸውን ሲገልፅ Lang ም የአርያኖችን እና ክላሲካል ሚቶችን ከአውሮፓውያን ተረቶች "ሞቲፍ" ጋር በማነፃፀር ተረኮቹ በቅድመ ታሪክ ወቅት ከነበሩ የሰው ልጆች ልማዶች (customs) እና እምነቶች (Beliefs) የመነጩ እንደሆኑ ይገልፃሉ። (Degh 1969:55)

Oring (1986፡122) እንደሚገልፁትም ቃላዊ ተረኮች ቋንቋ ከተፈጠረ ጀምሮ የነበሩ እና እስከአሁንም የሚገኝ እንዲሁም ሁሉም ማህበረሰብ በየትኛውም የስልጣኔ እርከን ውስጥ ቢሆን የሚጠቀምበት ነው። የጥንታዊ ኃላቀር (Primitive) እና አርሶ አደር (Peasantry) ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ የሚገኝ የስነ-ቃል ዘርፍ አይደለም።

ስለዚህ ቃላዊ ዝርውተረክ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ የስነ-ቃል ዘርፍ ነው። ይህን ሀሳብ በተመለከተ ፈቃደ(1999፡52) ተረክ በማንኛውም ማህበረሰብ ዘንድ ያለ እና በዕለታዊ ህይወት ውስጥ በተለያየ መልኩ የሚከወን ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ። በተመሳሳይ Degh (1972፡54)ደግሞ ቃላዊ ዝረውተረክ ከሰው ልጅ ስልጣኔ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ የሚያረጅ እና ራሱን ከዘመኑ ሁኔታ ጋር በመቀያየር የሚኖር የስነ-ቃል ዘርፍ እንደሆነ ያብራራሉ ።

Oring (1986፡121) ስለ ቃላዊ ዝርው ተረክ ምንነት ሲያስረዱ ተረክ የሰው ልጅ ያካበታቸውን ልምዶቹን ቃላዊ በሆነ መልኩ የሚገልፅበት አንድ መንገድ ነው ይላሉ በዚህ

ከተረክ ምንነት ጋር በተያየዘ Lwis እና Sandra(2001:16) ሲያስረዱ Narrative is a discourse with a clear sequential order that place events in a meaningful way for definite audience and thus gives in sight about the world and peoples experience of it

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ተረክ ሁነቶች ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ቅደም ተከተላዊ በሆነ መንገድ የምናቀርብበት «ዲስኮርስ›› ነው። የራሱ ታዳሚዎች አሉት። ተረክ ስለአለም እና ስል ተረኩ ባለቤቶች ይገልፃል።

De Finna (2003:12) ደግሞ ተረክን ተረክ ካልሆኑ ድርሳናት እንዴት እንደሚለይ ሲገልጹ ተረክ ክስተቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ተቀናጅተው መተረካቸው እና የሚያስደንቁ እንዲሁም ያልተጠበቁ ክስተቶችን የያዙ ታሪኮች ያሏቸው መሆናቸው ተረክ ካልሆኑ ሌሎች ድርሳናት ይለያቸዋል። እነዚህ ያልተጠበቁ ታሪኮች እና ክስተቶች ታሪኩ ስለምን እንደሆነ፣ ታሪኩ የት ቦታ እንደተፈፀመ፣ የታሪኩ ዋና ሃሳብ ምን እንደሆነ፣ የታሪኩ ፍፃሜ ምን እንደሚመስል እንዲሁም የተራኪውን የግል አስተያየትና ማብራሪያ ሁሉ ይይዛሉ ።

ስለ ቃላዊ ዝርውተረክ ምንነት Degh (1972:58) ጠቅለል አድርገው በዝርው መልክ የሚቀርብ ማንኛውም የስነ-ቃል አይነት ቃላዊ ዝርው ተረክ እንለዋለን በማለት ይገልፃሉ ።

ከዚህ የDegh ጥቅል ሃሳብ በተቃረነ መልኩ Bascom (1996 : 3-4) ቃላዊ ዝርው ተረክ ሚቶችን፣ አፈ ታሪኮችን እና ተረቶችን በውስጡ አካቶ የያዘ የስነ ቃል ዘርፍ እንደሆነ ይገልፃሉ። ስለ እያንዳንዱ ሲያብራሩም ሚቶች በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ እውነት የሚቆጠሩ እንዲሁም ከሃይማኖትና ከእምነት ጋር የተያያዙ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ናቸው። አለም ከመፈጠሩ በፊት ስለነበረው ሁኔታ ይተርካሉ። አፈ ታሪኮችም እንደ ሚቶች በተረኩ ባለቤቶች ዘንድ አንዱ እውነት የሚቆጠሩ ሲሆን አሁን ላለው ዓለም ቅርብ የሆኑ ታሪኮች ያተረኩባቸዋል። ገፀ-ባህሪያታቸውም ያለፉ ጀግኖች እና በታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ የሆኑ ክስተቶች ናቸው። ተረቶች ደግሞ እንደ ፈጠራ የሚቆጠሩ የዝርው ታሪክ ዓይነቶች ናቸው። መቼታቸውም በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊሆን ይችላል።

Ben-Amos(1992:101-102) ይህን የቃላዊ ዝረው ተረክ ሚት ፣ አፈ ታሪክ እና ተረት ብሎ በመከፋፈል መገለፅን አይቀበሉትም፡፡ እንደእርሳቸው አገላለፅ ይህ የአውሮፖውያን የቃላዊ ዝርው ተረክ አከፋፈል ተረኮቹ በእርግጥ ማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን የእውነትነት /Factness/ እና ፈጠራነት /fictionness/ መሰረት አድርጐ የተከፋፈለ ቢሆንም አለማቀፋዊ ግን ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የአከፋፈል ስልት ሊኖረው ይችላል፡፡ የማህበረሰብበ ስምምነት፣ አስተሳሰብ፣ አላማ፣ የአተራረክ ዘዴ እና ተረኮቹ ለተራኪው ማህበረሰብ የሚሰጡት ትርጉም ተረኮቹ አከፋፈሉን በየማህበረሰቡ እንዲለያዩ የሚያደርጉት ገፅታዎች /distinictive features/ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ግን ቃላዊ ዝርው ተረክ ከሰው ልጅ የለት ተእለት የህይወት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያለው፤ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር አብሮ የሚነሳ፤ ራሱን ከተለያዩ ማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ እየቀያየረ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ የሚቀርብ፤ የሰው ልጅ ልምዱን፣ አስተሳሰቡን በአጠቃላይ የተለያዩ ሁኔቶችን ቅደም ተከተላዊ በሆነ መንገድ የሚገልፅበት፤ እውነትና ፈጠራነቱ በራሱ በማህበረሰቡ የሚወሰን፤ አለም ከመፈጠሩ በፊት እንዲሁም አሁን ስላለው የማህበረሰቡ ሁኔታ የሚገልፅ እና በዝርው መልክ በቃል የሚቀርብ የስነ-ቃል ዘርፍ ነው ልንል እንችላለን፡፡

በአፍሪካ የስነ-ቃል ጥናት ዘርፍ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት Finnegan (1996:380) ስነ-ቃል ህልውናው ተጠብቆ እንዲቆይ መከወንና በቃል መተላለፍ ይኖርበታል፡፡ ይህ ሀሳብ ቃላዊ ዝርው ተረክ ያለ ክዋኔ ህልዉና እንደሌለው የሚያሳይ ነው፡፡

ለክዋኔ ደግሞ ከዋኝ እና ታዳሚ መኖራቸው ግድ ነው Lwis and Sanda (2001: 251) በማለት ሲገልጹ በተያያዘ መልኩ Dorson (1972:25)እንደሚገልፀው ትረካ ያለ ታዳሚ ፋይዳ እንደሌለው እና የትረካው ትርጉምም ፋይዳውም የሚታወቀው በተራኪው እና በታዳሚው መስተጋብር ውስጥ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

ስለዚህ የቃላዊ ዝርው ተረክን በምናጠናበት ወቅት የተራኪውን እና የታዳሚውን ሚና ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ተረኩ የሚነገርበትን አውድ ማጤን ተገቢ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ Ben Amos /1993:5/ ከማንኛውም የፎክሎር

ዘርፍ በበለጠ የቃላዊ ዝርዉ ተረክ ጥናት አውድን መሠረት አድርጎ መጠናት ይኖርበታል በማለት ይገልፃሉ፡፡ እንደ Sims (1968፡137-139) አውድ የአንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ አባላት በፎክሎራቸው የሚጋሩበት አካባቢያዊ መቼት (physical setting) እና ማህበራዊ ሁኔታ (social situation) ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በታዳሚዎች መካከል ያለው ግንኙነትም አውዱ ውስጥ ይጠቃለላል፡፡ ስለዚህ የአንድን ተረክ ትርጉም በምንተነትንበት ወቅት ከክዋኔው አካባቢያዊ ገጽታ በተጨማሪ በክዋኔው ስፍራ እና ወቅት ያለውን ሁኔታ በአጠቃላይ በትኩረት ማጤን ይገባናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክዋኔው በሚካሄድበት አካባቢ ያለውን ማህበራዊ ሁኔታ ማለትም ዘር፣ ሃይማኖት፣ ስራ፣ ባህል ወዘተ... ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት አንድ ተረክ በተለያየ አውድ ውስጥ በተለያየ መልኩ ስለሚቀርብ ሊቀርብ ስለሚችል እና ተረክ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ትርጉም የሚታወቀው በአውድ ውስጥ ስለሆነ ነው፡፡

ይህን ሃሳብ በሚደግፍ መልኩ Oring ሲያስረዱ ቃላዊ ዝርው ተረክ በቃል የሚቀርብ ከመሆኑ የተነሳ የተለያዩ ባህሪያት አሉት፡፡ የመጀመሪያው አንድ ቃላዊ ዝርው ተረክ ብዙ ቅጅዎች /Versions/ ሊኖሩት ይችላል፡፡ ትክክለኛው እና ቀዳማዊውን መርጦ ለማውጣት ግን አዳጋች ነው ምክንያቱም አንድ ተረክ የተለያየ ሁኔታ /circumstnce/ ውስጥ በተለያዩ መልኩ ሊከወን ይችላል፡፡ ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው የአንድን ተረክ ትርጉምም ሆነ ፋይዳ ስናጠና ተረኩ የሚከወንበትን ሁነት ማጥናት ተገቢ እንደሆነ ነው፡፡ ሁለተኛው ባህሪ ደግሞ ቃላዊ ዝርው ተረክ እንደገና የመባል አጋጣሚ ስለሚኖረው ያለፈ ታሪክ ከአሁን ካለ ሁኔታ ጋር ተቀላቅሎ የማቅረብ ባህሪ አለው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ቃላዊ ዝርው ተረክን ስናጠና ልናስተውላቸው የሚገቡት ነጥቦች ይኖራሉ፡፡ እነዚህም የተረኩ መልእክት ምንድነው? ተረኮቹ እንዲፈጠሩ፣ እንዲተረኩ እና እንዲከወኑ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው እንዲሁም ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ትርጉም ምንድን ነው የሚሉ ናቸው (Degh 1972፡54) ስለዚህ በዚህ ጥናትም በዚገም ወረዳ የሚኖሩ የአዊ ማህበረሰብ አባላት ስለማንነታቸው የሚተርኳቸውን ተረኮች ፋይዳ በሚመረመርበት ወቅት እነዚህ ነጥቦች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡

ቀጥሎ ደግሞ የቃላዊ ዝርው ተረክንና የማንነትን ግንኙነት አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን ያነሱዋቸው ሃሳቦች ይቀርባሉ፡፡

### 2.1.2 ቃላዊ ዝርው ተረክና ማንነት

የተለያዩ ማህበረሰቦችን ማንነት (identity) ትኩረት አድርጎ የፎክሎር ጥናትና ምርምር ማድረግ የተጀመረው ከ1970ዎቹ ጀምሮ ነው፡፡ (Dundes 1984፡149)፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የፎክሎር ምርምር ድርሳንን *(text) እና ምደባ መሠረት አድርጎ ጥናት ከማካሄድ ተላቆ የተረኮችን ትርጉም በመተንተን ላይ ትኩረቱን ያደረገ በመምጣቱ ነው፡፡ (Mathisen 1993፡35)

እንደ Dundes (1986፡132) ፎክሎር ስለ አንድ ማህበረሰብ ማንነት ለማወቅ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እንደ መረጃ ምንጭነት ከማገልገል በተጨማሪ አንድ ማህበረሰብ ወይንም ግለሰብ ማንነቱን የሚፈጥርበት ወይንም የሚገልፅበት መንገድ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፎክሎርን እና የማንነትን ግንኙት ለማወቅ በቅድሚያ ፎክ (folk) የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ መመርመር ተገቢ እንደሆነም ይገልፃሉ፡፡ ሲያብራሩትም ማንኛውም ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ አባላት ያሉበት ቡድን የሚጋራው እና የእኔ ነው የሚለው «ትራዲሽን›› ካለው ፎክ ብለን ልንጠራው እንችላለን፡፡ ቡድኑ ውስጥ ያሉ አባላት እርስ በእርሳቸው ተዋወቁም አልተዋወቁ የሚጋሩትን «ትራዲሽን›› ግን ያውቃሉ፡፡ ይህም ቡድኑ የጋራ ማንነት ስሜት እንዲሰማው ያደርጋል፡፡

Sims ይህንን ሃሳብ ሲያብራሩት «ትራዲሽን›› ቁሦችን፣ ልማዶችንና ስነ-ቃሎችን አንድ ቡድን በጋራ ሲጠቀምበት እና የእኔ ነው ብሎ ማመንን የሚገልፅ ፅንስ ሃሳብ ነው፡፡ ስለዚህ በ‹‹ትራዲሽን›› ማንነት ይገለፃል እንዲሁም ይፈጠራል፡፡ ምክንያቱም ትራዲሽን ሂደትም (process) ማህበረሰቡ የሚጋራው ባህልም (lore) ነው፡፡

---

*ዶክተር ባይለየኝ ጣሰው በክፍል ውስጥ ‹‹text›› ለሚለው እንግልዝኛ ቃል አቻ ‹‹ድርሳን›› በማለት ከተጠቀሙት የተወሰደ

Mathisen (1993፡35) ደግሞ የጋራ ፎክሎር የጋራ ማንነት መገለጫ ነው በማለት ሲያስረዱ Bauman (1972፡32) በበኩላቸው *folk lore is a function of shared identity* በማለት ይገልፃሉ። ስለዚህ ከላይ ከተነሱት ሃሳቦች እንደምንረዳው በፎክሎር ማንነትን መግለፅም መፍጠርም ይቻላል።

Mathisen /1993፡37/ ማንነት የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ሁለት መሠረታዊ ቁም ነገሮችን በውስጡ እንደያዘ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> ....From one point of view, it has to do with the feeling that some thing is and remains the same; the feeling of continuity, on the other hand, having an identity means being different from others. The double meaning of the concept implies that identity should be understood in a dynamic context.... the re-inforcement of group identity is combined with the continuous marking of symbolic boundaries between "us" and "them".

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ማንነት የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የአንድን ነገር ምንነት እና አሁን ባለበት ተመሳሳይ መልኩ መቆየትን ከመግለፅ በተጨማሪ ከሌሎች የተለዩ መሆንንም ያሳያል። ከሌሎች የተለዩ መሆን ሲባል በውስጡ «እኛ›› እና «እነሱ›› ወይንም ሌሎች የሚለው ሃሳባዊ ድንበር እንዳለው እንረዳለን። ስለዚህ ማንነትን ስናጠና አውድን መሠረት ማድረግ ይገባናል።

Dundes በበኩላቸው ቀጣይነት (continuity) ስለ ማንነት ብያኔ ሲነሳ ሊቀር የማይገባ ቁም ነገር እንደሆነ ይገልፃሉ። ስለዚህ አንድ ማህበረሰብ ስለማንነቱ ሲጠየቅ ካለፈ ታሪኩ መጀመሩ ግድ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ማንነት ግለሰባዊ (individual) የጋራ (collective) ሊሆን ይችላል። የዚህ ጥናት ትኩረትም በቃላዊ ዝርው ተረክ አማካይነት የሚገለፀው የጋራ ማንነት ነው።

Lwis እና Sandra (2001፡17) እንደሚገልፁት ማንነት "ማንነኝ" ለሚለው እንቆቅልሽ ጥያቄ መልስ የሚሰጥበት ሲሆን የሚገለፀውም እኛ ስለራሳችን በምንተረካቸው ተረኮች አማካኝነት ነው።

ስለዚህ የማንነት ተረኮች ስንል አንድ ማህበረሰብ ስለራሱ የሚተርካቸው ተረኮች ሲሆኑ እነዚህን ተረኮች ሌላው ማህበረሰብ ለመግለፅ ይተርካቸውም።

የማህበረሰብን ማንነት በተመለከተ Dundus (1993:9) ሲያስረዳ Identity of a group of people consists at their subjective symbolic and emblematic use of any aspect of culture in order to differentiate them selves from other groups.

ከጥቅሱ እንምንረዳው የአንድ ቡድን ማንነት የሚገለፀው ቡድኑ የሚጠቀምበትን ማንኛውንም ዓይነት ባህል እና ከለላው የሚለየውን ነገር በማጤን ነው። *De finna ም እንደሚገልፁት Definition of identity with in social psychology, often refers to sense of belong up to social category* በማለት ነው።

Dundus (1993:9) የተለያዩ ምሁራንን ሀሳብ በመጭመቅ የደረሰቡበትን ድምዳሜ ሲያስረዱ ሙዚቃ፣ ዳንስ እና የማህበረሰብ ጀግኖች፣ የማህበረሰብ ልማዶች እንዲሁም በአጠቃላይ ‹‹ትራዲሽን›› ብዙ ጊዜ የቡድን ማንነት የሚገለፅባቸው መንገዶች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ደግሞ ፎክሎር በውስጡ የሚይዛቸው ናቸው። ምክንያቱም ፎክሎር ሚትን፣ ተረትን፣ አፈ ታሪክን፣ ምሳሌያዊ ንግግርን፣ እንቆቅልሽን፣የሀገረሰብ አልባሳትን፣ ዘር ቆጠራዎችን ወዘተ በውስጡ ያካትታል።

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው የአንድ ማህበረሰብ ማንነት በተለያየ መልኩ ሊገለፅ እንደሚችል ዋናው ጉዳይ ተረኩ ማህበረሰቡን ከሌላ ማህበረሰብ እንዴት እንደሚለይ ማሳየቱ ላይ ነው። ስለዚህ የስነ ቃል ክፍል የሆኑት ቃላዊ ዝርው ተረኮችም ማንነትን መፍጠርና መግለጽ ይችላሉ። ይህን ሀሳብ በሚጋራ መልኩ Sims (1963:168) እንደሚያስረዱት ተረኮች ብዙ ጊዜ የማህበረሰቡን አመለካከት የያዙ እና የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ስለ ተረክ እና ማንነት ዝምድና De Finna (2003:19) ሲገልፁ የተረክና የማንነት ግንኙነት በሶስት መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። እነዚህም አንደኛ ተራኪው የማህበረሰቡን ቋንቋ እና የአነጋገር ዘዬ በመጠቀም ትረካውን ማቅረቡ ያ ማህበረሰብ የቋንቋ አጠቃቀሙ ምን እንደሚመስል እና ከሌላ ማህበረሰብ እንዴት እንደሚለይ ያሳያል።

ሁለተኛው ግንኙነት ደግሞ ተራኪዎች በተረኮቻቸው አማካይነት እነሱ የሚገኙባቸው ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ማህበራዊ ግንኙነት ምን እንደሚመስል ያሳያሉ። ከዚህ በተጨማሪ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ባህል ወይ ይወቅሳሉ ወይንም ደግሞ ያርማሉ። ሶስተኛው የማንነነት እና የተረክ ግንኙነት ደግሞ ተራኪዎች ያ ማህበረሰብ ወይንም ግለሰብ ከሌላ አንፃር ሲታይ ምን እንደሚመስል ያሳያሉ።

ከእነዚህ ሶስት ነጥቦች መካከል የመጀመሪያው ነጥብ የማህበረሰቡን የቋንቋ አጠቃቀም ስለሚመለከት ይህ ጥናት በጥልቀት ትኩረት አይሰጠውም። ነገር ግን ሁለተኛው እና ሶስተኛው ነጥቦችን ይህ ጥናት ይጋራቸዋል። ምክንያቱም ሁለተኛው ነጥብ የማህበረሰቡን ሁኔታ የሚገልፅ ሶስተኛው ነጥብ ደግሞ ከሌላው ማህበረሰብ አንፃር ሲታይ ማህበረሰቡ ምን እንደሚመስል የሚያሳዩ ተረኮችን ስለሚመለከቱ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት ሀሳቦች መነሻነት በዚህ ጥናት ውስጥ የዚገም ወረዳ የአዊ ብሄረሰብ የማንነት ተረኮች ተብለው የሚወሰዱት ብሄረሰቡ ስለራሱ የሚተርካቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ብቻ ናቸው።

## 2.1.3 ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ

የተለያዩ የፎክሎር ምሁራን የፎክሎር ድርሳኖችንና ክዋኔዎችን ለመረዳት እንዲሁም ለመተንተን የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን ይጠቀማሉ። ከእነዚህ ንድፈሃሳቦች አንዱ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional approach) ነው። ይህ ንድፈ ሃሳብ የአንድን ማህበረሰብ ቃላዊ፣ ቁሳዊ እና ልማዳዊ ሀብቶችን በመመርመርና ፋይዳቸውን ወይንም ተገባራቸውን የሚያሳይ እና የሚገልፅ ነው(Sims1964፡124)።

እንደ Ben amos (1942፡115) አገላለጽ የተረክ ተግባር በሚመረመርበት ጊዜ ትኩረት የሚሰጠው ለራሱ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ መሠረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በመነሳት ተገባራዊ ትንተና (functional interpretation) ሲካሄድ በሁለት መልኩ ነው። አንደኛው ምልከታ (observation) በመጠቀም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተረኩን ወስዶ ትርጉሙን በመተንተን ነው። በምልከታው ተረኩ የሚከወንበትን ሁነት ወይም

(occasion) በማጤን ሲካሄድ ከዚህ በተጨማሪ ተረኩን ወስዶ ጭብጣዊ ትንተና (thematic analysis)በማከናወን የተረኩን ፋይዳ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ተረኮች የማህበረሰቡን ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ማለትም ፍርሃቱን፣ አለመረጋጋቱን እና ስጋቱን ወዘተ ሊገልፁ እንደሚችሉ ደግሞ ከመላ ምት (assumption) በመነሳት መግለፅ ይቻላል፡፡ ይህም ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ከሳይኮ አናሊቲክ ንድፈ ሃሳብ የተዋሰው ዘዴ ነው፡፡

ከተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አራማጆች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት Bascom ናቸው፡፡ እንደሳቸው አገላለፅ ፎክሎር አራት ዋና ዋና ተግባራት አሉት፡፡ እነዚህም የማዝናናት ወይንም የማስደነቅ (Amusement) የባህልን ጠቀሜታ ማስረገጥ (validating cultures)፣ ባህልን ጠብቆ የማቆየት (maintaining cultural conformity to accepted patterns of behavior) እና የማስተማር (educating) ተግባራት ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ፈቃደ (1997፡17) ከፎክሎር ዘርፎች ስነ-ቃልን ብቻ ነጥለው ወስደው አምስት ተግባራት እንዳለው ይገልፃሉ፡፡ እነዚህም የማጠናከር፣ የመትከል፣ የማምለጫነት የማስተማር እንዲሁም የመግለጥና የመቆጣጠር ተግባራት ናቸው፡፡ ካሉ በኋላ ነገር ግን የስነቃል ተግባራት እነዚህ ብቻ ናቸው፡፡ ብሎ መደምደም አይቻልም ምክንያቱም የስነ-ቃል ተግባራቱ ባህላዊ አካባቢን (cultural area) እና ማህበራዊ ሁኔታን (social milieu) ያገናዘቡ ቢሆኑ መልካም ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ Bauman (1992፡ 277) ፎክሎር በጣም ዘርፈ ብዙ ግልጋሎቶች እንዳሉት ያስረዳሉ፡፡

Ben Amos (1992፡113) እንደሚያስረዱት ማንኛውም ተረክ ያለ አንድ ምክንያት አይተረክም እንዲሁ ለባልት ወይም ፈንጠዝያ (Fantasy) እንኳ የሚተረኩት ተረኮችም ቢሆን እንኳ የራሳቸው ምክንያት አላቸው፡፡ ፈንጠዝያም ያለ ምክንያት ትርጉም የለውም፡፡ ከላይ የተለያዩ ምሁራን የቃላዊ ዝርው ተረክን ፋይዳ በዝርዝር ሲያሳዩ Finnegan (1992፡120) በበኩላቸው ስለተረኮች ፋይዳ ጠቅለል አድርገው ሲያስረዱ ታሪኮች አንድ ሁለት ተብሎ ተቆጥሮ የማያልቅ ፋይዳዎች አሏቸው ከማለት በሚከተለው መልኩ ሃሳባቸውን ይገልፃሉ፡፡

> Verbal formulations regard as 'oral' traditions, verbal art, folklore, narrative or what ever can have a near infinite range of function, different event to depend on where and to whom you look at what level

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ማንኛውም በቃል የሚቀርቡ የፎክሎር ዓይነቶች ተቆጥሮ የማያልቅ ግልጋሎት አላቸው፡፡ ልዩነት የት፣ ለማን እና በምን ያህል መጠን ተረኮችን እንደምንረዳቸው ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ሃሳቦች መሠረትነት በዚገም ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ የአዊ ማህበረሰብ አባላት የማንነት ቃላዊ ዝርው ታሪኮች ምን ፋይዳ አላቸው ብሎ ለመመርመር ያስችላል ተብሎ ስለታመነበት ይህ ንድፈ ሀሳብ በዚህ ጥናት ተግባር ላይ ሊውል ችሏል፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከ1982 እ.ኤ.አ ጀምሮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የውጭ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ እንዲሁም በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የተሰሩ አስራ አንድ የኤም.ኤ ጥናታዊ ፅሁፎች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህን ጥናቶች ብቻ መርጦ ለመቃኘት ያስፈለገበት ምክንያት ለጥናቱ ካላቸው ቅርበት እና ጥቅም አንፃር ነው፡፡

ስለዚህ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት አላቸው ተብለው የተመረጡት አማረ ሞላ "የሸክቾ ብሄረሰብ ሀገረሰባ ተረቾች ምደባ የአከዋወን ስልትና ይዘት ትንተና (1990 ዓ.ም)፣ ማን ያለው አባተ ‹‹የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች እና ፋይዳቸው›› (1999 ዓ.ም)፣ ምንዳ ገብሬ «የጌዲኦ ልማዳዊ ስርዓች ዝርው ቃል ተረኮቻቸው» (1999 ዓ.ም)፣ ከሁሉም በላይ «የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት››(2004ዓ.ም)፣ አብዱል ቃድር ሀጂ ጃማ "Some Cultural Elements as Reflected in Somalia Folktales" (1982 G.C)፣ ተስፋዬ ገብረማርያም "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales" (1990 G.C) ፣መልአክነህ መንግስቱ፣ "The major themes and motif of southern Agaw folktales (1990 G.C)፣ ይሄነው ጀምበሬ "Generic classification of Amharic oral prose narratives of west Gojjam (1996 G.C)፣ ሳህሉ ኪዳኔ "Borana Oromo Oral Prose Narratives: a contextual

study" (1999 G.C)፣ አብርሃም አለሙ "Jimma Ormo Oral Prose Narrative: A preliminary descriptive analysis" (2000 G.C)፣ እንዲሁም ባይለየኝ ጣሰው "an Ayuaa, Oral Prose Narrative: Ethnic Geners and Social Functions" (1999)፣ የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህ ጥናቶች ከተነሱበት አላማ አንፃር እንደሚከተለው ተከፋፍለው ይዳሰሳሉ፡፡

### 2.2.1 በጭብጥ ላይ የተመሰረቱ ጥናቶች

አብድል ቃድር ሐጂ "Some Cultural Elements as reflected in Somali folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በ1982 እ.ኤ.አ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ የአጥኚው አላማ ተረቶቹን ሰብስቦ በማጥናት የሶማሌን ብሔረሰብ ባህላዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ሰማንያ ሁለት ተረቶችን ሰብስቦ ጭብጣቸውን መሰረት በማድረግ በስምንት ክፍል መድቦ አቅርቧል፡፡ የተረኮቹ ጭብጦችም ብልሃት ወይንም ጥበበኛነት፣ ፍትህ፣ ሃማኖተኛነት፣ ጋብቻን የተመለከቱ እና ሴቶችና ቅናትን የተመለከቱ የሚሉ ናቸው፡፡ አጥኚው በጥናቱ ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ ጭብጣቸውን በመተንተን ያሳየ ቢሆንም መረጃ የሰበሰበበት መንገድ ላይ ክፍተት ታይቷል፡፡ አብድል ቃድር ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች የሰበሰበበት ቦታ ጅጅጋ ስደተኞች ካምፕ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ (1982፡23) ይህ ደግሞ የጥናቱ ቀርነት ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ካምፕ ውስጥ ብቻ የተሰበሰበ መረጃ አጠቃላይ የሶማሌን ብሔረሰብ ስነ ልቦናዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ያሳያል ብሎ መደምደም ይከብዳል፡፡

መላክነህ መንግስቱ 1990 እ.ኤ.አ ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡ ይህም "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ ነው፡፡ በጥናቱ ስልሳ የሚደርሱ ተረቶችን ሰብስቦ በስምንት ጭብጣዊ ክፍሎች ከፋፍሎ አቅርቧል፡፡ አጥኚው ተረቶችን ሰብስቦ ጭብጣቸውን እና «ሞቲፋቸውን›› በመመርመር ያላቸውን ማህበራዊ እና ባህላዊ ጠቀሜታ ማሳየት እና የህዝቡን ስነ ልቦናዊ እንዲሁም ስነ ምግባራዊ አመለካከት መመርመር የሚል አላማ ይዞ ተነስቷል፡፡ በድምዳሜውም ተረቶቹ የማህበረሰቡን መልካም እሴቶች ለማስተማር

እና የወጣቶቹን ስብዕና በጥሩ መልኩ ለመቅረፅ እንደሚያገለግሉ ገልጿል፡፡ መላክነህ የሰበሰባቸውን ስልሳ ተረቶች በተለያዩ ጭብጦች መድቧል እነዚህም አምባገነንነት፣ ተስፈኝነት፣ ትእግስት ወይንም አለመታገስ፣ ሞኝነት፣ ስስት እና ማስመሰል ናቸው፡፡ እነዚህን ጭብጦች መሰረት በማድረግ ነው የማህበረሰቡን አመለካከት ለመመርመር የቻለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተረኮቹ ‹‹ሞቲፍ›› ምን እንደሚመስል በዝርዝር አሳይቷል፡፡

ሌላው ጭብጥን መሰረት አድርጎ የተሰራው ጥናት የተስፋዬ ገብረ ማርያም "A Study Of Major Themes in Jablawi Folktales" ነው፡፡ ይህም እንደ መላክነህ ጥናት ለውጭ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በ1990 እ.ኤ.አ የቀረበ ነው፡፡ በጥናቱ ከሰበሰባቸው ውስጥ ሰባሁለቱን መርጦ ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡ አላማው የተረቶችን ጭብጥ በመተንተን የማህረሰቡን እምነትት ማህበራዊ እሴት እና ለአለም ያላቸውን አመለካከት ማሳየት ነው፡፡ ተስፋዬ ሰባሁለቱን ተረኮች በሀያ አምስት ጭብጥ ከፋፍሎ አቅርቧል፡፡

ሶስቱ ጥናቶች ተረኮቹ የሚያነሷቸውን ጭብጦች በመመርመር ላይ በማተኮር ጥናታቸው ሲያቀርቡ ሶስቱም ከተረኮቹ ጭብጦች በመነሳት ተረኮቹ ውስጥ የማህበረሰቡ አመለካከት ምን እንደሚመስል አሳይተዋል፡፡ ከሁለቱ ጥናቶች በተለየ የመላክነህ ጥናት መረጃዎች ከተሰበሰቡበት ቦታዎች መካከል ዚገም አንዱ ነው፡፡ ይህም ከእኔ የጥናት ቦታ ጋር ያመሳስለዋል፡፡

### 2.2.2 በምደባ ላይ የተመሰረቱ ጥናቶች

በዚህ ርዕስ ስር በቅድሚያ የሚዳሰሰው የይሄነው ጀምበሬ "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam" የሚል ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡ ይህ ጥናት ለውጭ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በ1996 እ.ኤ.አ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በተጠቀሰው የጥናት አካባቢ የሚገኙ ተረኮችን መሰብሰብ እና መመደብ ነው፡፡ ለምደባው መሰረት የሆኑት ቁም ነገሮችም፡- ማህበረሰቡ ለተረኮቹ ያለው አመለካከት፣ ያተራረክ ስልት እና የገፀባህሪያት አሳሳል የሚሉ ናቸው፡፡ አጥኚው በሶስት ወር የመስክ

ቆይታው መቶ ሰላሳ ስምንት ተረኮችን ሰብስቧል፡፡ እነዚህን ተረኮቹ ሀገረሰባዊ ተረቶች፣ አፈታሪኮች እና ዘር ቆጠራዎች (genealogy) በማለት መድቧል፡፡

ሳህሉ ኪዳኔ "Borena Oromo Oral Prose Narrative: A Contextual Study" የሚል ርዕስ በ1996 እ.ኤ.አ ለውጭ ቋንቋና ስነ ዕሁፍ ትምህርት ክፍል ጥናቱን አቅርቧል፡፡ የሳህሉ ዋና አላማ በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ተረኮችን ሰብስቦ አይነታቸውን ማሳየት ነው፡፡ አጥኚው ሰባ አራት ተረኮችን ሰብስቧል፡፡ እነዚህን ተረቶች ማህበረሰቡ የሚጠራው መጠሪያ መሰረት "ዱሪዱሪ" (የልጆች ተረቶች)፣ "ማማክሳ" (የጎልማሶች ተረቶ) እና "አርጋጌቴ" (ሚቶችና አፈታሪኮች) በማለት በሶስት ከፍሎ አቅርቧቸዋል፡፡ ነገር ግን አጥኚው በጥናቱ እንደቀርነት ሊታይበት የሚችለው ነገር በጥናቱ ቃለ መጠይቅ መጠቀም አለመጠቀሙን አለመግለፅ ነው፡፡ ምክንያቱም ቃለ መጠይቅ ስነ ቃል ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (Goldstein 1964:76)

ሌላው ምደባን መሰረት አድርጎ የተሰራ ጥናታዊ ዕሁፍ የባይለየኝ ጣሰው "An yuaa, Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions" ነው፡፡ ባይለየኝም ቀደም ሲል እንደተጠቀሱ ጥናቶች ጥናቱን ለውጭ ቋንቋና ስነ ዕሁፍ ትምህርት ክፍል ያቀረበው ነው፡፡ ጥናቱ በ1999 እ.ኤ.አ የተሰራ ነው፡፡ የጥናቱ አላማ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን የባህል ባለቤቶችን የአመዳደብ ስልት በዋና መመደቢያ ስልት ወስዶ ተረኮቹ ያላቸውን ተግባር መመርመር ነው፡፡ አጥኚው አንድ መቶ አስራ ስምንት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ሰብስቦ ሊሪ (the lerree)፣ ዋኤ (the wae) እና አንጋዴ (the angade) በማለት መድቧቸዋል፡፡

አብርሃም አለሙ "Jimma Oromo oral prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis" የሚል ጥናት በ2000 እ.ኤ.አ አቅርቧል፡፡ የአብርሃም ጥናትም ለውጭ ቋንቋና ስነ ዕሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የኤም.ኤ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ማህበራዊ እና ባህላዊ አውዶችን መሰረት በማድረግ ተረኮችን መለየትና መበየን፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ቃላዊ ዝርው ተረኮችን መለየት፣ ተጠኚው ማህበረሰብ ተረኮችን እንዴት እንደሚመድባቸው ማሳየት፣ ተረኮቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች መመርመር እና የተረኮቹን ባህሪያት ማጥናት የሚሉ አላማዎች አሉት፡፡ ተረኮቹን "ሴና"

(Seenaa) "በማለት በሶስት መድቧቸዋል፡፡ ምደባው አውድን መሰረት አድርጎ የማህበረሰቡን የአመዳደብ ስልት የተከተለ ነው፡፡

አማረ ሞላ "የሼክቾ ብሄረሰብ ተረቶች ምደባ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋ እና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ጥናቱን በ1999ዓ.ም አቅርቧል፡፡ የጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው የሼክቾ ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ ተረቶችን በመሰብሰብ መተንተን ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አከዋወን ስልትንና ይዘትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አጥኚው የሰበሰባቸውን ሰባ አራት ተረኮች አካባቢያዊ ምደባን ተከትሎ መድቧል፡፡ ከይዘትም አንፃር ተረቶቹ ብልህነትን፣ መጥፎ ባህሪያትን፣ ፍትሀዊነትን፣ ጓደኝነትን፣ ትዕግስትን እና ወጣትነትን እንደሚያሳዩ ገልጿል፡፡

በመጨረሻ የሚቃኘው ምደባ መሰረት አድርጎ የተሰራ ጥናት የማንያለው አባተ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርእስ ‹‹የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ፋይዳቸው›› የሚል ነው፡፡ ጥናቱ ለኢትዮጵያ ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ኤም ኤ ማሚያ በ1999 ዓ.ም የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማዎች በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ጥናት ማድረግ እና የቤንች ብሄረሰብ አባላት የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችን ለይቶ መግለጽ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በዚህም መሰረት የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ‹‹ቤንችቶስ›› እና ‹፣ኤሽሽ›› ተብለው በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ እንደሚመደቡ ይገልጻል፡፡ ይህም ምደባ ከክወና አውዳቸው፣ ከአፈጣጠራቸው ከታሪኩ እውነተኛነትና አውዳቸው፣ ከአፈጣጠራቸው ከታሪኩ እውነተኛነትና ከትረካው ግብ ዓላማ አንጻር እንደሆነ ያስረዳል፡፡

በዚህም መሰረት ‹‹ቤንቺ ቶስ›› በቀን የሚተረክ በአካባቢው የሚታወቁ ታሪካዊ ሰዎችን የተመለከቱ አፈታሪኮችና የብሔረሰቡን ባህላዊ እምነትና የአምልኮ ስርዓት የሚመለከት ሲሆን፤ ኤሸሽ ደግሞ የፈጠራ ተረክ እና ክንዋኔውም በምሽት እንደሚካሔድ ይገልጻል፡፡

ምደባን መሰረት አድርገው የተሰሩት እነዚህ ስድስት ጥናቶች ተረኮችን ብቻ ወስደው ጭብጣቸውን በመመርመር ከተሰሩት የእነ አብድል ቃድር፣ መላክነህ እና ተስፋዬ ጥናቶች በተለየ የተረኮች ትንታኔ አውድን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ሞክረዋል፡፡

### 2.2.3 ተረኮችና ባህላዊ ሥርዓቶች የተጣመሩባቸው ጥናቶች

ምንዳ ገብሬ "የጌዲኦ ልማዳዊ ስርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው" በሚል ርዕስ ጥናቱን ለኢትዮጵያ ስነ ፅሁና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በ2000ዓ.ም የቀረበ የኤም.ኤ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ በጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ምን ምን ግንኙነቶች እንዳሉ መመርመር፣ የተረኮቹ ይዘት ምን ምን እንደሆነ ማሳየት የተረኮቹን ጎሳዊ ምደባና አካባቢያዊ ስያሜዎችን ለይቶ ማውጣት የሚሉ ናቸው፡፡ በጥናቱ ዝርው ተረኮቹን "ሲንጎ" እና "ማማጎ" በሚል በሁለት ለይቶ አቅርቧል፡፡

ምንዳ በጥናቱ የጌዲኦ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ የአምልኮ፣ የሀዘን እና ሰርግ ስርዓት እንዳለው ገልጿል፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ደግሞ የማህበረሰቡን ስያሜ አመጣጥ፣ የስራ ባህል፣ የእምነት ፅናት እና በዝቅተኛ ኑሮ ያሉት በእርግማን ምክንያት እንጂ ባለመስራታቸው አለመሆኑን እንደሚያመለክቱ ይገልፃል፡፡ የተረኮቹን እና ልማዳዊ ስርዓቶቹን ግንኙነት በተመለከተ ደግሞ ተረኮቹ ልማዳዊ ስርዓቶች ለማጠናከርና ቁርጠኝነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ይገልፃል፡፡

ከሁሉም በላይ "የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ለነፅሁና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ጥናቷን አቅርባለች፡፡ ጥናቷ በ2004 ዓ.ም የቀረበ የኤም.ኤ ጥናት ነው፡፡ የሁሉም ጥናት እንደ ምንዳ ጥናት ሁሉ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ከባህላዊ ስርዓቶች ጋር በማጣመር አቅርባለች፡፡ የጥናቷ አላማ የተጠኚ ማህበረሰብ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች ለአዲስ ትውልድ የሚተላለፍበትን ምክንያት መመርመር፣ በቃላዊ ዝርው ተረኮችና በባህላዊ ስርዓቶች የሚተላለፍ ጉዳዮችን መተንተን፣ የማህበረሰቡ በባህላዊ ስርዓቶች ላይ ያላቸውን አመላከት መፈተሽ እና ተረኮቹ የማህበረሰቡ ስያሜ አመጣጥ፣ የስራ ባህል አምልኮ እንዴት እንደገለፁ ማሳየት የሚሉ ናቸው፡፡ በድምዳሜዋም ቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል የተወሰኑት የማህበረሰቡ ስያሜ ከአመጋገብ ስርዓታቸው ከነገዱ ስም፣ ከስራ ባህላቸውና በአካባቢው ካለ የእህል ፍሬ መጠሪያ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ለማወቅ እንደቻለች ትገልፃለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነገደ

ወይጦ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ የአምልኮ፣ የግርዛትና የስርግ ስነ ስርዓት አለው ትላለች፡፡

ምንዳም ሆነ ከሁሉ ተረኮቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ፋይዳ ከመግለፅ በተጨማሪ ከማህበራዊ ስርአቶች ጋር ያላቸውን ቁርኝት አሳይተዋል፡፡ በዚህም ምንዳ ተረኮቹ ማህበራዊ ስርአቶችን ለማጠናከር ይጠቅማሉ ሲል ከሁሉም ደግሞ ተረኮቹ ማህበራዊ ስርአቶችን ለመግለጽ ያገለግላሉ ብላለች፡፡

ከላይ ለመቃኘት የተሞከሩት ሁሉም ጥናታዊ ፅሁፎች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው አንድ ነገር በቃላዊ ዝርው ተረክ ዙሪያ መሰራታቸው ነው፡፡ ከሁሉም በተለየ ግን የከሁሉም ጥናታዊ ፅሁፍ የቃላዊ ዝርው ተረኮችን ፋይዳ ዋነኛ ትኩረቷ አድርጋ መሰራቷ በይበልጥ ከእኔ ጥናት ጋር ያገናኛታል፡፡ ነገር ግን የእሷ ጥናት ማህበራዊ ስርአቶችንም ስለሚጨምር ልዩነታችን እዚህ ይመጣል፡፡ መላክነህ፣ ተስፋዬ፣ አብዱል ቃድር እና ባይለየኝ በተወሰነ መልኩ ተረኮች ያላቸውን ፋይዳ በማሳየታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ይሄነው፣ አብርሃም፣ሳህሉ ምንዳ እና አማረ ተረኮቻቸው ምደባ ላይ ስለሚያተኩሩ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች አንፃር ሲታይ ይርቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአጠናን፣ የአቀራረብ እና የአገላለፅ ስልታችን የተለያየ ነው፡፡

# 3. የዚገም ወረዳ ህዝብ እና መልክዓ ምድራዊ ገፅታ

በዚህ ክፍል ስለ አዊ ማህበረሰብ ጥንተ አመጣጥ፣ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ፣ ቋንቋ፣ የህዝብ ብዛትና ኢኮኖሚ እንዲሁም ሃይማኖት ይገለጻል።

እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ከዚገም ወረዳ የአዊ ማህበረሰብ አጠቃላይ ገፅታ መካከል የተመረጡበት ምክንያት ከተሰበሰቡት የማንነት ተረኮች ጋር ጥብቅ ትስስር አላቸው ብዬ ስላመንኩ ነው።

## 3.1 ጥንተ አመጣጥ

አዊ በቀድሞው አጠራር አገው ምድር በተባለው እና በአሁኑ አማራ ክልል አዊ ዞን ውስጥ በሚገኙት አንከሻ፣ ባንጃ፣ ፍግታ ለኮ ማ፣ ዳንግላ፣ ጃዊ፣ ጓንጓ እና ዚገም ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ አገዎች የሚታወቁበት የጋራ መጠሪያ ነው (አማረ 1999:2)።

እንደ Tadesse (1988:194) አገው የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በአዱሊስ የድንጋይ ላይ ፅሁፎች (monumentum Addultiam) ተፅፎ ይገኛል። እነዚህ ፅሁፎች በሶስተኛው መቶ ክፍል ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ የተፃፉ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በኢዛና አገዛዝ ዘመን (አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ) እንደተፃፈ የሚነገርለት አንድ የድንጋይ ፅሁፍ ውስጥም ይህን ስም ተጠቅሶ እናገኘዋለን።

Gamst (1984:5) ደግሞ ከ5000 ዓ.ም ጀምሮ የሁሉም የኢትዮጵያ ኩሽ ነገዶች ምንጭ የሆነው የካውካሶይድ የሰው ዘር በሰሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ ስፍራዎች በአደን እና ፍሬ ለቀማ ይተዳደር ነበር በማለት ያስረዳሉ።

Uhlig ደግሞ Cosmosን ጠቅሰው እንደሚገልፁት በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአገው ህዝብ ግዛት ከተከዜ ወንዝ በስተ ምስራቅ እስከ ጣና ሀይቅ ድረስ ይደርሳል። በዘመኑ ዋናው የወርቅ ንግድ መስመርም የአገው ገገር በሚያስተዳድረው በዚህ ግዛት ውስጥ ያልፍ ነበር።

ቀደምት ከሆኑ የኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ ፀሀፊያን መካከል የሚጠቀሱት አለቃ ታዬ (1922፡ 28) እንደሚገልፁት ነገደ አገው በፊት ነገደ አዲል ይባል ነበር፡፡ አዲል ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር ከእስራኤል የመጣ የየጁ እና ላስታ ገዥ ነበር በማለት ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ ነገደ አዲል የተባሉት በዚህ ገገር ስም ነበር ፡፡

Ayenew (2007/8፡5) በሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አክሱም ውስጥ አገዎች ይዘው የነበረውን ቦታ አገዎች በአክሱም መንግስት መስፋፋት ወቅት ወደ ላስታ እና ሰቆጣ እንዲሸሹ ተደረገ እስከ አስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ቆይተው በንግድ ምክንያት ሲዘዋወሩ ጎጃም በመድረሳቸው እዛው ሰፍረው እንደቀሩ ይገልፃሉ፡፡

Uhlig (2003:142) አገዎች የሰሜንና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ቀደምት ህዝቦች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በአካባቢው ታሪክና ባህል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ኣላቸው በማለት ይገልፃሉ፡፡ Tadesse (1972፡5) በበኩሉ ከጀማ ወንዝ በስተሰሜን እስከ አባ ወንዝ በስተምስራቅ ከዚህም በተጨማሪ ከበሽሎ (Bashillo) ወንዝ በስተምስራቅ እና ደቡብ የሚገኘው አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ቀደምት ህዝቦች ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡ በእነዚህ ምሁራን ሀሳብ መሰረት አገው ቀደምት ከሆኑት የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል አንዱ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

አገዎች በአብዛኛው የኢትዮጵያን ክፍል መቼ እንደተቆጣጠሩ እና መቼ ስልጣን እንደያዙ የታሪክ ማስረጃዎች በግልፅ ባያስረዱንም የላስታ አገዎች የዛጉዌን ስርዎ መንግስት በመመስረት አብዛኛውን ጥንታዊት ኢትዮጵያን እ.ኤ.አ ከ1137-1270 መግዛታቸው የተረጋገጠ ነው፡፡ ይህ ዘመን የዛጉዬ ስርዎ መንግስት ስልጣን ላይ የቆየበት ዘመን ነው (Gamst 1964:21):: ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ Uhlig (2003:142) እንደሚያብራሩት ይህ ዘመን የአገውኛ ተናጋሪ ከሆኑት የቀማና የላስታ ህዝቦች በተጨማሪ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ አገዎች ዘራቸውን ከዛጉየ ስርዎ መንግስት ጋር አያይዘው እንዲናገሩ አስችሏቸዋል፡፡ ከስርዎ መንግስቱ መውደቅ በኋላም ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች እንደተሰራጩ ያምናሉ፡፡

እንደ Taddesse (1972:27) አገው ምድር እና መተከል ውስጥ የሚኖሩ አገዎች የእነሱ ቅደመ አያቶች ከላስታ ሰባት ሆነው እንደመጡ እና “የሰባት ቤት አገው” የሚለውን ስያሜም ከሰባቱ ወንድማማቶች ግዛት ጋር ተያይዞ እንደመጣ የሚነግሩ ስነ ቃሎች አሏቸው። ይህንን መረጃ የምናረጋግጥበት ጥናት እስካሁን አልተገኘም ነገር ግን በረጅም ርቀት ንግድ የተነሳ አገዎች ወደ አገው ምድር (አዊ ዞን) ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ መስፈር ጀምረዋል። ከስድስተኛው እስከ አስራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ግዛታቸው እስከ ደንቢያ ይደርስ ነበር።

Ayenew (2007/8:10) ደግሞ የአገው ህዝብ ወደ አገው ምድር ከመምጣቱ በፊት አገው ምድር (አዊ ዞን) በተለያዩ ብሔረሰቦች የተያዘ ነበር ይላል። Taddesse (1972:27) ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ እንደሚገልፀው አገዎች ወደ አገው ምድር ከመምጣታቸው በፊት በስፍራው የሚኖሩ ቀደምት ህዝቦች የጉምዝ እና የሽናሻ ማህበረሰቦች ነበሩ። እነዚህ ብሄረሰቦች እስካሁን ከአቸፈር በስተ ምዕራብ እስከ ኢትዮ ሱዳን ድንበር ድረስ ሰፍረው ይገኛሉ።

እንደ ታዬ (1922: 9) አባባል ደግሞ የላስታ አገዎች ወደ ዳሞት ሰባት ሆነው ዝሆንና ጎሽ ለማደን ሲመጡ ሰው ወደ ሌለበት ጠፍ እንደሆነ አይተው በየዱሩ እና በየዛፉ ማር እየቆረጡ እና የእንስሳት ስጋ አድነው እየበሉ ለሰባት ወራት ከቆዩ በኋላ ምሽቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ይዘው መጥተው አገሪቷን አቀኗት ።

## 3.2 መልክዓ ምድራዊ ገፅታ

አዊ ዞን በአማራ ክልል ከሚገኙ አስራ አንድ ዞኖች መካከል አንዱ ነው። ዞኑ በደቡብ ከኦሮሚያ ዞን፣ በምዕራብ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በሰሜን ምዕራብ ደግሞ ከሰሜን ጎንደር ዞን ጋር እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ከምስራቅ ጎጃም ዞን ጋር ይዋሰናል።

በዞኑ ስድስት ወረዳዎች ይገኛሉ። እነዚህም አንከሻ፣ ባንጃ፣ ዳንግላ፣ ጓንጓ ፋግታ (Zelalem 2001:17) እንዲሁም ዚገም ወረዳዎች ናቸው።

ዚገም ወረዳ ሐምሌ 1፣ 2003 ዓ.ም ራሷን የቻለች ወረዳ እስክትሆን ድረስ በጓንጓ ወረዳ ስር ትተዳደር ነበር፡፡ ወረዳዋ ከአዲስ አበባ 595 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህር ዳር ደግሞ 210 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

ወረዳዋ በአራት ቀጠናዎች ማዕከል የተከፋፈለች ናት እነዚህም ቅላጅ ቀጠናዎች ማዕከል፣ ጎሃናዊ ቀጠናዎች ማዕከል፣ አህቲ ቀጠናዎች ማዕከል እና ጎደር ጀዋ ቀጠናዎች ማዕከል ናቸው፡፡ በነዚህ ቀጠናዎች ማዕከል ውስጥ አስራ አራት የገጠር ቀበሌዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ቅላጅ፣ ጎሀናጅ፣ ጅሞራ፣ ናናችባላ፣ አህቲ፣ አካኮ፣ ኩሲ፣ ጊሳይታ፣ አበይ ኮሉብ፣ አምቡቃይና ገፈጫ፣ አበራች ዛዝበል፣ ዕውሲ፣ ጎደርጃዊ እና ሳሳ ዱባክቻ ናቸው፡፡ *

## 3.3 ቋንቋ

ከኩሽ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ አንዱ የሆነው አውኚ (አገውኛ) የአዊ ማህበረሰብ ቋንቋ መጠሪያ ነው፡፡ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መጠሪያም ይጠሩታል፡፡ ከነዚህም መካከል የመካከለኛው ኩሽ (Central Cushitic)፣ አገው እንዲሁም የደቡብ አገው በማለት ይጠሩታል (Uhlig 2003:404)፡፡ የደቡብ አገው የተባለበት ምክንያት በስተ ምዕራብ ከሚነገረው ቅማንትኛ፣ በሰሜን ከሚነገረው ብሌን እንዲሁም በምስራቅ ከሚነገረው ህምጥኛ በንፅፅር ሲታይ በስተ ደቡብ ስለሚገኝ ነው (Zelalem 2011:17)፡፡

አገውኛ (አውኚ) በአዊ ዞን ሁሉም ወረዳዎች ውስጥ የሚነገር ሲሆን በተጨማሪም በቤንሻጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን በቤንሻንጉል እና ሽናሽኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች መካከል በሚገኙ አገዎች ይነገራል፡፡ ቋንቋው በአሁኑ ወቅት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋ ከመሆን ባሻገር እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣል፡፡

---

* አቶ ወንዳየሁ ምናሉ የወረዳዋ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ፤ የካቲት 07፣2004 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

እንደ (Gamst 1984:23) በመካከለኛውና ሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ አገውኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከአገውኛ ቋንቋ በተጨማሪ የአማርኛ ወይም ትግርኛ ቋንቋዎችን መናገር ይችላሉ። ይህ የሆነበት ምክንያት የአገውኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከአማርኛና ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ጋር የነበራቸው የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ። ይህን ሃሳብ በተመለከተ (Gamst 1984:124) የአገውኛ ተናጋሪ ህዝቦች ለብዙ ክፍለ ዘመናት ከአማርኛ እና ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ጋር ግንኙነት ነበራቸው። የባህል መመሳሰልም ይታይባቸዋል በማለት ያስረዳሉ። በተለይም ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ በአገውኛ ቋንቋ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሯል። ይህንን ተጽእኖ አማራይዜሽን (Amharization) ብለው የተለያዩ ምሁራን ይጠሩታል። Amharization የሚለውን ሃሳብ መልአክነህ (1990:3) ሲያብራሩ የአማርኛ ቋንቋ በአገውኛ ቋንቋ ላይ የወሰደው የበላይነት እንደሆነ በመግለጽ ነው። ለዚህ መከሰት የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ምክንያቶችን ያቀርባሉ። ከነዚህ መካከል መልአክነህ (1990: 29-30 )የአገውኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ከላስታ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች መፍለስ አንዱ ቋንቋው በአማርኛና በትግርኛ ቋንቋ ተጽእኖ ስር የመውደቅ ምክንያት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ግን የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት በአባ ተክለሃይማኖት መሪነት እና በቤተክርስቲያን አስተባባሪነት ያደረገው ጸረ ዛጉዌ እንቅስቃሴም አንዱ ምክንያት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አማርኛ የስራ እና የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ መቆየቱ በአገውኛ ቋንቋ ላይ ተጽእኖ የፈጠረ ሌላው ምክንያት እንደሆነ ያስረዳሉ። በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ በአገውኛ ቋንቋ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ Gamst (1984:124) Amharization በአገው ብሄረሰብ ላይ ያደረሰውን ተጽእኖ ያክል ሌላ ብሄረሰብ ላይ አላደረሰም በማለት ይገልጻሉ። (Tadesse 1972:27) በአሁን ወቅት አማራውን ከአገው ለይቶ ለማወቅ ቀላል አይደለም። ብዙ አገዎች አማርኛ ቋንቋ ከመናገራቸው በተጨማሪ መጠሪያ ስማቸው ሁሉ የአማርኛ ትርጉም ያላቸው ናቸው። የአገውኛ ትርጓሜ ያላቸው መጠሪያ ስሞች ለማግኘት ብዙ ትውልዶችን ወደ ኋላ መቁጠር ግድ ነው በማለት ያስረዳሉ።

በዚገም ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የአዊ ብሄረሰብ አባላትም የዚህ ተጽእኖ አካል ናቸው። የወረዳዋ ነዋሪዎች በብዛት ከአገውኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማርኛ መግባባት ይችላሉ።

## 3.4 የህዝብ ብዛት እና ኢኮኖሚ

በዚገም ወረዳ ውስጥ 92,825 የሚደርስ ህዝብ ይኖራል፡፡ 47,251 የሚሆኑት ወንዶች ሲሆኑ 45,574 የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ከወረዳው ህዝብ 90% የሚሆነው በግብርና ስራ እና 10% የሚሆነው ደግሞ በንግድ ስራ ይተዳደራል፡፡ *

ጥንታዊ አገዎች ከደቡብ አረብያ በስርጭት የደረሰውን ስንዴና ገብስ የመሳሰሉትን የተለያዩ ሰብሎች ያመርቱ እንደነበረና በአካባቢያቸው የሚገኙትን መበላት የሚችሉትን ሌሎች ሰብሎችን በማላመድና አገልግሎት ላይ በማዋል የታወቁ ነበሩ፡፡ ይኼውም ለግብርና እድገት እንደ መነሻ ያስቆጥራቸዋል (Gamst 1961:8)፡፡ የአሁኑ የአዊ ማህበረሰብም ከሚተዳደርባቸው የገቢ ምንጮች መካከል ግብርና ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል (Zelalem 1999:24)

## 3.5 ሀይማኖት

በሰሜን ኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ አገዎች የክርስትና ሀይማኖት ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቀደም ብለው ተቀብለዋል፡፡ በአዊ ዞን ውስጥ የሚኖሩ የአዊ ማህበረሰብ አባላትም ከአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት ጀምሮ የክርስትና ሀይማኖትን ተቀብለዋል፡፡ በዚህ የተነሳ አጼ ዮሐንስን “ጻድቁ ዮሐንስ” እያሉ ይጠሯቸዋል (Uhlig 2003፡139-143)፡፡ በአሁኑ ወቅት የአዊ ማህበረሰብ በአብዛኛው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ነው (Zelalem 2001)፡፡ በማለት ሲገልጹ መላክነህ (1990:27) ደግሞ ባህላቸው ከሃይማኖታቸው ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚገም ወረዳ ህዝብ መካከልም 97% የሚሆነው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆን 3% የሚሆነው ደግሞ እስልምና እምነት ተከታይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ግን የአዊ ብሄረሰብ በኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ፣ ባህል፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ የሚጫወተው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም ለማለት ያስችለናል፡፡

---

* አቶ ወንዳየሁ ምናሉ የወረዳዋ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ፤ የካቲት 07 2004 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

# 4. የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና

በዚህ ክፍል በዚገም ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ የአዊ ብሄረሰብ አባላት ስለማንነታቸው የሚተረኳቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንታኔ ይሰጥባቸዋል፡፡ ትንታኔው የሚደረገው ተረኮቹ ያላቸውን ፋይዳ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በትንተናው የተመረጠውም ንድፈ ሃሳብ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ይህን ንድፈ ሃሳብ መሰረት አድርገን ተረኮችን ስንተነትን በሁለት መልኩ ሊሆን እንደሚችል የBen Amos ሀሳብ እንደሚያስረዳ በክፍል ሁለት ተገልጿል፡፡ ይሔውም ተረኩ የሚከወንበትን አውድ መሰረት ማድረግ እንዳለብን ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የተረኮችን ይዘት ማጥናት እንደሚገባን አስረድቷል፡፡ ሌላው ነጥብ ደግሞ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ስነ ልቦናዊ ፋይዳ ለመቃኘት ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች በተጨማሪ የአጥኚው መላ ምት ወይንም አጥኚው በመስክ ቆይታ ወቅት የተገነዘበውንና የተረዳውን ሊያነሳ እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ ስለዚህ ትንታኔው እዚህን ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት ይደረጋል፡፡

የተሰበሰቡት የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ብሄረሰቡ ስለማንነቱ ሲጠየቅ የሚቀርባቸው ማስረጃዎች ናቸው፡፡

በተረኮቻቸው ውስጥ የሚገለጹት የታሪኩ ባለቤቶች መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በበጎ ስራቸው እና በፈጣሪ ስለመመረጣቸው የሚነገርላቸው ግለሰቦች፣ ታዋቂ ነገስታት፣ ማህበረሰቡ ብቻ የሚያውቃቸው ጀግኖች ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ንግስት ሳባ፣ አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ላሊበላ እና ንጉስ ሰለሞን በታሪክ ውስጥ ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦች ሲሆኑ ከቅዱሳን መካከል ደግሞ ቅዱስ ገብርኤልን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የብሄረሰቡ ጀግኖች የሚባሉት ሰባቱ ወንድማማቾች ማለትም አንከሻ፣ ባንጃ፣ ጫራ፣ ቱምሃ፣ መተከል፣ ዚገምና አዘና ናቸው፡፡

እያንዳንዳቸው ተረኮች ጭምቅ ታሪኮች ናቸው ምክንያቱም ለረጅም ጊዜ የተከናወኑ ክስተቶች ቅደም ተከተል ይዘው እና ተደራጅተው ቢበዛ ሁለት ገጽ ባልበለጠ የሚቀርቡባቸው ትረካዎች ናቸው፡፡

ሁሉም የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች መነሻቸው ያለፈው ዘመን ማረፊያቸው ደግሞ አሁን ያለው የማህበረሰቡ ሁኔታ ነው፡፡ ታሪኩ ያለፈው ዘመን ተጀምሮ እዚያው ያለቀ ቢሆን እንኳን ተራኪዎቹ  አሁን ካለው ዘመን ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ያሳያሉ፡፡ ያለዚያም ደግሞ ተረኮቹ አሁን ካለው የማህበረሰቡ ሁኔታ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡

የብሄረሰቡ አባላት የሚተርኳቸው አብዛኛው የማንነት ተረኮች ብሄራቸውን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ራሳቸውን በአዊ ዞን ሌሎች ወረዳዎች ውስጥ ከሚኖሩ አገዎች ነጥለው አያዩም፡፡ የማንነት ተረኮቻቸውም ከነዚህ የአዊ ዞን አገዎች ጋር የተያያዘ ነው፡፡

አብዛኞቹ ተራኪዎች የሚተርኩት ትረካ እነሱ ያዩት ወይንም የተሳተፉበት በማስመሰል እና በቦታው የነበሩ በሚመስል ሁኔታ በእርግጠኝነት የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ጥቂቶች ደግሞ ከአባቶቻቸው ወይንም ከቀደሙ ሰዎች የሰሙት ታሪክ እንደሆነ ‹‹አባቶቻችን እንዳቆዩት››፣ ‹‹ነው ሚሉ››፣ ‹‹እንደተባለው›› እና ‹‹ኑና››* የሚሉ ቃላትን በመጠቀም ከሌሎች የማህበረሰቡ አባላት የሰሙት ትረካ እንደሆነ ይመሰክራሉ፡፡ አንድ ተራኪም እንዲሁ የተረኩት ተረክ እሳቸው  ከመሬት አንስተው የተረኩት እንዳልሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቁ ሰዎችን በመጥቀስ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ ‹‹ቀኝ አዝማች በላይ ስዩም ከፊታውራሪ ደረሶ የሚበልጡ ናቸው፡፡ ፊታውራሪ ዘለቀ ተሰማ ለኛ አጎት ናቸው፣ እና ራሳቸው ፊታውራሪ ደረሶ የነገሩኝ ታሪክ ነው እኔ ዝም ብዬ የተናገርኩት አይደለም›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ ተራኪዎች ለትረካቸው ምንም አይነት ቅድመ ዝግጅት አያደርጉም፡፡

በወረዳዋ የሚኖሩ የብሄረሰቡ አባላት ተረክ ለመተረክ ብለው ያስቀመጧቸው የተለዩ ስፍራዎችና ቀናት የሉም፡፡ ነገር ግን በጋራ የሚያሰባስቧቸው አጋጣሚዎችና ክብረ በዓላት ሲኖሩ እንዲሁም ተረኮችን የሚተርኩባቸው ምክንያች ከተከሰቱ ተረኮቹ ሊተረኩ

---

*‹‹ኑና›› የሚለው የአገውኛ ቃል የአማርኛ አቻው ‹‹አሉ›› ነው

ይችላሉ። የብሄረሰቡን አባላት በጋራ ከሚያሰባስቧቸው አጋጣሚዎች መካከል ማህበር (ማምቤሪ)፣ የተለያዩ አውዳመቶች ‹‹አሜትባል›› (ከነዚህ መካከል የመስቀል በዓል በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል።)፣ ግንኙ (ዛሃዚሚዲ)፣ሃዘን (እዝን)፣ ሰርግ (ሃስ) እንዲሁም ስብሰባዎች (ኩፕቲ) ናቸው።

የማህበረሰቡ አባላት የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውን ጥንተ አመጣጣቸውን፣ (አሰፋፈራቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ከታዋቂ የታሪክ ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመግለጽ እና ሌሎች ማህበረሰቦች ስለ እነሱ የሚሏቸውን አባባሎች በማስቀልበስ ወይንም በማስቀየር ስነ ልቦናዊ እፎይታ የመስጠት ፋይዳ አላቸው። ትንተናውም በእነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ተከፋፍሎ እና ድምዳሜ ላይ እንዴት እንደተደረሰ ለማሳየት በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

## 4.1 ጥንተ አመጣጣቸውን ለመግለጽ የተተረኩ ተረኮች

የአዊ ብሄረሰብ አባላት ጥንተ አመጣጣቸውን በተረኮቻቸው ሲገልጹ የዘር ግንዳቸው ከየት እደሚጀምር በማስረዳት ነው። በዚህም መሰረት የዘር ግንዳቸው ከእስራኤሉ ንጉስ ከንጉስ ሰለሞን እንደሚጀምር ያስረዳሉ። ንግስተ ሳባ ደንገጡሯን አስከትላ የንጉስ ሰለሞንን ዝና ሰምታ ጥበቡን ለማየት በሔደችበት ወቅት የተከሰተው ሁኔታ ለአገው ዘር መነሻ እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህንንም በተረኮቻቸው አማካይነት በሚከተለው መልኩ ይገልጻሉ። ከተረኮቻቸው መካከል ወሬኛ ዘውዴ የተረኩትን እንመልከት።

ወሬኛ ዘውዴ በዚገም ወረዳ ቅላጅ ከተማ ነዋሪ ናቸው። እድሜያቸው 85 ሲሆን በጡረተኝነት ይተዳደራሉ። የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይም ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በወረዳዋ ነዋሪዎች ዘንድ የሚታወቁት በሀገር ሽማግሌነታቸው ነው። ይህንን ትረካ በቤታቸው ጓሮ የተረኩት ነው። በትረካው ወቅት እሳቸውን ጨምሮ እኔ እና ረዳቴ ባይሞት ምንይሉ ነበርን።

> … ንጉስ ሰለሞን ነብይ ስለሆነ ‹‹ለአበሾች በርበሬና አሻቦ የበዛበት ምግብ ስጣቸውና ዘወር በል›› ይላል ንጉሱ ሰለሞን ፊት ለፊት ነው እንደዚ. (በእጃቸው ወደ ፊት እየጠቆሙ) ምኝታ ማስተናገጃ የተሰጣቸው እንደዚ ሰለሞን ፊት ለፊት ይተያያሉ። ውሃ ጥም ሲያቃጥላቸው

ውሃው ጧንጧ ያለ ከንጉስ ሰለሞን ምኝታ አካባቢ ነው ያለ፡፡ ንግስቲቱ እንቅልፍ ሲወስደው ሂጂ ሰርቂ እጠጣለሁ ብላ አስባ እያለች ንጉሱ ያንቀላፋ መስሎ ሰርቃ ስትጠጣ ያዛት፡፡ ‹‹ያንድ ሀገር ንጉስ ያንድ ሀገር ንግስት እንዴት ይይዛል›› ብትል ‹‹በኢትዮጵያ ሴባ የለም ብለሽ ነበርሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሰርቂ ተይዘሻል፡፡ ያንድ አገር ንግስት ያንድ አገር ንጉስን ንብረት እንዴት ይሰርቃል?›› አላት ከዚያ በኋላ ሲጨቃጨቁ ያው ሴት መሆን አይቀርም ተገናኛት፡፡ እና ቀዳማዊ ምኒሊክ ተረገዘ፡፡ ባንድ ለሊት፡፡ ይሔ የእግዚሃር ፈቃድ ነውና ሂዳ ወደ ምኝታዋ እንትን ስትል ደንገጡሯ ‹‹ውሃ ጠጥተሽ መጣሽ›› ስትል ‹‹አዎ›› አለች ይህን ነገር ተደረግሁ አላለችም፡፡ አሷም ጠጥታ ልትመለስ ልትጠጣ ስትል እሷንም ደገመ፡፡ ከዚያ ዛጉዬ ተረገዘ ባንድ ለሊት ነው የተረገዙ፡፡ ከዚያ ሶስት ወር ቆይታ የሰለሞንን ቤተ መንግስትና ህገ ኦሪትን ተምራ ሲመለሱ መንገዱ ስድስት ወር ነው የሚፈጅ፡፡ ሁለቱም ባንድ ቀን ምጥ ተያዙ ‹‹ውሃ አምጪ›› ‹‹ውሃ አምጪ›› ሲባባሉ ቦታውም ማይቤላ ተባለ፡፡ …


ሲያድጉ ንግስቷ የሰለሞንን ፎቶ እያሳየች ነው ያሳደገች፡፡ ምኒሊክ ስሙ ምን ሊግ ነው፡፡ ከአልጋ ወደ አልጋ ማለት ነው፡፡ በዚያው በነሱ አነጋገር፡፡ ከዚያ በኋላ አድገው አምሮ አግኝተው ሰው ሲሆኑ አባታቸው ዘንዳ ሲደርሱ ማቆያ ቤት ሁነው ሁሉ ከተዘጋጀ በኋላ አሳሳች መኳንንቶችን ዘውድ አስጭኖ እሱም ዘውድ ጭኖ ‹‹በሉ እንግዴህ አባታችሁን ለዩ›› ተባሉ፡፡ ምኒሊክ የአባቱን ፎቶ ያይ ስለነበረ ጋድ እሱን አሉ ሚመስል ቀብ አረገ አባቱን፡፡ እንደገና ዛጉዬ ወደ መሳሳቱ ይልና በኋላ ግንለየ አዛገ አለው ‹‹ቢሳሳትም ልጁ ነው›› ማለቱ ነው፡፡ ---አዎ በዚያ በነሱ ቋንቋ ነው፡፡ ከዚያ ለተወሰነ ጊዜ ትምህርተ ኦሪትና ህግን ሲማሩ ቆዩ ሁለቱ ልጆች ጋድ ሰለሞንን ነው ሚመስሉ፡፡ እና ህዝቡ ልጆችህን ስደድልን ይላል ‹‹እኔ የበኩር ልጆቼ ናቸው ከናንተስ የበኩር ልጆችን የሚሰድ ማነው›› አለ፡፡ በኩርማት የበኸር የመጀመሪያ ማለት ነው፡፡  ሀያራት የበኩር ልጆቻቸውን ሰጡ እስራኤላውያን፡፡ በኋላ የደብር አስተዳዳሪውም ምንም እስራኤላውያን  ሁኖ… ሁለት ታቦት ብቻ ነበረ እስራኤል ውስጥ የነበረ የዚያን ግዜ ሚካኤልና ጺወን፡፡  ጺወንን ይዘው ሺ እግረኛ ሺ ፈረሰኛ ሁነው ሀያራቱ እስራኤላውያን የደብር አስተዳዳሪ ሁነው… ሚስጥሩን ስለሚያውቁ እነዚ እስራኤላውያን ልብሱን የሚካኤልን አርገው የጺወንን ታቦት ይዘው ሲመጡ እስራኤላውያን እርስ በርስ ሲበጣበጡ እስኪ ታቦቱን ፍቀዱ ሲባል ጺወን የለችም ሚካኤል ነው ያለ እንዳሁን ባየር ተሯሩጠው የሚመጡት አደለም፡፡ አሁን ታቦት አለች ተብሎ አይነገርም ፈረንጆች በሀይል እንዳይወስዱ ተብሎ ነው፡፡ … እና የሰለሞንን ህገ መንግስቱን ተምረው መጠው የለ? ንግስቲቱ ከሞተች በኋላ መጀመሪያ ምኒሊክ ነገሰ ከዚያ ዛጉዬ የአገው ስርዎ መንግስትን ይዞ ለሶስት መቶ ስንትስ አመት ገዛ፡፡ (ወሬኛ ዘውዱ፣ የካቲት 9፣ 2004 ዓ.ም)

ጥንተ አመጣጣቸውን በተመለከተ የተተረኩትን ተረኮች ትንታኔ ከመስጠቴ በፊት በምእራፍ ሶስት አጠቃላይ ገጽታ ከተጠቀሱት ነጥቦች መካከል ከዚህ ተረክ ጋር ተያያዥ ያላቸው ነጥቦች አነሳለሁ፡፡ የመጀመሪያው ሃሳብ የዚገም ወረዳ የአዊ ማህበረሰብ አባላት መካከል 97% የሚሆኑ

የክርስትና እምነት ተከታይ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ የዛጉዌ ስርወ መንግስት የአገው ስርወ መንግስት መሆኑና ከ1137-1270 እ.ኤ.አ. ስልጣን ላይ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ ነው።

ከላይ የሰፈረው ተረክ የአዊ ብሄረሰብ አባላትን ዘር ከየትነት የሚገልጽ ነው። የዘር ግንዳቸውን ከመግለጽ በተጨማሪ ግን አንድ አብይ ፋይዳ አለው። ተረኩ ለማህበረሰቡ የራሱ ታሪክ መነሻ እና ምንጩ ነው። ምክንያቱም የማህበረሰቡ ዘር፣ ሀይማኖት፣ ከሌሎች ማህበረሰቦች አንጻር ሲታይ ያለው ደረጃ ሁሉ እዚህ ተረክ ውስጥ ይገኛል። ሌሎች የብሄረሰቡ የማንነት ተረኮች ይህ ተረክ ባቆመላቸው መሰረት ላይ የተመሰረቱ ይመስላሉ።

ይህንን ሃሳብ ለማብራራት ተረኮቹ ውስጥ ያሉት አብይ ሁነቶችን አንድ በአንድ በመመርመር ሁነቶቹ የሚሰጡትን ትርጉም በማየት ትርጉሙ የሚፈጥረው የተረኩ ፋይዳ ናቸው ተብለው ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ሃሳቦች እንደሚከተለው አመሳክራለሁ።



አባ ወሬኛ ዘውዴ በትረካ ላይ (የካቲት 9፣2004 ዓ.ም)

የብሄረሰቡ ዘር በፈጣሪ የተመረጠ እንደሆነ የሚገነባልን በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚጠቀሱ በፈጣሪ ዘንድ ከተመረጡ እና ቃል ከተገባላቸው ግለሰቦች መካከል አንዱ የሆነው ሰለሞንን በመጥቀስ ነው። ሰለሞን በጠቢብነቱ ከመታወቁ ባሻገር አባቱ ዳዊት

ፈጣሪ እንዲህ የሚል ቃል እንደገባለት በመጽሀፍ ቅዱስ (መዝ 89÷4) ‹‹ለባሪያዬ ለዳዊት ማልሁ። ዘርህን ለዘለአለም አዘጋጃለሁ። ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሰርታለሁ››

በዚህም መሰረት ዘሩ እና ስልጣኑ ዘለአለማዊ የሆነ ዘር መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ስለዚህ ከፍ ያለ ደረጃ እና ስልጣን የሚገባው ዘር መሆኑን ያሳያል። ከስልጣን ጋር በተያያዘ አገው የሆነው ዛጉዌ ስርዎ መንግስት ለ‹‹ሶስት መቶ ስንትስ›› አመት መግዛቱን ተያይዞ በተረኩ መብራራቱ የዘሩን ደረጃ ይገልጻል። ስለዚህ ይህ ተረክ ስለ አዊ ዘር ቀደምትነትና በፈጣሪ መመረጥን የሚያሳይ ነው። ከመጽሀፍ ቅዱስ የተመረጡ ሰዎች መካከል አንዱን ጠቅሶ የዘር ግንዳቸውን ማዛመድና መተረክ 97% የሚሆን የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ለሚገኝበት የዚገም ወረዳ የአዊ ማህበረሰብ ተረኩ በማህረሰቡ ዘንድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ እንዲሆን ያደርገዋል።

መልአከ ህይወት ሃብተማርያም (የካቲት 11፣2004 ዓ.ም) የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደሚገልጹት ‹‹አገው አባ ተክለ ሀይማኖት በሚባል መነኩሴ ስብከት አማካይነት በተራ ወሬ ስልጣን የለቀቀ ዘርህ ሁሉ ርስትህ ሁሉ ስር የለውም ብለው በመስበካቸው የተነሳ ነው እንጂ ባለ ርስት ነው።››

በዚህ ተረክ የታቦተ ጽዮን በምኒሊክና በዛጉዬ አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የሀይማኖቱ መሰረት ጥንታዊ መነሻውም እንደዘሩ ሁሉ እስራኤል እንደሆነ እና ሀይማኖቱ የቆየ እንዲሁም ጠንካራ መሰረት ላይ የቆመ ሀይማኖት መሆኑን ይገልጻል። የክርስትና ሃይማኖት በንግስተ ሳባ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ በተረክ አምስት ውስጥ አዳሙ እንዳለው የተባሉት ተራኪ ገልጸዋል። ለሀይማኖተኝነታቸው መገለጫ የማህበረሰቡ አባላት የመስቀል በአል አከባበራቸውን እንደመረጃ እና እንደማሳያ ያቀርባሉ። ‹‹በመስቀል ስላዳንነ መስቀልን በደንብ ነው የምናከብር አዊ እኮ ሀይማኖቱን ጠባቂ ነው›› በማለት ይገልጻሉ።

በተመሳሳይ መልኩ በተረክ 2 ውስጥም ተመሳሳይ ሃሳብ ቀርቦ እናገኛለን። በዚህ ተረክ ንግስት ሳባ የሰለሞንን ጥበብ በአንድ ነጋዴ አማካይነት ሰምታ ደንገጡሯን አስከትላ

እስራኤል በሄደችበት ወቅት ሁለቱም ከሰለሞን መጸነሳቸውን ይገልጻል፡፡ ዛጉዌና ምኒሊክ በተመሳሰይ ቀን ተረግዘው እንደተወለዱና ሁለቱም በየተራ ነግሰው ኢትዮጵያን የመሩ የንጉስ ሰለሞን ልጆች እንደሆኑ ይገለጻል፡፡ የሁለቱ ተረኮች መሰረታዊ ሃሳብም ይህ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን ተረኮቹ ልዩነቶችም አሏቸው ከልዩነታቸው መካከል በተረክ 1 ምኒሊክ አባቱን እንደሚመስል የአባቱን ፎቶ እያየ ማደጉ የተገለጸ ሲሆን በተረክ 2 ደግሞ የራሱ ምስል ውሃ ውስጥ በማየት እንዳደገ መገለጹ አንዱ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ንጉስ ሰለሞን የተረገዙት ልጆች ወንድ ከሆኑ ወርቅ ሴት ከሆኑ ደግሞ ብር በምልክትነት እንዲላክለት ጠይቋል፡፡ ይህ ሃሳብ በተረክ ሁለት ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የብሄረሰቡ አባላት እደሚገልጹት በዱሮ ጊዜ ስል ወይንም ሌላ ዘመናዊ መልእክት የመለዋወጫ መሳሪያ ባለመኖሩ መልእክት ላኪው መልእክተኛ ሲልክ ለመልእክት ተቀባዩ ‹‹እንዲህ እንዲህ ያደረግነው ምልክት ይሁንና ያንን ነገር ለላኩት ሰው ላክልኝ›› ብሎ መልእክቱ ከትክክለኛው ሰው እንደተላከ ማረጋገጫ መላክ ይኖርበታል፡፡ ከላይ የሰፈረውን ተረክ የተረኩት ተራኪ ከተረኩ ጋር በማያያዝ በድሮ ጊዜ የተከሰተ ነው በማለት የሚከተለውን ተረክ ተርከዋል፡፡

> በድሮ ጊዜ የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ባልዬው በጠዋት ተነስቶ ወደ ሩቅ አገር ዘመዶቹን ሊጠይቅ ሲሄድ አንድ ሰው ያገኘዋል፡፡ ይህ ሰው ጋር ሰላምታ ሲለዋወጡ በባልዬው ኑግ በልቶ ነበርና ሳቅ ሲል ጥሩ ላይ የተለጠፈ ኑግ ይታይ ነበር፡፡ ይህን ያዬው መንገደኛ ባልዬውን ተሰናብቶ ወደ ሚስትዮው ቤት ይሔድ እና ‹‹ባልሽ ሲልሽ ማታ በኑግ የበላሁት ምልክት ይሁን ጠመንጃውን ላኪልኝ›› ሲላት እውነቱን መስሏት የባሏን ጠመንጃ አውጥታ ሰጠች አሉ (አበራ የካቲት 12፡ 2004)፡፡

ይህን ተረክ የተረኩት አቶ አበራ አበበ ሲሆኑ ትረካውን በአገውኛ ተርከውት በረዳቴ ባይሞት አማካይነት ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው፡፡ ትረካውን ከሱቃቸው አጠገብ ተቀምጠን የሰጡኝ ሲሆን በትረካው ወቅት እሳቸውን ጨምሮ እኔ ባይሞት እና አንድ እሳቸውን የሚያውቅ ሰው ነበርን፡፡

አንድ ቃላዊ ዝርው ተረክ በተለያየ መልኩ ሊገኝ እንደሚችል የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ በክፍል ሁለት ውስጥ Oring የተባሉ ምሁር

እንዳስረዱት ቃላዊ ዝርው ተረክ በቃል በመተላለፉ ምክንያት አንዱ ተረክ የተለያዩ ቅጂዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ ስለዚህ ይሔኛው ነው ቀዳሚ ማለት አንችልም፡፡ De Finna የተባሉት ምሁርም ተረኮች ከሚተረኩባቸው ጊዜ ከሌላ ቴክስቶች ውስጥ የሚገኙ ታሪኮች ሊቀላቀሉባቸው ይችላሉ ብለዋል፡፡

ስለ ንጉስ ሰለሞን የተተረከው ተረክ በተመሳሳይ መልኩ ክብረ ነገስት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ልዩነቱ ክብረ ነገስት ውስጥ ያለው ታሪክ የምኒሊክ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ የአዊ ማህበረሰብ አባላት ግን ተረካቸው ውስጥ አዛገ (ዛጉዬ) የምኒሊክ መንታ ወንድም እንደ ሆነ መተረካቸው ነው፡፡

ይህን ሀሳብም በመውሰድ የትኛው ትክክል የትኛው ደግሞ ስህተት እንደሆነ ወይም የትኛው ኋለኛ የትኛው ፊተኛ እንደሆነ ለማሣየት እኔ የምከተለው የአጠናን ስልት አይፈቅድም፡፡ ምክንያቱም እንደ Dundes አባባል አንድ ፎክሎር ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ አጠናለሁ ብሎ የተነሳ ተመራማሪ ፎክሎሩ ምንድን ነው? ፎክሎሩ ከየት መጣ? (where does folklore originate?) እንዲሁም ፎክሎሩ እንዴት ተላለፈ የሚሉት ጉዳዮች ሳይሆኑ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው? ለምንስ ይጠቅመዋል? እንዲሁም መቼ እና የት ይጠቅመዋል? የሚሉት ቀዳሚ ጉዳዮቹ ሊሆኑ ይገባል (1975፡277)፡፡

ስለዚህ ይህ የምኒሊክ እና የአዛገ ‹‹መንታ›› ሆኖ መቅረብ (ከአንድ አባት በአንድ ቀን መረገዛቸው) ምንድን ነው ፋይዳው የሚለው ነጥብ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የአዊ ማህበረሰብ አባላት ስለ ብሔራቸው መነሻ ሲናገሩ የሚተርኩት ተረክ የሰለሞናዊው (አማራው) ዘር መነሻ የንግስና መሰረት ታሪክ መነሻ ከሆነው ቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር በመንታነት በማገናኘት ነው፡፡ ይህም የአዊ እና የአማራ ብሔረሰብ አባላት አንድ ዘር ሀረግ እንዳላቸው የሚገልጽ የማንነት ተረክ ነው፡፡ ይህም ሁለቱ በአንድ ክልል እና አካባቢ ውስጥ የሚኖሩ ብሔረሰቦች በጠላትነት እንዳይታዩ እና ‹‹እኛ›› እና ‹‹እነሱ›› የሚለው ድንበር ከልዩነት ይልቅ አንድነትን (ሰላማዊነትን) እንዲያመጣ ያደርጋል፡፡ ወሬኛ ዘውዴ የተባሉ መረጃ አቀባይም ‹‹አንድ ነን እኮ ልዩነቱን በደምብ የማያውቅ ነው

የሚለያየን›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ አማራም ሆነ አገው የንጉስ ሰለሞን ዘር መሆናቸውን ተረኮቹ ያሳያሉ፡፡

የታሪክ ተመራማሪዎች ጥንታዊ የኢትዮጵያ ቀደምት ነዋሪዎች (Indeginious peoples) የሚሏቸውን አገዎች የወረዳዋ የብሄረሰብ አባላት ግን በተረኮቻቸው ጥንታዊነታቸውን በመግለጽ የዘር ግንዳቸው ግን ከሰለሞን እንደሆነ እና የእስራኤል ዘር እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ግን እነዚህ ተረኮች የማህበረሰቡን የዘር ግንድ እና ሀይማኖት ከየት መጣነት እንዲሁም ከሌሎች ብሔረሰቦች አንጻር የሚኖረው ደረጃ ምን እንደሚመስል ያሳያሉ፡፡

## 4.2 የአሰፋፈራቸውን ሁኔታ ለማሳየት የተተረኩ ተረኮች

የአዊ ብሄረሰብ አባላት አሰፋፈራቸውን በተመለከተ ሲተርኩ ከላስታ ሰቆጣ ሰባት ወንድማማቾች አገዎች ለአደን ወደ አገው ምድር (አዊ ዞን) እንደመጡ እና ቦታው ስለተስማማቸው እዚሁ ግዛት ተከፋፍለው እንደ ቀሩ ይገልጻሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ወሬኛ ዘውዴ የሚከተለውን ትረካ ተርከዋል፡፡

> ሰባቱ ወንድማማቾች የሚባሉ አንከሻ፣ባንጃ፣ኳኩራ፣ጫራ፣መተከል፣ዚገም እና ቱምሃ ናቸው፡፡ ዋናው መነሻቸው ላስታ ሰቆጣ ነው፡፡ ከዚያ ተነስተው ጎሽ እና ገዞን ለማደን ነው ወደዚ የመጡ፡፡ የነዚ የሰባቱ አገዎች እናት አዱክ ነው ምትባል፡፡ ከዚያ ቦታው ለምለም መሆኑን ሲያዩ ተመልሰው ሂደው ላባታቸውም ለምሽቶቻቸውም ለዘመዶቻውም ነግረው መጡ እነዚህ አገው ምድርን ተክለው ተከፋፍለው መኖር ጀመሩ፡፡

(ወሬኛ ዘውዴ፣ የካቲት 9፣ 2004 ዓ.ም ከቤታቸው ጓሮ)

ይህ ተረክ የብሄረሰቡ አባላት ጥንተ አመጣጥ እና አሰፋፈር ምን እንደሚመስል ያሳያል፡፡ እነዚህ ሰባት ወንድማማቾች ብሄረሰቡ እንደ ጀግና የሚቆጥራቸው ናቸው፡፡ እንደወሬኛ አገላለጽ ‹‹ጀግና ባይሆኑ ለግዳይ ከላስታ እዚ ይመጡ ነበረ? አይመጡም፡፡

በእነዚ ተረኮች የአዊ ብሄረሰብ የራሱ ጀግኖች አማካይነት የብሔረሰቡ የጀግንነነት መገለጫ አደን (ግዳይ) መሆኑንም ተረኮቻቸው ያስረዳሉ።

አደን የጀግንነት መገለጫ ስለመሆኑ አዳሙ እንዳለው የተባሉ መረጃ አቀባይ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ።

> አገሬ ዚገም የወንድ አገር ነው። በፊት በፊት ግዳይ ይዞ ያልገባ ጀግና አይባልም ነበረ። አውሬ ማደን ያባት ነው። የሰውን ነፍስ ማጥፋት ግን በፈጣሪ የተወገዘ ነው። ዚገም እርስ በርስ መገዳደሉን ያበዛሉ። ዘሩን ዘሩ ማጥፋት ይሄ ጥሩ አይደለም። እኔ አገሬ ዚገምን እወዳለሁ። ‹‹እንኳን ለዚገም ሰው ለዚገም አውሬ ይዋሳል›› ይሉኝ ነበር ድሮ። (የካቲት 17፣2004 ዓ.ም)

ይህ የአዳሙ መረጃ አደን በአዊ ብሄረሰብ በወረዳዋ የአዊ ማህበረሰብ ዘንድ የጀግንነት መገለጫ እንደነበረ የሚጠቁም ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተራኪው ዚገም ወረዳ ውስጥ የሚኖሩት የብሄረሰቡ አባላት ከሚፈጽሟቸው ተግባራት መካከል ነፍስ ማጥፋት ስህተት መሆኑን ጠቁመው አልፈዋል። ደም በመመለስ ሰበብ አንዳንድ የብሄረሰቡ አባላት አልፎ አልፎ ነፍስ ሲያጠፉ ይታያሉ። ይህም እንደአዳሙ አባባል ስህተትና የተወገዘ ተግባር ነው። በአንድ ርእሰ ዙርያ ተረካቸውን ሲያቀርቡ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተቀራራቢ ጉዳዮችን በጎን ማንሳት የአንዳንዶቹ ተራኪዎች ባህሪያት ናቸው።

ሰባቱ ወንድማማች አገዎች ከላስታ ተነስተው ለአደን መምጣታቸውን በተመለከተ መልአከ ህይወት ሃብተማርያም የሚከተለውን ተረክ ተርከዋል። መልአከህይወት ሃብተማርያም ይህን ተረክ የተረኩት በመኖሪያ ቤታቸው በረንዳ ላይ ሲሆን በትረካው ወቅት እሳቸውን ጨምሮ እኔ፣ ረዳቴ ባይሞት እንዲሁም ህጻን ልጃቸው ነበርን። መልአከ ህይወት ሃብተማርያም እድሜያቸው 37 ነው። የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ ቤተክርስቲያንን በማገልገል ስራ ላይ ይገኛሉ።

> ዋናው መነሻቸው ሰቆጣ ላይ ነው። የሰባቱም አገዎች እናት አዱግ ነው ስሟ። ሰባቱ አገዎች የሚባሉ አንከሻ፣ባንጃ ኳኩራ፣ ጫሬ፣ መተከል፣ ዚገም እና ቱምሃ ናቸው። ጎሽ እና ዝሆን እናድናለን ብለው መጠው ቦታውን ስለወደዱ አገው ምድርን ተከፋፍለው መኖር ጀመሩ። (ሃብተማርያም፣ የካቲት 11፣ 2004 ዓ.ም)

Dundes ስፔንሰር የተባለውን ምሁር ጠቅሰው እደሚገልጹት ከመኖሪያ አካባቢ እና ቋንቋ በተጨማሪ ሙዚቃ፣ ዳንስ እና ጀግኖች የተለመዱ የማንነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ (1993:9)

እነዚህ ተረኮች እንደሚያሳዩት የሰባቱ ወንድማማች አገዎች መነሻ ላስታ ነው፡፡ ላስታ የዛጉዌ ስርወ መንግስት የፖለቲካ ማእከል ነው፡፡ ተረኩ ከዛጉዌ ስርወ መንግስት ጋር መያያዙ ቀደም ሲል በተተነተነው ተረክ ውስጥ የተገለጸውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ይህም ዘሩ ከሰለሞን የሆነ ዛጉዬ የተባለ ሰው አገዎች የሚገዙበትን የዛጉዬ ስርወ መንግስት መሰረት፡፡ የዛጉዬ ስርወ መንግስት የፖለቲካ ማእከል ላስታ ነው፡፡ አሁን እየተተነተነ ባለው ተረክ መሰረት ሰባቱ ወንድማማቾች ከላስታ ተነስተው አዊ ዞን ሰፈሩ፡፡ ከአዊ ዞን ወረዳዎች መካከል ደግሞ አንዱ ዚገም ወረዳ ነው፡፡ ዚገም ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ የአዊ ማህበረሰብ አባላት ደግሞ ከሰባቱ ወንድማማቾች አንዱ የሆነው ዚገም ዘሮች ናቸው፡፡

ከላስታ አገዎች ጋር ስላላቸው ግንኙነት አደመ የተባሉ ተራኪ ሲገልጹ

> አደን ሲመጡ አገሩን ለምለም መሆኑን አይተው ተመልሰው መጠው ኖሩ ነው ሚሉ፡፡ እንደዝምድናችን ሁሉ ባህላችን አንድን ነው፡፡ ግን ሰቆጣዎች ባህላቸውን አልለቀቁም የኛዎች ናቸው የተዉ፡፡ ሰቆጣዎች እንዳለ ናቸው፡፡ የጸጉር አላላጭ ላይ ከፍ ያለች፣ ለትዳር የደረሰች፣ ያገባች፣ ያገባች እያሉ የኛዎች ግን እንዲህ የነበረውን ትተዋል አልነበረም ሚል ካለ ይምጣና ከኔ ጋር ይከራከር፡፡ (አደመ፣ የካቲት 18፣ 2004 ዓ.ም፣ በመኖሪያ ቤት ውስጥ)

በዚህ ተረክ መሰረት ሰቆጣዎች ከአዊዎች ጋር የዘር ግንዳቸው እና ባህላቸው አንድ ነበር ነገር ግን የባህል መለያየቱ የመጣው በአዊዎች ባህል እየረሱ እና እየተው መምጣት ነው፡፡

እንደ ታሪክ ተማራማሪው Tadesse (1972:27)

> From bogos in Ertria to agawmider in Gojjam, in all their traditions of origin they indicate Lasta as the area of dispersal Conti Rossini has explained this as being a general tendency of the agaw to show a common origin, and to associate themselves with a political fruites of the Zagwe Daynasty.

ከጥቀሱ እደምንረዳው ኤርትራ ውስጥ ቦጎስ ከተባለው ስፍራ እስከ ጎጃም አገው ምድር ውስጥ የሚገኙ አገዎች ጥንተ አመጣጣቸውን በተመለከተ ከላስታ እደሆነ የመግለጽ ባህል አላቸው። ይህን ደግሞ Conti Rosini የተባለው ምሁር እንደሚያስረዳው ከዛጉዌ ስርዎ መንግስት ስልጣን ጋር ራሳቸውን የማያያዝ አዝማሚያ ነው። ይህን የታሪክ ተመራማሪውን ሀሳብ የጠቀስኩት የተረኮቹን እውነት ወይንም ሀሰትነት ለማረጋገጥ አይደለም። ምክንያቱም እንደ Bascom (1965:7) የተረኮች እውነትና ፈጠራነት በተራኪዎች እና በታዳሚዎች አመለካከት ሲወሰን ይገባዋል።

ይህን የታደሰ ሀሳብ ከእኔ ትንታኔ ጋር የሚያስተሳስረው የዛጉዌ ስርወ መንግስት የስልጣን ማእከል ላስታ እደሆነ ከመግለጽ በተጨማሪ ተረኮቻቸው ውስጥም የብሄረሰቡ አባላት ዘራቸውንና የመጡበትን ቦታ ከዛጉዌ ስርወ መንግስት ጋር የተሳሰረ መሆኑን ስለሚገልጹ ነው። ስለዚህ የብሄረሰቡ አባላት ስለ አሰፋፈራቸው የሚተርኳቸው ተረኮች እንዴት እንደሰፈሩ ከመግለጻቸው በተጨማሪ ጥንተ አመጣጣቸውን እና ለጀግንነት ያላቸውን አመለካከት የማሳየት ፋይዳ አላቸው።

## 4.2.1 ዚገም

‹‹ዚገም›› ስለሚለው ስያሜ የተለያዩ የብሄረሰቡ አባላት የተለያየ ትርጓሜ ይሰጡታል። ከነዚህም መካከል አብዛኞዎቹ ቃሉ ከላስታ ለአደን ሰባት ሆነው ከመጡ ወንድማማቾች መካከል አንዱ የሆነው ዚገም መጠሪያ ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ የቃሉ ትርጓሜ ‹‹ስም ነው›› የሚል እንደሆነ ይገልጻሉ። ዚገም ማለት ‹‹ሂድ ውረድ›› ማለት እንደሆነ የሚገልጹ የማህበረሰቡ አባላት ደግሞ ዚገም ከሰባቱ ወንድማማቾች መካከል ዘግይቶ

ቦታውን በመያዙ የተነሳ ‹‹እንዚግ ጌም›› ሂድ ውረድ ብለው ወንድሞቹ ስለገፋፉት መጠሪያው ከዚህ የመነጨ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የዚገም ወረዳ የአዊ ማህበረሰብ አባላት ስለ አሰፋፈራቸው ስለ ጠቅላላው የአዊ ማህበረሰብ  አሰፋፈር ከመግለጽ በተጨማሪ ስለ ራሳቸው አመጣጥ የሚተርኳቸው ተረኮች ተገኝተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል በዚገም ማህበረሰብ ቀዳሚ አባት ነው ተብሎ የሚታሰበው ከሰባቱ ወንድማማቾች መካከል አንዱ የሆነው ዚገም የተሰኘው ግለሰብ ነው፡፡ በቀዳሚው ተረክ ላይም የወረዳዋ መጠሪያ በዚሁ ግለሰብ ስም መነሻነት እንደተሰየመ ተገልጿል፡፡ ይህም ቦታ ሲከፋፈሉ ዚገም የአሁኑ የዚገም ወረዳ ስለደረሰው ነው፡፡

ቀጥሎ የቀረበው ተረክ ግን ዚገም የተባለው የዚገም አገዎች አባት ወደዚህ እንዳልመጣ እና ሙኻን የተሰኘ ልጁ ወደዚህ መጥቶ ዘጠኝ ልጆቹን ወልዶ ዘሩ ተባዝቶ እዚህ እንደደረሰ ይገልጻሉ፡፡

ይህን ትረካ የተረኩት ካሰዬ አስረስ ናቸው፡፡ እድሜያቸው 74 ሲሆን የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ ትረካው በቅላጅ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ የተካሄደ ሲሆን በትረካው ወቅት እሳቸው፣ አኔ መምህር መንክር የተባሉ የቤተክርስቲያን አገልጋይ እንዲሁም እረዳቱ ባይሞት ነበርን፡፡

> ዚገም አይደለም ወደዚ የወረደ፡፡ የዚገም ሚሽት ሰቆጣ እና ምኾንን ሁለቱን ወልዳ ስትሞት ጎንደር ላይ ሂዶ ማንስ ከሚባል አገር አመጣ፡፡ አዎ ንጉስ ሱሲንዮስ የሚባል ያለበት እንፍራዝ ከሚባል አገር አመጣ፡፡ እሷም ሁለት ልጆች የነበራት ናት፡፡ ይቺ ከጎንደር እንፍራዝ የመጣች ሴት የዚገምን ልጆች በብትር እየደበደበች ቆሎ ብቻ እየሰጠች በራብ ልትጨርስ ስትል ሁል ግዜ ያለቅሳሉ፡፡ ባዲ የሚባል በሬ ዳልጋው መሬት የሚደርስ በሬ ‹‹አይዟችሁ እኔ እናትም አባትም እሆናለሁ አምላክ እናንተን እንዳነጋግር አፌን የከፈተ አምላክ ያውቃል›› ይላል፡፡ በኋላ ሽንቱን ወተት እበቱን እርጎ እያረገ ሲያበላ እነዚ ልጆች በጣም አማረባቸው፡፡ በጣም በጣም ወፈሩ፡፡ አሁን በበረበሬ እያጠነች ስትጠይቅ ሴቷ ባዲ ይሔን አረገልን በማለት ተናገረች ወንዱ ዝም አለ፡፡ ጳጉሜ ሲደርስ ካልታረደ አልኖርም አለች፡፡ መኾንም በሽማግሌ ተይዞ ሲጠየቅ እሺ አርዳለሁ አለ፡፡ ከዚያን ጳጉሜ ሲደርስ ካራውም ተሳለ ‹‹ኧረ ባዲ ካራውስ ተሳለ ልትታረድብን ነው እውይ አሉ›› ወንዱን ትከሻው ላይ አረገ ከዚያ ‹‹አንቺ ሴት ነሽና ኋላ ሁኚ›› ብሎ ዋጅራ አቦን አርጎ ሻሽና

አፋፍ ይደርሳል፡፡ ከዚያ በዶንዶር አርጎ ቻጃ ሙካ ላይ ደርሶ እዚያው ያርፋል፡፡ አሁን እነዚያን ልጆች እበላቸው ካደጉ በኋላ ‹‹እናንተ ሽናሻ ጋር አትጋቡ›› ብሎ ቅዱስ ገብርኤል በብስራት ስለተናገረ በሬው እነዚህን ልጆች ያጋባል፡፡ አዳምም ከጎኑ ላይ የወጣችቱን ነው ያገባ፡፡ እናንተም እርስበርስ ተጋቡ እንጂ ሽናሻ ጋር አትጋቡ ብሎ አጋባ፡፡ ከዚያ ሰቆጣ ማንን ትወልዳለች? ቻንጋን፣ ጓንጓን፣ ሚንጋን ወለደች ራሱ ሞራይ ሙኻንንም ወለደች እነዚህን ወልዳ ሞተች፡፡ አሁን ሙኻን ብቻውን ቀረ ‹‹አንተ ሙኻን ና እኔ መርቼ ልውሰድህ›› ልጆችህን ምታሳድግበት ቦታ ሲል ‹‹ሽናሻ አያሳልፈኝም›› ይላል እንግዲያስ ሂድና ‹‹የቀጋ ብትር ሳትፈቀፍቀው አምጣ›› አለው፡፡ ብትሩን ይዞ ልጆቹን ይዞ ሽናሻ ጋር ተቀላቅሎ ሲሄድ ‹‹ምንሜና ቋንቋ ማያውቅ መጣ ብለው ሽናሻ ሮጦ ሄደ፡፡ ‹‹ሂደህ ሽናሻ ንጉስ የተቀመጠበት ቦታ ላይ ሒደህ ይህን ብትር ተደብቀህ ሰክተህ ቀጥታ ሩጠህ ና›› ብሎ ባዲ ይናገራል፡፡ ከዚያ ሽናሻ መሀል ቆይቶ ጦሩን ሰክቶ ሩጦ ይመጣል ምንድን ነው ይሔን አይነት ነገር ይላል፡፡ የሽናሻ ንጉስ ‹‹እኛ እደዚ ያለ ጦርም አይተን አናውቅም አምላክ እንጂ እኛን የወጋ ሰው አልወጋም›› ብሎ ዱራ ማዶ ሒዶ ሽናሻ ይቀመጣል፡፡ እንገዲህ ቡከር የሚባል ዋና ሽናሻ ብቻ ይቀራል፡፡ እሱ ለዚገም ኩሲያ ቡክር ምትባል ልጁን ይድራል፡፡ እሷ ማንን ትወልዳለች አዋሻን፣ ጫራጃን አንባቂን ማለት ነው ናናን፣ ጎሃናጅን፣ (አሁን የቢምረው አባት ያለበትን) ጊዜን ትወልዳለች፡፡ ዘጠኝ ቤት ዚገም የሚባለውም ‹‹ ሴስቲ ግና ዚገም›› የሚባለው ይሔ ነው፡፡

ይሔን እኔ የፈጠርኩት ታሪክ አይደለም ቀኛዝማች በላይ ስዩም ከፊታውራሪ ደረሶ የሚበልጡ ናቸው፣ ፊታውራሪ ዘለቀ ተሰማ (ለኛ አጎት ናቸው አህቲ ላይ ነው የተቀበሩ) እና ፊታውራሪ ደረሶ ራሳቸው የነገሩኝ ነው፡፡ እና አዊ እንደዚሁ ዘሩ ብርር ብሎ የመጣ አደለም በአምላክ ፈቃድ በእግዜር የተመራ የመጣ አደለም የአዊ ታሪክ... (ካሳዬ፣ የካቲት 18፣ 2004 ዓ.ም)

ይህ ትረካ የዚገም ወረዳ ህዝብን አሰፋፈር የሚያሳይ ትረካ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ሙካን የተባለው ግለሰብ በአምላክ ፈቃድ በበሬ እየተመራ የመጣ ሚስት እዲያገባ የተነገረውም በቅዱስ ገብርኤል ብስራት እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ተራኪውም በትረካቸው መጨረሻ የሚገልጹት ይህንን ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ተረክ ስለ አሰፋፈራቸው ከመግለጽ በተጨማሪ በወረዳው ውስጥ የነበሩት ቀደምት ህዝቦች የሽናሻ ብሄረሰቦች እንደነበሩም ያሳያል፡፡ ነገር ግን በአምላክ ፈቃድ እና እገዛ የሽናሻ ብሄረሰብ አባላትን አስለቅቀው የአዊ ማህበረሰብ አባላት እንደሰፈሩ መግለጻቸው ወራሪ ሆነው ሳይሆን ፈጣሪ እዚያ ቦታ እንዲኖሩ በሬን እንደሰው በማናገር ተዓምር በመስራት ያዘዛቸው መሆኑን ለማሳየት

ነው፡፡ ይህም ትረካቸው ከጎረቤት ሸናሻ ብሄረሰቦች ጋር በሰላማዊ መንገድ እንዲኖሩ እና የቦታ ጥያቄዎች እንዳይነሱ ይረዳቸዋል፡፡

የቦታ ጥያቄ ወይንም በብሄረሰቦች መካከል ግጭት እዳይነሳ ያደርጋል በማለት ተረኩን ከጎረቤት ብሄረሰቦች ጋር በማያያዝ ያነሳሁበት ምክንያት ብዙ ጊዜ የተለያዩ ብሔረሰቦች ማንነት (Ethnic identity) ከፖለቲካ እና ከግጭት ጋር በተያያዘ መልኩ እንደሚነሳ የተለያዩ ምሁራን ስለሚገልጹ ነው፡፡

ከነዚህም መካከል Huntchison እና D.smith (1996:3) የተባሉ የአንትሮፖሎጂ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት

> Ethnic community and identity are often associated with conflict and more particularly political struggles in various parts of the world. We should observe, however, that there is no necessary connection between ethnicity and conflict

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ብሄረሰቦች እና የብሄረሰቦች ማንነት ብዙ ጊዜ ከግጭትና ከፖለቲካዊ ትግል ጋር ተያይዞ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ውስጥ ሲነሳ እናያለን፡፡ ነገር ግን በግጭትና በብሔረሰቦች ማንነት መካከል ምንም አይነት ግንኙነት እደሌለ መገንዘብ ይገባናል፡፡

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰው ተረክም የዚገም ወረዳ ህዝብ እንዴት እንደሰፈረ ከማሳየት በተጨማሪ የአሰፋፈሩ ሁኔታ በሀይል በመውረር ሳይሆን (ከተራኪው የመጨረሻ ገለጻ እና ከጭብጡ በመነሳት) በአምላክ ፈቃድ እየተመራ እንደመጣ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም ከጎረቤት ማህበረሰቦች ጋር በሰላም እንዲኖር ወይንም ተቃውሞ እንዳይገጥመው ይረዳዋል፡፡ ምክንያቱም ከሰው ልጆች በላይ የሆነው ፈጣሪ እየመራ ስላመጣው ሌላው ብሔር ቢቃወም ፈጣሪን የመጋፋት ያህል ይቆጠራል የሚል ሀሳብ ያዘለ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ዚገም ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቦታ ስያሜዎችም የዚገም ዘጠኝ ልጆች ስሞች እንደሆኑ በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡ በወንዴ ተስፋ የተተረከው ተረክ 37 የሚሳየው ይሄን ነው፡፡ ወንዴ ተስፋ ድሂ ቀበሌ ገበሬ ማህበር የሚኖሩ ሲሆን የ60

ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የሚቀርበው ተረክ የተተረከው በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ሲሆን በትረካው ወቅት እሳቸውን ጨምሮ እኔ ረዳቴ ባይሞት እና አንድ የእሳቸው ዘመድ ነበርን፡፡

> ከሠባቱ አገዎች አንዱ ዚገም ነው፡፡ አዱግ እናትም ይላሉ ሞግዚትም ይላሉ፡፡ እንጅባራ ላይ ነው የተቀበረች፡፡ ዚገም ሰሜን ዚገም አካበቢ መኾን እንደሚባል ነው፡፡ ዚገም ዘጠኝ ልጆች አሉት መንግሀ፣ጠንግሀ፣ጫራጃ፣ጎሀናዥ አዋሻ እና ጊሣ የቀሩት አፌ ላይ ነበሩ ጠፋብኝ የሠው ስም አሁን የቦታ ስም ናቸው እነዚ በጠቅላላ፡፡ መተከል እንዳለ የአዊ ታሪክ ነው፡፡
>
> (ወንጼ፣ የካቲት 15፣ 2004 ዓ.ም)

ወንጼ በትረካቸው የረሷቸውን ሁለት የዚገም ልጆች ጨምረው ሃብተማርያም ‹‹ዚገም ዘጠኝ ልጆች አሉት አዋሻ፣ ጎሃናጅ፣ ጉንጋ፣ ጊሳ፣ ዛልና፣ ናና፣ ጠንግሃ፣ ጫራጃ፣ መንገሃ እነዚህ እንግዲህ ዘጠኙ የዚገም ልጆች ናቸው፡፡ ዘጠኙ ቀበሌዎች ናቸው አሁን፡፡ መተከል ወደጉምዝና ሽናሻ ሄደ እንጂ የአንድ ቀበሌ የአንድ ጎጥ ስም ነበር፡፡›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከነዚህ ተረኮችም እደምንረዳው የብሄረሰቡ አባላት ጀግኖቻውን ለማስታወስ እና ከትውልድ ትውልድ ታሪካቸው ይተላለፍ ዘንድ ስማቸውን በቦታ ሰይመው እደሚያቆዩ ነው፡፡

## 1.3 ሌሎች ብሄረሰቦች የሚያሳድርባቸውን ጫና ለመቋቋም የሚተርኳቸው ተረኮች

የአዊ ብሄረሰብ ከአማራ፣ ከጉሙዝ፣ እና ከሽናሻ እንዲሁም ከኦሮሞ ብሄረሰቦች ጋር ተቀላቅሎ እንደሚኖር በምእራፍ ሶስት ውስጥ ተገልጿል፡፡ እነዚህ ብሄረሰቦች ስለ አዊ ብሄረሰብ የሚናገሯቸው እና በአዊ ብሄረሰብ አባላት ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው አባባሎች አሉ፡፡ እነዚህም ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ ስምቱን አኑሮ አንዱን አጫወተኝ›› ‹‹አገው ጆሮ ቆራጭ›› እና ‹‹አገው ሲሰለጥን በጨረቃ ጥላ ይዞ ይሔዳል›› የሚሉ ናቸው፡፡ የእነዚህን አባባሎች ስህተትነት ለማሳየት የዚገም ወረዳ የአዊ ብሄረሰብ አባላት የሚተርኳቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች አሏቸው፡፡



በቡድን ውይይት ወቅት (የካቲት 29፣2004 ዓ.ም)

### 3.1 ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ...››

የተለያዩ ብሄረሰብ አባላት ስለአዊ ከሚናገሯቸው አባባሎች መካከል ይህ አንዱ ነው። ይህም አባባል በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ተቀባይነት የሌለው እና የብሄረሰቡን አባላት የሚያስከፋ ነው። የአባባሉን ስህተትነት በተረኮቻቸው እንዲህ ይገልጹታል።

‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ ስምንቱን አኑሮ አንዱን አጫወተኝ›› የሚለው አባባልን በተመለከተ የተተረኩ ሶስት የተለያዩ ተረኮችን እንመልከት።

1. ዘጠኝ ወንድማማቾች አገዎች ከአንድ አማራ ጋር ተጣልተው ስምንቱ ከዛፍ ላይ ወጠው ሾላ ይሁን ምን ይሁን ይበላሉ። የተጣላው ብቻ ቁሞ እያለ ‹‹አንተ ወንድሞችህሳ?›› ቢለው ‹‹ሁሉም ሙተው እኔ ብቻ ቀረሁ›› ይላል። ከዚያ ሾላ ነው ምንድን ነው መሬት ላይ ዱብ ስትል ቀና ብሎ በያይ ስምንቱም ከላይ ናቸው። ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ ስምንቱን አኑሮ አንዱን አጫወተኝ›› ስምንቱ ከላይ አንደኛው ከታች ማለቱ ነው።
(አያልነሽ፣ የካቲት 13፣ 2004 ዓ.ም)

ይህን ተረክ የተረከችው አያልነሽ በቀለ ናት። እድሜዋ 37 ሲሆን ትረካውን የተረከችው አይዋህ የገጠር መንደር በአባቷ ቤት ውስጥ ነው። በትረካው ወቅት እሷን ጨምሮ አባቷ በቀለ ጊዮን፣ እኔ እና ወንድሟ ያረጋል በቀለ ተገኝተናል።

2. አገው አሁንም ልቡ ዘጠኝ ነው! ጀግና ነው ልቡን አልሰጠም፡፡ እንዲህ የተባለ እንግዲህ በድሮ ግዜ አላምን ብሎ ነው አሉ፡፡ እና ጦርነት ላይ ጦር ገጥሞ እርቅ ያርግ ሲባል አገው የውነት እርቅ ነው ብሎ አላምን ብሎ ግማሹን ጦር ሸሽጎ እውነት እርቅ መሆኑን ሲያይ አወጣ ነው ሚባል፡፡ ሌላ ምናለ እና ሁልንም ጦር አውጥቶ ከማለቅ … ዋ ሞኝ ነሽ?
(ሃብተማርያም፣ የካቲት 11፣ 2004 ዓ.ም)

ይህን ትረካ የተረኩት መልአከህይወት ሃብተማርያም ሲሆኑ በትረካ ወቅት እሳቸውን ጨምሮ እኔ ባይሞት እና ሴት ልጃቸው ተገኝተናል፡፡ ተረኩ በቤታቸው በረንዳ የተረከ ነው፡፡

3. አገውና አማራ በድንበር ተጣልተው ነው እርቅ ይባልና ለድርድር ቀርበዋል፡፡ አገው ስምንት ወንድሞቹን ጫቃ ውስጥ ደብቆ አርጎ ብቻውን እሱ ይወጣል፡፡ ኋላ እርቁ የውነት መሆኑን ሲያረጋግጥ ጫቃ ውስጥ የተደበቁትን ይጠራል በዚ ግዜ አማራ "አገው ልቡ ዘጠኝ ስምንቱን አኑሮ ባንዱ አጫወተኝ" አለ፡፡ እንግዲ ይሄ ለብልሃት ነው እርቁ የውነት ካልሆነ ከወንድሞቹ ጋር ሁኖ ሊገጥም ነው፡፡
(ቆለጭ፣ የካቲት 10፣ 2004 ዓ.ም)

ይህን ትረካ የተረኩት ቆለጭ አየል ናቸው፡፡ እድሜያቸው 64 ሲሆን የመኖሪያ ቤታቸው ቅላጅ ከተማ ነው፡፡ የባህል ህክምና ባለሙያ ናቸው፡፡ ተረኩ የተተረከበት ስፍራ ከመኖሪያ ቤታቸው ፊት ለፊት የከብቶችና በጎች ማደሪያ ቤት ጎን የሚገኝ አግዳሚ ወንበር ላይ ነው፡፡ በትረካው ወቅት እሳቸው፣ እኔ እና ባይሞት እንዲሁም ህጻን ልጃቸው ነበርን፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተረኮች ሌሎች ብሄረሰቦች ስለ አዊ ብሄረሰብ የሚናገሯቸው አባባሎቹ ብሄረሰቡ ላይ ከሚፈጥሩት መጥፎ ተፅዕኖ ለማምለጥ የነዚህ ተረኮች ፋይዳ የጎላ ነው፡፡ አባባሎቹም መጥፎ ተጽእኖ እንዳላቸው የተረዳሁት ተራኪዎቹ ከሚሰጡት ምላሽ ነው፡፡ በምላሻቸው አገው ላደረገው ምክንያታዊ እርምጃ በስህተት መወቀሱን ከመግለጽ በተጨማሪ የሁለተኛው ተረክ ተራኪ ‹‹አገው አሁንም ልቡ ዘጠኝ ነው!" ሲል "አበጀ ደግ አረገ" የሚል በሚመስል እልህ እና ቁጣ በተቀላቀለበት ድምጸት ነበር፡፡ ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ …›› የብሄረሰቡን አባላት የሚያጥላላና ክብራቸውን ዝቅ የሚያደርግ ነው፡፡ ነገር ግን የዚህን ኣባባል አመጣጥ በተረክ በመግለጽ የአገውን ብልሃተኝነት ሌላው ማህበረሰብ በተለየ መንገድ እንደተረዳው በማሳየት የአባባሉን ስህተትነት የሚገልጹ ተረኮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ሌላው ማህበረሰብ የሚፈጥሩበትን ተጽእኖ በማስቀልበስ ስነ ልቦናዊ እፎይታን በተረኮቻቸው ያገኛሉ፡፡

4.3.2 "አገው ጆሮ በላ"

ሌሎች ብሄረሰቦች በአዊዎች ዙሪያ ከሚናገሯቸው እና በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ቅሬታ ከሚያስከትሉት አባባሎች አንዱ ‹‹አገው ጆሮ በላ›› የሚለው አባባል ነው፡፡

"አገው ጆሮ በላ" የሚለው አባባል ከየት እንደመጣ የማህበረሰቡ አባላት በተረኮቻቸው ይገልፃሉ፡፡ ይህ አባባል የተሳሳተ እንደሆነም በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡

> 1ኛ. በድሮ ጊዜ ነው አሉ የጭቃ ሹም ነው ምንድነው ሚባል ግብር ሲያስከፍል ሂዶ ነው፡፡ ለአማራው ሹመኛ ግብር አንከፍልም ብለው እምቢ ብለዋል የግምጃ ቤት አገው ተሹሞ ይሔዳል፡፡ ሲሄድ ስንቅ የሚሆን ቋንጣ ከኪሱ ይዞ ነበር፡፡ ከዚያ ህዝቡን ይሰበሰብና "እናንተ ለምንድ ነው ግብር ማትከፍሉ?" ቢላቸው "አልሰማንም" ሲሉ "ይሔ ጆሮ ለምንድነው ሚጠቅም?" ብሎ ሽክ ሽክ አርጎ ጣለ ጆሮአቸውን፡፡ ከኪሱ አውጥቶ ቋንጣ የበላውን ‹‹አገው ጆሮ በላ" አሉ፡፡
>
> (አያልነሽ፣ የካቲት 13፣ 2004 ዓ.ም)

> 2ኛ. እሱማ ቋሪት ላይ ደርግ ላይ እኮ ነው፡፡ ደርግ ሲነሳ አልገዛም ሲል በተለይ በክርስትና የተነሳ ነው፡፡ ደርግ ክርስቲያን አይደለም አንገዛም ብለው ነው፡፡ እንዳሉት ጆሮ ቆርጧል ነው ሚባል፡፡ አንገዛም ሲል ጊዜ ጆሮ ቆርጦ ቆርጦ ጣለ አገው፡፡ ግን ጆሮ በላ የሚሉትን እውነት አትበይ ይሄ ሌላ አገር የመንግስት ጦርነት ላይ ተደረገ የሚባለውን ነው አገውን ጆሮ የበላ የሚሉት
>
> (ሃብተማርያም፣ የካቲት 11፣ 2004 ዓ.ም)

ከሁለቱም ተረኮች እንደምንረዳው አገው፡ ህዝቡ ግብር አልከፍልም በማለቱ የወሰደው አስገዳጅ እርምጃ ጆሮ መቁረጥ ነበር፡፡ ነገር ግን የሁለቱም ተረኮች ተራኪዎች እንደሚገልጹት አገው የሰው ጆሮ አልበላም፡፡ ስለዚህ አባባሉ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም ተረኮቹ ሌሎች ማህበረሰቦች የሚጠቀሟቸውን እና አገውን በተመለከተ የሚነገሩ ‹‹ስህተት›› አባባሎች ለማረም እና እነዚህ አባባሎች ከሚያደርሱት ስነ ልቦናዊ ጫና ለማምለጥ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቀዳሚዎቹ ትንተናዎች ላይ የተገለጹት የአገው ሃያልነትና ጥንታዊነትን የሚያሳዩ ተረኮች ለእዚህ አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡



አባ ይታይህ አለሙ በትረካ ላይ (የካቲት 16፣2004 ዓ.ም)

### 4.3.4 "አገው ሲሰለጥን በጨረቃ ጥላ ይዞ ይሄዳል"

ሌላው የወረዳዋን የአዊ ብሄረሰብ አባላት የሚያስከፋው አባባል ይህ ነው። ለዚህ አባባልም ምላሽ ሲሰጡ የአገው ጥላ ከሰሌንና ከሳጠራ የተሰራ በመሆኑ ሊታጠፍ አይችልም። ይህ በመሆኑ ቀን የተዘረጋ ጥላ ፀሀይ ከተጠለቀች በኋላም ስለ ማይታጠፍ የተጠቀሙት አባባል ነው።

> በድሮ ጊዜ ነው። አገው ሙሽራ ሊያመጣ ወደ ሩቅ አገር ጥዋት የጀመረ ጥላውን ዘርግቶ ሲሄድ ሲሄድ የአገው ጥላ ስለማይታጠፍ ቀን የተዘረጋው እስከ ማታ ድረስ ሳይታጠፍ ዝም ብሎ ይጓዛል ይሄንን ያየ መንገደኛ "አገው ሲሰለጥን በጨረቃ ጥላ ይዞ ይሄዳል" አለ አሉ።
>
> (አደመ፣ የካቲት 19፣ 2004 ዓ.ም)

ተራኪው እንደሚገልጸው ‹‹ይሄ የአገውን ጥበብ ለማጣጣል የተባለ ነው እንጂ አገው ቀድሞም የሰለጠነ ነው።›› በመሆኑም የብሄረሰቡ አባላት ከተረኩ ይልቅ የተተረከለት የአዊ ብሄረሰብ ጥላ የጥበበኝነቱ መገለጫ እንጂ መሰደቢያ ሊሆን እንደማይገባ ለማመልከት የቀረበ ተረክ ነው። የአገው ጥላን በተመለከተ ቆለጭ (የካቲት፣ 11፣ 2004 ዓ.ም) በተረካቸው፡- ሰባቱ ወንድማማች አገዎች ሲመጡ ቡር ወይም ኮርች የተባለ ከልጥ የተሰራ ጫማ ለብሰው እናታቸው አዱግ ደግሞ ይቺን የአገው ጥላ

ይዘው ነው የመጡ፡፡ በማለት ከአዊ ጥንተ አመጣጥ ጋር የተቆራኘች ጥንታዊ ጥላ እንደሆነች ያስረዳሉ፡፡

‹‹የአገው ጥላ›› የአዊ ብሄረሰብ አባላት ካበረከቷቸው የእደ ጥበብ ውጤቶች መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ የጥላ አይነት ከሳጠራ የተሰራ ሲሆን መታጠፍና መዘርጋት የሚችል ጥላ አይደለም፡፡ ነገር ግን እንደ አሁኑ በቴክኖሎጂ እድገት ምክንያት የተለያዩ ዘመናዊ እና በቀላሉ መታጠፍና መዘርጋት የሚችሉ ጥላዎች ሳይመጡ በፊት አገዎች ይህንን ጥላ በእጃቸው በመስራት እራሳቸውን ከጸሃይ ይከላከሉ ነበር፡፡

ስለዚህ ራሷ ጥላዋን "የአገው ጥላ" ብለው ነው ትረካቸው ውስጥ የሚገልጿት፡፡ ይህቺ ጥላ የሌላው ማህበረሰብ አይደለችም፡፡ የተለየች የአገው ብቻ ጥላ ናት፡፡ በመሆኑም በተረኮቻቸው እንደተገለጸው የአገው ጥላ የጥበበኝነቱ መገለጫ እንጂ መሰደቢያ ሲሆን አይገባም የሚል ምላሽን ይሰጣሉ፡፡

ከንጉስ ሰለሞን ጋር በተያያዘ እና ከሰባቱ ወንድማማች አገዎች ከላስታ መምጣት ጋር በተያያዘ የተተረኩ ተረኮችም ሌሎች ማህበረሰቦች ከሚያደርሱባቸው ተጽእኖዎች ለማምለጥ ለሚተርኳቸው ተረኮች አጋዥ ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያዎቹ ተረኮች የብሄረሰቡን ዘር ሃያልነትና ጥበበኝነት ያሳያሉና፡፡

በአጠቃላይ የዚገም ወረዳ የአዊ ብሄረሰብ ከተለያዩ ብሄረሰቦች ጋር አብሮ እንደሚኖሩ እርስ በእርስ ግንኙነቱ ወቅት አንዱ ብሄረሰብ ስለ ሌላው ብሄረሰብ ሊሰማው የሚችለው ነገር ይኖራል፡፡ ይህ ስሜት ደግሞ በተለያየ መልክ ይገለፃል፡፡ ከእነዚህ ነገሮች መካከል አንዱ ስነ ቃሉ ነው፡፡ በስነ ቃሉ ውስጥ ቃላዊ ዝርው ተረኩ ይገኛል፡፡ በንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ክፍሉ ውስጥ የተለያዩ ምሁራን እደገለጹትም ቃላዊ ዝርው ተረክ የሰው ልጅ ልምዱን እና የተለያዩ ክስተቶችን፣ ስሜቱን፣ ሀሳቡን ወ.ዘ.ተ ሊገልጽ ይችላል፡፡ በአዊ ብሄረሰብ ውስጥም ይህ ነው የሚሆነው አዊዎች ራሳቸውን በቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው ከመግለጽ በተጨማሪ ሌሎች ብሄረሰቦች ስለ አዊ ብሄረሰብ የሚሰማቸውን እና በስነ ቃሎቻቸው የሚገልጿቸውን አባባሎች እነሱም በቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው ምላሽና ማፍረሻ ይሰጡባቸዋል፡፡

ቀጥሎ ደግሞ በታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ የሆኑትን ግለሰቦች እያነሱ የአዊ ብሄረሰብ አባላት ከእነሱ ጋር ያላቸውን ዝምድና እንዴት እንደሚገልጹት እንመልከት፡፡

### 3.4 አገውና ታዋቂ ነገስታት

የብሄረሰቡ አባላት ከንጉስ ሰለሞንና ከንግስት ሳባ ሌላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ከሚሰጣቸው አጼ ቴዎድሮስ እና አጼ ላሊበላ ጋር ያላቸውን የዘር ግንኙነት በተረኮቻቸው ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የብሄረሰቡንና የሁለቱን ነገስታት ግኙነት በተመለከተ የተተረኩ ተረኮች ትንታኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

#### 3.4.1 አገው እና አፄ ላሊበላ

ንጉስ ላሊበላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ከሚሰጣቸው የዛጉዌ ስርወ መንግስት ነገስታት መካከል አንዱ ነው፡፡ እንደ Sergaw (1978፡21) ላሊበላ ኢትዮጵያን ለአርባ አመታት የገዛ እና የተለያዩ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን በተለያየ አይነትና ቅርጽ ያሰራ ንጉስ ነው፡፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያም (1957፡196) ከአፄ ላሊበላ የገድል መፅሀፍ ያገኘሁት ነው በማለት እንደገለጹት አፄ ላሊበላ በዘመኑ የጽድቅና የመንፈስ ስራ መስራት የዘወትር ልማዱ ነበር፡፡

የዚገም ወረዳ የአዊ ማህበረሰብ አባላትም ንጉስ ላሊበላን የአገው ዘር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ ከተረኳቸው ተረኮቸ መካከል አደመ ተስፉ የተረኩትን የሚከተለውን ተረክ እንመልከት፡፡

> አፄ ላሊበላ ኮ አገው ነው፡፡ የላስታ አገው ነው፡፡ ግን ቅኔ የተማረ እዚህ ጎጃም ማርቆስ ነው፡፡ በጣም ቅኔ አዋቂ በጣም ስለነበረ ሁለት ተማሪዎች ይቀኑበት እና ለመምሩ ምግብ ሲሰራ ሳለ የሞተ የህፃን ልጅ እጅ ቆርጠው ወጡ ውስጥ ከተው ቡዳ ነው አስባሉ ከዚያ በኋላ ተመልሶ ላስታ ገባ.....
>
> (አደመ፣ የካቲት 18፣ 2004 ዓ.ም)

የወረዳዋ የአዊ ብሄረሰብ አባላት ማነታቸውን በአብዛኛው የሚገልጹት ከብሄራቸው ጋር በተገናኘ ነው፡፡ በዚህ ተረክም የአዊ ብሄረሰብ አባላት ከላሊበላ ጋር ያላቸውን የዘር ግንኙነት ገልጸዋል፡፡ ይህም የአዊ ብሄረሰብ ከነገስታት ዘር የሆነ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ ሌሎች ማህበረሰቦች የሚያደርሱባቸው ተጽእኖችን ማስቀልበሻ አንዱ መሳሪያ ነው፡፡

## 4.4.2 አገው እና አፄ ቴዎድሮስ

አፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ከሚሰጣቸው ነገስታት መካከል አንዱ ነው። ኢትዮጵያን ከ1855-1868 ገዝቷል። የዘመነ መሳፍንትን ፍፃሜ እውን እንዲሆን ያደረገ እና ኢትዮጵያ አንድ ማዕከላዊ መንግስት ይኖራት ዘንድ ጥረት የጀመረ ቀዳሚው ንጉስ ነበር።

የአዊ ብሄረሰብ አባላትም የዚህ ንጉስ ዘር አገው ስለመሆኑ በተረካቸው እንዲህ ይገልጻሉ።

> አፄ ቴዎድሮስ የቋራ አገው ነው። ‹‹አዋ ቁሪኚ›› ሚለው ላይ ነው አገሩን ቋራ ያሉት። ‹‹አዋ ቁሪኚ›› ማለት ፀሀይ ብቅ አለች ማለት ነው በአገውኛ። ዛሬ እሱን ማንም መጠቀሚያ አርጎታል ጎንደርም፣ ወሎም፣ ትግሬም የኛ ነው ይላሉ እንጂ አፄ ቴዎድሮስ ማ አገው ነው። በድሮ ጊዜ ነገስታት ጎንደር ነበር ሚነግሱ (አዳሙ፣ የካቲት 18፣ 2004 ዓ.ም)

ከዚህ ጋር በተያያዘ “አዊ” ማለት “ፀሀይ” ማለት ነው። ብለው ቆለጭ የተባሉ ተራኪ ነግረውኛል። አፄ ቴዎድሮስ አገው እንደሆነ የገለፁት አፄ ቴዎድሮስ ከተወለደበት ስፍራ ስያሜ የአገውኛ ቃል መሆኑን በማያያዝ ነው።

እነዚህ አፄ ላሊበላን እና አፄ ቴዎድሮስን በተመለከተ የተነገሩት ተረኮች የአገው ዝርያ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ላይ የተወሰኑ ናቸው። ነገር ግን የአፄ ላሊበላ ሀይማኖተኝነት እና ጥበበኝነት እንዲሁም የአፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት ከሌላውና በታሪክ ተጠቃሽ ካልሆነው ህዝብ በተለየ መልኩ ተነስቶ የአገው ዘርነታቸው እንዲነገር አድርጓል። በእርግጥ አፄ ላሊበላ ከላስታ ነገስታት መካከል አንዱ መሆኑ አገው ከላስታ ጋር ትስስር እንዳለው በቀዳሚዎቹ ተረኮች ውስጥ መጠቀሱ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ ግን በሃይማኖት እና በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጣቸው ንጉስ ሰለሞን፣ ንግስተ ሳባ፣ አፄ ላሊበላ እና አፄ ቴዎድሮስ የአገው ዘር ጋር ተያይዘው በተረኮች ውስጥ መጠቀሳቸው የዘሩም ኃያልነት ያሳያሉ።

## 4.5 ቋንቋ

የአዊ ብሄረሰብ አባላት አዊኛ (አገውኛ) የቋንቋቸው መጠሪያ እና መግባቢያዎች ከመሆኑ በተጨማሪ ከሌላው ማህበረሰብ ተለይተው የሚታወቁበት መገለጫዎች ነው ማለት እንችላለን። አገውኛን ቋንቋ በተመለከተ መልአከህወት ሃብተማርያም በተረካቸው ‹‹አገውኛን ሎሎ የሚባል

ሰይጣን የፈጠረው ቋንቋ ነው። እግዚሃር አልፈጠረውም በሚል። የአባ ተክለሃይማኖት ስብከት ያገው መንግስት ለቅጣት የመጣ ነው በማስባል ጣሉት እንጂ አገው ለሰላሳ ሶስት አመት እዚያው ላስታ ላይ ነግሧል››። በማለት ይገልጻሉ በዚህ ተረክም አገውኛ በታሪክ አጋጣሚ እየከሰመ እንደመጣ ነገር ግን ቋንቋው ጥንታዊነት እንደነበረው እንረዳለን። ከዚህ በተጨማሪ የቋንቋ ጥንታዊነትና ቀደምትነትን የሚገልጹ ተረኮችም ተገኝተዋል። ይህንን አስመልክቶ መምህር መንክር የሚከተለውን ተረክ ተርከዋል።

መምህር መንክር እድሜያቸው 36 ሲሆን በቅላጅ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የትርጓሜ መምህር ናቸው። በትረካው ወቅት እኔ መምህሩ እና ባይሞት ተገኝተናል። ትረካው ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ የተካሄደ ነው።

> አለም ከተፈጠረ በኋላ ቋንቋ አንድ ነበረ ነገር ግን ከምድር ሰባት አፍ ከሰማይ ሰባት አፍ በሚደነግገ ሰናኦድ በሚባል ሜዳ ትልቅ ግንብ በሰናኦድ ገነቡ በፀሀይ ምግብ አብስለው እስከመብላት ደርሰው ነበር አሁን ሰይጣን ሲፈትናቸው ሲፈልግ ጦር ወደ ሰማይ ወርውሩ ይልና “አሁን አብን ወጋችሁ”፣ አሁን ወልድን ወጋችሁ” “አሁን ደሞ መንፈስ ቅዱስን ወጋችሁ እያለ ጦሩን ደም ቀብቶ ወደ እነሱ ሲልክ እግዚአብሔር ተቆጣና በመካከላቸው እንዳይግባቡ ቋንቋን ሰባ ሁለት አርጎ ለያየባቸው።... የለያየው የግዚአብሄር ቃል እንዲስፋፋ ነው ከሰባሁለቱ አንዱ አገውኛ እንደሆነ ነው እንግዲህ... (መንክር፣ የካቲት 19፣ 2004 ዓ.ም)

ይህ ተረክ አገውኛ ቋንቋ ጥንታዊ እና ቀዳሚ ቋንቋ እንደሆነ ይገልጻል። ይህ ማለት ቋንቋው ቋንቋዎች ከተፈጠሩበት ዘመን አንስቶ እስከ አሁን የቆየ ቀዳሚ ቋንቋ ነው። ስለዚህ ተረኩ የቋንቋን ቀዳሚነት እና ጥንታዊነት የማሳየት ፋይዳ አለው።

እስካሁን ከተተነተኑት ተረኮች እንደምንረዳው የዚገም ወረዳ የአዊ ብሄረሰብ አባላት ማንነታቸውን ከብሔራቸው ጋር በተያያዘ መልኩ ነው የገለፁት። ይህም በወረዳዋ ውስጥ የሚኖሩ ብሄረሰቦች ከጠቅላላው የአዊ ብሔረሰብ የዘር ሀረግ፣ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ እና ሌሎች ማህበረሰቦች ስለ አዊ ለሚናገራቸው አባባሎች ምላሽ፣ በታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ የሆኑ ነገስታት ዘር ከአዊ ብሔረሰብ ዘር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልፁ ተረኮች ናቸው።

Dundes (1993:10) እንደሚያስረዳው የብሔረሰብ ማንነት (ethnic identity) አንዱ የጋራ ማንነት አይነት ነው በማለት እንዲህ ይገልፃሉ "…. It is one type of identity, that is one type of group identity". የወረዳዋ የብሄረሰቡ አባላትን የሚተርኳቸው ሁሉም የማንነት ተረኮች ከጠቅላላው የአዊ ብሄር ጋር የተያያዙ ናቸው። እነዚህ ተረኮች የብሄራቸውን ጥንተ አመጣጥ፣ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ እና ከታዋቂ ነገስታ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከመግለጽ በተጨማሪ ሌሎች ብሄረሰቦች የሚያሳድሩባቸውን ስነ ልቦናዊ ጫና ለመቋቋም ይጠቀሙባቸዋል።

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው በቃላዊ ዝርው ተረክ ማንነትን መግለፅ ይቻላል። በትንታኔው የተረጋገጠውም ይህ ነው። ከዚህ ውጪ ግን የብሄረሰቡ አባላት ራሳቸውን ወይንም ብሔራቸውን በተለያየ መልኩ የመግለጽ ነገራቸው ከፍተኛ ነው። ተረኮቻቸው የሚያተኩሩት ራሳቸውን መግለጽ ላይ እንጂ ከሌሎች ማህበረሰቦች አንፃር የመግለጹ ነገር በግልጽ የሚታይ አይደለም። በእርግጥ "እኛ እንዲህ ነን" ሲሉ በተዘዋዋሪ መንገድ ‹‹ሌላው ደግሞ እንዲያ ነው›› ማለታቸው ሊሆን ይችላል። በቀጥታ ግን አንድ ማህበረሰብን መርጠው ከእዚያ ማህበረሰብ አንፃር ተረኮቻቸውን ሲተርኩ አይታይም። በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት የማንነት ተረኮቹ የተለያዩ ፋይዳዎች ተረኮቹ እንዲፈጠሩ፣እንዲተረኩ እና ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ የሚያደርጉ ናቸው።

# 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የዚገም ወረዳ የአዊ ብሄረሰብ አባላትን የማንነት ተረኮች ፋይዳ ማጥናትን ዋና አላማው አድርጎ በመነሳት ተካሔዷል፡፡ በዚህ ዋና አላማ ስርም ተራኪዎቹ ለሚተርኳቸው ተረኮች ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ማሳየት፣ ተረኮቹ የሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ መግለጽ እንዲሁም ለተረኮቹ መፈጠር፣ መተረክና እስካሁን መቆየት ምክንያቶቹ ምን እንደሆኑ መመርመር የሚሉ ንዑሳን አላማዎች ተካተዋል፡፡ እነዚህ አላማዎችን መሰረት በማድረግ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ የተሰኘውን የፎክሎር መረጃዎች የመተንተኛ ዘዴ በመጠቀም የተረኮች ትንታኔ ተካሔዷል፡፡ የትንታኔው መሰረቶችም የተረኮቹ ይዘቶች፣ የተተረኩባቸው አውዶች እና አጥኚዋ በመስክ ቆይታዋ ወቅት የተረዳቻቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላም የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ጥናቱ ሊደርስ ችሏል፡፡

የማንነት ተረኮቹ የብሄረሰቡ አባላት ስለ ራሳቸው የሚተርኳቸው ተረኮች ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮችም የብሄረሰቡን ጥንተ አመጣጥ እና የዘር ሀረግ ቋንቋ እንዲሁም አሰፋፈር የመግለጽ ፋይዳ ነበራቸው፡፡ እንዲሁም ሌሎች ብሄረሰቦች የሚያደርሱባቸውን ስነ ልቦናዊ ጫና ለመቋቋም ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ታዋቂ የታሪክ ሰዎች ጋር ያላቸውን የዘር ግንኙነት ለመጥቀስ ግልጋሎት ላይ እንደሚውሉም ተረጋግጧል፡፡ የብሄረሰቡ አባላት በአብዛኛው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በመሆናቸው አብዛኞዎቹ የማንነት ተረኮቻቸው ውስጥ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ቁም ነገሮች ያቀርባሉ፡፡

የብሄረሰቡ ጥንተ አመጣጥ እና የዘር ግንድ ከእስራኤሉ ንጉስ ሰለሞን ጋር የተያያዘ ዘር እንዳላቸው ይህም የዛጉዬ ስርወ መንግስትን እንዲመሰርቱ እንደረዳቸው እና ዘራቸውን ከፈጣሪ ለንግስና ከተመረጠ የዘር ማንነት እንዳላቸው በቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው አማካይነት እንዲያሳውቁ እንደረዳቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

አሰፋፈራቸውን በተመለከተ ደግሞ ወደ አዊ ዞን የመጡት ለአደንና ለግዳይ ቢሆንም ወደ ዚገም ወረዳ የአዊ ማህበረሰብ የሰፈረው በእግዚአብሔር (በፈጣሪ) እየተመሩ በመምጣት ሌሎች ማህበረሰብ አባላትን በማሸነፍ የሰፈሩ መሆኑንና ይህ የፈጣሪ እገዛ ወራሪ እንዳልሆኑ የሚያሳይ ስለሆነ ሌሎች ያስለቀቋቸው ማህበረሰቦች ተቃውሞ እንዳያስነሱባቸው ሊከላከልላቸው እንደሚችል በጥናቱ ታይቷል፡፡ ይህ ማለት የአሰፋፈራቸው ሁኔታ ጀግንነት እና የፈጣ እገዛ የተቀቀለበት እደሆነ ተረኮቻቸው በመገለጫነት እረድቷቸዋል፡፡

ሌሎች ብሄረሰቦች የሚያሳድሩባቸውን ስነ ልቦናዊ ጫና ለመቋቋምም የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው እንደሚጠቅሟቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ይህም የወረዳዋ የአዊ ማህበረሰብ ከአማራ፣ ከጉምዝ፣ ኦሮሞ እና ከሽናሻ ብሄረሰቦች ጋር ይኖራል፡፡ በዚህም ምክንያት ሌሎች ብሄረሰቦች ስለ አዊ ብሄረሰብ የሚሏቸው አንዳንድ አባባሎች የማህበረሰቡን ክብር የሚቀንሱ ናቸው፡፡ ለእነዚህ አባባሎች ማፍረሻነት የማህበረሰቡ አባላት የሚጠቀሟቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከስነ ልቦናዊ ጫናው እንዲያመልጡ ይረዷቸዋል፡፡ ተረኮቹ በአብዛኛው የብሄረሰቡ ታላቅነትና ጥበበኛነት ላይ ያተኩራሉ፡፡ ይህም የብሄረሰቡ ደረጃ ከሌላው ማበረሰብ አንጻር ሲታይ ምን እንደሚመስል ያሳያል፡፡

ታዋቂ የታሪክ ሰዎች ማለትም አፄ ላሊበላ እና አፄ ቴዎድሮስ የአገው ዘር እንደሆኑ በማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው ይገልፃሉ፡፡ ይህም በተዘዋዋሪ መንገድ የማህበረሰቡን አባላት ጀግንነት እና ጥበበኘነት ለማሳየት እንደሚችል ጥናቱ ገምቷል፡፡ ስለዚህ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ይዘት የብሄረሰቡ አባላት በማንነታቸው እንዲኮሩ የሚያደርጉ በመሆናቸው ቀጣዩ ትውልድ በማንነቱ እንዳያፍር የሚያደርጉ ናቸው፡፡

የወረዳዋ የብሄረሰቡ አባላት በተረኮቻቸው አማካይነት ስለማንነታቸው የሚሰማቸውን ነገር ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ የማንነታቸው መፍጠሪያ፣ ማሳያ እና ከትውልድ ትውልድ ማስተላለፊያ መሳሪያዎቻቸው ናቸው፡፡

ብሄረሰቡም እነዚህን የማንነት ተረኮች እንደ ብሄራቸው እውነተኛ ታሪክ የሚቀበሏቸው እና ስለማንነታቸው ሲጠየቁ የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች ናቸው።

እነዚህ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች በአዊ ብሄረሰብ ውስጥ የሚሰጧቸው ፋይዳዎች መኖራቸው ብሄረሰቡ በጋራ እንዲጠቀምባቸው ወይንም እስካሁን ድረስ እንዲተርካቸው ምክንያት ሆነውታል። ስለዚህ ለማንነት ተረኮቹ መፈጠር፣ መከወንና መቀጠል ምክንያቶቹ ብሄረሰቡ እንደታሪኩ ስለሚቆጥራቸው እና ስለሚያምናቸው ሲሆን ሲያምናቸው ደግሞ ይከውናቸዋል። ስለከወናቸው እስካሁን ሊዘልቁ ችለዋል።

በአጠቃላይ የማንነት ተረኮቹ ከላይ የተዘረዘሩት ፋይዳዎች ስላሏቸው ማህበረሰቡ ሊፈጥራቸው ሊከውናቸው እና እስካሁን ሊያቆያቸው መቻሉ ጥናቱ የደረሰበት ተጨማሪ ድምዳሜ ነው።

## ዋቢ ጽሁፎች

### ሀ. የአማርኛ ምንጮች

ማን ያለው አባተ። ‹‹የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው››። በኢትዮጵያ ቋንቋ እና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1999 ዓ.ም።

ምንዳ ገብሬ። ‹‹የጌዲኦ ልማዳዊ ስርአትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው››። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ። <u>የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ኑብያ-አክሱም ዛጉዬ እስከ ዓጼ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት</u>። አዲስ አበባ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1946።

ታዬ ገብረ ማርያም። <u>የኢትዮጵያ ህዝበ ታሪክ</u>። አስመራ፣ ወንጌላውያን ማህበር ማተሚያ ቤት፣ 1956።

አማረ ሞላ። ‹‹የሸክቾ ብሄረሰብ ሃገረ ሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና፣ በኢትዮጵያ ቋንቋ እና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1999 ዓ.ም።

አያሌው ሲሳይ። <u>የአገው ህዝቦችና የዛግዌ ስርዎ መንግስት ታሪክ</u>። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1995።

ከሁሉም በላይ ‹‹የነገደ ወይጦ ቃላዊ ዝርው ተረኮች እና ባህላዊ ስርዓቶች፤ በኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2003 ዓ.ም።

ነጋ ጌጤ። <u>የቅማንት ህዝብ ታሪክ፣</u> ጎንደር ዳሸን አታሚዎች፣ 1993 ዓ.ም።

የኢትጵያ መጽሃፍ ቅዱስ ማህበር። <u>መጽሃፍ ቅዱስ</u>። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980።

## ለ. የእንግሊዝኛ ምንጮች

Aberaham, Alemu. "Jimma Oromo Oral Prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis". M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 2000.

____________. Oral Narratives as Ideological Weapon for subordinating women: The case of Jimma Oromo; Journal of African cultural studies. 2007.

Abdul Kadir, Haji Jama "Some Cultural elements Refelected in Somale Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1982.

Anna, De Finna. <u>Identity in Narrative: a Study of Immigrant Discourse.</u> Amsterdam/Philadelphia, John Benjamins publishing, 2003.

Ayenew, Mamo Seyoum, "Administrative history of Awi." M.A. thesis department of history, Addis Ababa University, 2007/8.

Bascom, William R.. The Forms of Folklore: Prose Narrative. In Segal, Robert A. (Ed.) <u>Anthropology, Folklore and Myth</u>. New York and London: University of Lancaster, Garland Publishing, 1996.

____________ "The forms of folklore: prose Narrative". Journal of American folklore, vol. 78, No 307 published by American folklore society. (Jan-Mar 1965)

Bauman, Richard, <u>Story, performance, and Event: Contextual studies of Oral Narratives.</u> Cambridge University press, New York, 1986.

____________. Four Functions of folklore. In Alen Dunduse, (Ed.), <u>The Study of Folklore.</u> prentice Hall, Inc, Englewood cliffel, N.j., 1965.

Dundes, Alen. <u>Folklore Matters</u>. USA, The University of Tennessee press, 1986.

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions". M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa University, 1999.

Ben Amos, Dan. Folklore in context. South Asian publishers, New Delhi Madras, 1982.

Degh, Linda. "Oral Folklore Oral Narratives." In Dorson, Richard M. (Ed.) Folklore and Folk life: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dorson, Richard M. (Ed.). Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago: The University of Chicago Press, 1972.

Finnegan, Ruth. Oral Tradition and the Verbal Arts: a Guide to Research Practices. New York: Thomas Publishing Company, 1992.

Gamst, F.H Charles. The Quemant: A pagan Hebraic Peasantry of Ethiopia. Illinois: wave land press, Inc, 1984.

Goldstin, Keneth. Guide for field workers in folklore. Pennsylvania: folklore associates inc, 1964.

Hetzron, Robert. The verbal system of south Agaw. Berkley University of California press, 1996.

Lewis P. Hinchman and Sandra K., Hinchman. (eds) Memory, Identity and Community. State University of New York press, 2001.

Melakneh Mengistu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales". M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Oring, Elliot. Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. Long: Utah University Press, 1986.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa University, 1996.

Sergaw Hable sillase. Ancient and Medieval Ethiopian History to 1970. Addis Ababa, United printers,1972.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions. Long: Utah State University Press, 2005.

Taddesse Tamrat, Church and State in Ethiopia (1270-1527). London, oxford University press, 1972.

__________ "Process of Ethnic Interaction and Integration is Ethiopian History: the Case at Agaw." Proceedings of the 9th International congress of Ethiopian studies, Moscow, 1988.

Tesfaye Gebre Mariyam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa University, 1990.

Uhlig, Siegbert. (ed) Encyclopedia Aethiopica A-C. Harrassowitz, Verlang Washaden, 2003.

Yihenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature: Addis Ababa U7cvniversity, 1996.

Zelalem Leyew. Wild Plants Nomenculture and Traditional Botanical Knowledge Among Three Ethnolinguistic Groups in Northwestern Ethiopia. Ethiopia, Organization for Social Science Research in Eastern and Southern Africa (OSSEREA), 2011.

## አባሪ 1፡- የተረኮች ስብስብ

### ተረክ 1፡- አገውና ንጉስ ሰለሞን

… ንጉስ ሰለሞን ነብይ ስለሆነ ‹‹ለአበሾች በርበሬና አሻቦ የበዛበት ምግብ ስጣቸውና ዘወር በል›› ይላል ንጉሱ ሰለሞን ፊት ለፊት ነው እንደዚ (በእጃቸው ወደ ፊት እየጠቆሙ) ምኝታ ማስተናገጃ የተሰጣቸው እንደዚ ሰለሞን ፊት ለፊት ይተያያሉ። ውሃጥም ሲያቃጥላቸው ውሃው ቧንቧ ያለ ከንጉስ ሰለሞን ምኝታ አካባቢ ነው ያለ። ንግስቲቱ እንቅልፍ ሲወስደው ሂጄ ሰርቄ እጠጣለሁ ብላ አስባ እያለች ንጉሱ ያንቀላፋ መስሎ ሰርቃ ስትጠጣ ያዛት። ‹‹ያንድ ሀገር ንጉስ ያንድ ሀገር ንግስት እንዴት ይይዛል›› ብትል ‹‹በኢትዮጵያ ሌባ የለም ብለሽ ነበርሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሰርቂ ተይዘሻል። ያንድ አገር ንግስት ያንድ አገር ንጉስን ንብረት እንዴት ይሰርቃል?›› አላት ከዚያ በኋላ ሲጨቃጨቁ ያው ሴት መሆን አይቀርም ተገናኛት። እና ቀዳማዊ ምኒሊክ ተረገዘ። ባንድ ለሊት። ይሔ የእግዚሃር ፈቃድ ነውና ሂዳ ወደ ምኝታዋ እንትን ስትል ደንገጡሯ ‹‹ውሃ ጠጥተሽ መጣሽ›› ስትል ‹‹አዎ›› አለች ይህን ነገር ተደረግሁ አላለችም። እሷም ጠጥታ ልትመለስ ልትጠጣ ስትል እሷንም ደገመ። ከዚያ ዛጉዬ ተረገዘ ባንድ ለሊት ነው የተረገዙ። ከዚያ ሶስት ወር ቆይታ የሰለሞንን ቤተ መንግስትና ህገ ኦሪትን ተምራ ሲመለሱ መንገዱ ስድስት ወር ነው የሚፈጅ። ሁለቱም ባንድ ቀን ምጥ ተያዙ ‹‹ውሃ አምጪ›› ‹‹ውሃ አምጪ›› ሲባባሉ ቦታውም ማይቤላ ተባለ። …

ሲያድጉ ንግስቷ የሰለሞንን ፎቶ እያሳየች ነው ያሳደገች። ምኒሊክ ስሙ ምን ሊግ ነው። ከአልጋ ወደ አልጋ ማለት ነው። በዚያው በነሱ አነጋገር። ከዚያ በኋላ አድገው አምሮ አግኝተው ሰው ሲሆኑ አባታቸው ዘንዳ ሲደርሱ ማቆያ ቤት ሁነው ሁሉ ከተዘጋጀ በኋላ አሳሳች መኳንንቶችን ዘውድ አስጭኖ እሱም ዘውድ ጭኖ ‹‹በሉ እንግዴህ አባታችሁን ለዩ›› ተባሉ። ምኒሊክ የአባቱን ፎቶ ያይ ስለነበረ ጋድ እሱን አሉ ሚመስል ቀብ አረገ አባቱን። እንደገና ዛጉዬ ወደ መሳሳቱ ይልና በኋላ ግንለየ አዛገ አለው ‹‹ቢሳሳትም ልጄ ነው›› ማለቱ ነው። ---አዎ በዚያ በነሱ ቋንቋ ነው። ከዚያ ለተወሰነ ጊዜ ትምህርተ ኦሪትና ህግን ሲማሩ ቆዩ ሁለቱ ልጆች ጋድ ሰለሞንን ነው ሚመስሉ። እና ህዝቡ ልጆችህን ስደድልን ይላል ‹‹እኔ የበኩር ልጆቼ ናቸው ከናንተስ የበኩር ልጆችን የሚሰድ ማነው›› አለ። በኩርማት የበኽር የመጀመሪያ ማለት ነው። ሀያራት የበኩር ልጆቻቸውን ሰጡ እስራኤላውያን። በኋላ የደብር አስተዳዳሪውም ምንም እስራኤላውያን ሁኖ… ሁለት ታቦት ብቻ ነበረ እስራኤል ውስጥ የነበረ

የዚያን ግዜ ሚካኤልና ጺወን፡፡ ጺወንን ይዘው ሺ እግረኛ ሺ ፈረሰኛ ሁነው ሀያራቱ እስራኤላውያን የደብር አስተዳዳሪ ሁነው... ሚስጥሩን ስለሚያውቁ እነዚ እስራኤላውያን ልብሱን የሚካኤልን አርገው የጺወንን ታቦት ይዘው ሲመጡ እስራኤላውያን እርስ በርስ ሲበጣበጡ እስኪ ታቦቱን ፍቀዱ ሲባል ጺወን የለችም ሚካኤል ነው ያለ እንዳሁን ባየር ተሯሩጠው የሚመጡት አደለም፡፡ አሁን ታቦት አለች ተብሎ አይነገርም ፈረንጆች በሀይል እንዳይወስዱ ተብሎ ነው፡፡ ... እና የሰለሞንን ህገ መንግስቱን ተምረው መጠው የለ? ንግስቲቱ ከሞተች በኋላ መጀመሪያ ምኒሊክ ነገሰ ከዚያ ዛጉዬ የአገው ስርዎ መንግስትን ይዞ ለሶስት መቶ ስንትስ አመት ገዛ፡፡

## ተረክ 2፡- አገውና ንጉስ ሰለሞን

የኢትጵያ ንግስት ሳባ በአንድ ግሪካዊ ነጋዴ አማካይነት ስለ ንጉስ ሰለሞን ከተነገራት በኋላ ንግስተ ሳባ ንጉስ ሰለሞን ትልቁን ቤተመቅደስ በሚያሰራበት ወቅት ብዙ የወርቅና የብር ስጦታ ላከችለት፡፡ ከዚያም በኋላ በዚሁ ነጋዴ አማካይነት የሁለቱ ነገስታት ቅርርብ በማደጉ ንጉስ ሰለሞን መልሶ ለንግስተ ሳባ ብዙ ሰጦታዎችን ላከ፡፡

በሂደትም ጠቢቡ ሰለሞን የኢትዮጵያ ንግስተ ሳባን ግብዣ አደረገለት እሷም ፍቃደኛ በመሆን የሚበላ፣ የሚጠጣና ብዙ ንብረት ይዛ ሞግዚቷ (ገርዷ ጋር ወደ እስራኤል ሄዱ ንጉስ ሰለሞን የሞቀ አቀባበል ካደረገላት በኋላ በአንዳንድ ጉዳዮች ተጫዋወቱ፡፡ ቀኑም በመሸ ጊዜ ንጉሱ ሰለሞን ጨውና በርበሬ የበዛበት ምግብ አበላቸው፡፡ የእራት ጊዜም ካለቀ በኋላ የምኝታ ቤቱ አሳየኝ ባለችበት ወቅት እዚሁ ሳሎን እንድትተኛ ነገራት ነገር ግን ንግስተ ሳባ ስለፈራችው ሳሎን መተኛት አልፈለገችም፡፡ በወቅቱም ንጉሱ ሰሎሞን ጋር ቃል ገቡ፡፡ ንግስተ ሳባ የንጉስ ሰለሞንን ንብረት እንዳትነካ አስምሏት ላይነካት ተማምለው ተኛች፡፡ በተኛች ወቅት ግን ነግስተ ሳባ የበላቸው ምግብ እያቃጠላት ስለነበር ውሃ መጠጣት ፈለገችና ሰራተኛዋን (ገረዷን) ንጉሱ ሰለሞን መተኛቱን አይተሽ ነይ ብላ ላከቻት ከዚያም ንጉሱ ሰለሞን በተፈጥሮው ሲተኛ አይኑን ይከፍታል፡፡ ሳይተኛ ደግሞ አይኑን ይዘጋል፡፡ ገረዷም የተኛ መስሏት ስትሄድ ንጉሱ ከገረዷ ጋር ተገናኛት፡፡ ገረዷም ይህን ምስጢር በመደበቅ ‹‹አዎ ተኝቷል›› አለቻት ከዚያም ንግስተ ሳባ ሂዳ የውሃ መጠጫውን ስትይዝ ንጉስ ሰሎሞን ያዛት ከዚያም ስምምነታቸው ስለፈረሰ እሷም ጋር ተገናኛት፡፡ በወቅቱ ሁለቱም ጸንሰው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተመለሱ፡፡

ንግስተ ሳባም በጸነሰች ጊዜ መጸነሷን ለንጉሱ ሰሎሞን ላከችበት። ሰሎሞንም መልስ ወንድ ከሆነ ወርቅ ሴት ከሆነች ብር ላኩብኝ አለ። በአጋጣሚ ሁለቱም ወንድ ወልደው ስለነበር ወርቅ ላኩለት።

በወቅቱም ልጆች አድገው ስለነበር አባታቸውን እንዲያውቁ የንግስተ ሳባ ልጅ አባት አንተን ይመስላልና ብላው በውሃ ፊቱን አሳይታው ስለነበር አባቱን ለየ። የገረዷ ልጅ ግን ምንም ስላላወቀ መለየት አልቻለም በዚያም የሳባ ልጅ ሚኒሊክ የገረዷ ልጅ ደግሞ ዘጉዬ የግል ስም ተሰጣቸው። በዚያም ሁለቱም አድገው የየራሳቸውን መንግስት መስርተው ይገዙ ነበር።

## ተረክ 3፡- አንኬሺ

አንከሻ ‹‹አንኬሺ›› ማለት እኔ እሻላለሁ ማለት ነው ባንጃ ማለት ደሞ …ነገ ዝናብ ነው ጥጋብ ነው ማለት ነው…መተከል ‹‹ማቲ ኪሲ›› ማለት ማተብ ካንተ ጋር ምንድንነው ያንገት ማተብ ካንተጋር ማለት ነው ሚቲ ባገውኛ ማተብ ማለት ነው እንግዲህ ዚገምም ወደዚ የመጣ መጨረሻ ነው። ‹‹እንዚጊ ጌም›› ሂድ ውረድ ማለት ነው። መጨረሻ ነው የወረደ።

## ተረክ 4፡- ሰባቱ ወንድማማቾች

ዋናው መነሻቸው ሰቆጣ ላይ ነው። የሰባቱም አገዎች እናት አዱግ ነው ስሟ። ሰባቱ አገዎች የሚባሉ አንከሻ፣ባንጃ ኳኩራ፣ ጫራ፣ መተከል፣ ዚገም እና ቱምሃ ናቸው። ጎሽ እና ዝሆን እናድናለን ብለው መጠው ቦታውን ስለወደዱ አገው ምድርን ተከፋፍለው መኖር ጀመሩ።

## ተረክ 5፡- ንግስተ ሳባ እና አጋቦስ

ክርስትናማ የመጣ ጥንት በኦሪት ቢሆንም ከእየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ኦሪት ሀይማኖት የገባ በንግስተ ሣባ ዘመን ነው። ኢትዮጵያ አርባ አመት ዘንዶ ነግሷል። ኢህ በታሪክ ኤመችም ብለው ትተው ነው እጂ ዘንዶማ ነግሷል። … የተወለደው ከንጉስና ከንግስት ነው። ከሡ ጋር አብራ የተወለደች ሴት ልጅ አለች። እንግዲህ ያን ግዜ ነው ኦሪት ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ የቻለ። ይሔ ዘንዶ አርባ አመት ሲገዛ ሠው እያስገበረ ነበረ የሚበላ። በቀን አንድ ሠው ነው የሚበላ የነበረ። … እና ውሃ የሚጠጣም ወንዝ ወርዶ ነው ሌላ ምግብም ሠውም ሲበላ እንደጭቃ እየተቦካ ገንዳ ላይ ነው የሚቀርብለት። አንድ ሀማሜናዊ ሳብታህ የሚበላው ‹‹እኛ ለዘንዶ እንዴት እንገዛለን ሲል ግዜ ህዝቡን ሠብስቦ ‹‹ኦሯ እኛማ ወደን አደለ ለሡ እንገዛለን እንጂ››

ቢሉ እሱን ባጠፋላችሁ ምን ትሠራላችሁ ለኔ ሲል ‹‹የሡን መንግስት እስከ ሰባት ጉልበት እንገዛለን›› አሉ። እንዲያ ሲሉ ምን አረገ ህዝቡን ሰበሰበና ወንዝ እሱ ውሃ መጠጣት ሲሄድ … ውሃ ወንዝ ወርዶ ነው ሚጠጣ። ምን አረገ በቀስተ ደመና በክብ ህንጻ ሠራና ከጀመረበት ጀምሮ እስከ ቤተ መንግስት በሠም ለበጠው ዘንዶው ውሃ ሊጠጣ ወንዝ ቢሔድ ሠው ሠብስቦ እንጨት ሠብስቦ በእሳት ለኮሠው። ወደ ግንቡ ሲመለስ ከወዲያ በኩል ያለው ጠብቆ ዘንዶው ሲመለስ በኋላ እሳት ለኩሠው እዚያው ፋትሮ ፋትሮ ይሞታል። ከዚያ ጀምሮ ሣብታህ የተባለው ሠው መንግስት ይዞ ሲመራ ቆዬ። እስከ አምስት ጉልበት ሲገዛ ቆየና ስድስተኛ ንግስተ ሳባ ልትገዛ ስትመጣ … እሷ ስድስተኛ ጉልበት ናት ‹‹ኦሯ እኛስ እንሰጥሽም ጠቅላላ ለናንተ ስንገዛ ልንኖር ነው? ዘላለም ልንገዛ ልንኖር ነው አሉና ቃል ኪዳን አፍርሠው አንሰጥሽም አሉ። በቃል ኪዳን አምላክ እባካችሁ ተዉኝ እንኳን እኔ የኔም ልጅ እንዴውም የልጅ ልጂ መግዛት አለበት ሠባት ዘር ነው መሃላው። ከዚያ በኋላ ዋሻው ማነው ግንቡ ፍርስራሽ ላይ ሁና ዘንዶው ጭንቅላት በፈሠሠበት ላይ ሠባት ቀን ብታለቅስ ሠባት ክንድ ዘንዶ ተፈጠረ ሁለት ሠባት ስትጸልይ አስራ አራት ክንድ ተፈጠረ ከዚያ በኋላማ ህዝቡ እግዞ ብሎ ለመነ›› ሳንቺም ሠባት ጉልበት እንገዛለን›› ሲላት ‹‹እሺ›› ብላ ዘንዶውን ስታስገድል ካውራ ጣቷ ላይ ደሙ ፈንጥቆ የአህያ ሸሆና አውራ ጣቷ ላይ በቀለ ንገስተ ሣባ ከግሯ ላይ ቀንድ አላት ሚሉ ይሔን ነው።

## ተረክ 6፡- ዛጎል

የሠባቱ አገዎች እናት ዛጎል ነው ምትባል። አዱግ ለአደን ጫቃ ለአደን ጫቃለጫቃ ሲሔዱ ያገኟት አጉሪ ናት። ግን መንገድ ምትመራቸው የነበረ እሷ ናት አባታቸው ደሞ አዴል ነው ሚባል።

## ተረክ 7፡- ሰባቱ ወንድማማቾች

ሰባቱ ወንድማማቾች የሚባሉ አንከሻ፣ባንጃ፣ኪኩራ፣ጫራ፣መተከል፣ዚገም እና ቱምሃ ናቸው። ዋናው መነሻቸው ላስታ ሰቆጣ ነው። ከዚያ ተነስተው ጎሽ እና ዝሆን ለማደን ነው ወደዚ የመጡ። የነዚ የሰባቱ አገዎች እናት አዱክ ነው ምትባል። ከዚያ ቦታው ለምለም መሆኑን ሲያዩ ተመልሰው ሂደው ላባታቸውም ለምሽቶቻቸውም ለዘመዶቻቸውም ነግረው መጡ እነዚህ አገው ምድርን ተክለው ተከፋፍለው መኖር ጀመሩ።

## ተረክ 8፡- አገው

ከሠሜን ክፍለ ሀገር በኤርትራ አካባቢ ከረን ከሚባለው ቦታ አገው ነው የተገኘ ነው ሚባለው፡፡ ዛሬ ራሡን ችሎ ኤርትራ ተብሎ ተሠይሟል እንጂ ግንዱ አገው መሠረቱ ከዚያ ሲሆን ኋላ ግን ሠው እየበረከተ ሲሔድ ተስፋፍተው መጠው ሀልሀል ቦጎስ ሚባል ሠፈሩ ይላሉ፡፡ ከኔ ይልቅ ግን መፃፍ ብትፈልጊ ይሻልሽ ነበር። እንደገና ሲፈልሱ ግማሹ ወደ ሠቆጣ ሲፈልሱ መጀመሪያ ወንድማማቾች ቢቸና ነው የገቡ የቆዩት፡፡ አገው ካምፕ ሚባል አሁንም አለ ቢቸና፡፡ ‹‹አገው ሲነቅል ጎጃም ሲተክል›› ብሎ ነው አሁን የቢቸና ሠው ንግግር ሲከፍት፡፡ እንደገና ደጀን ግርጌ ኩራር አርባ ቱንሳ ምትባል ደብር አለች፡፡ ዋናይቱ አገው ሰሪት ናት፡፡ ስሪውና መናሀሪያው ቦታው ግን አጋዊት ነው ሚባል ይላሉ አሁንም አማሮች አንዳንዶች አሁንም እንደዚያ ይላሉ፡፡

## ተረክ 9፡- ሰባቱ ወንድማማቾች

የአገው ብሔረሰቦች አመጣጡ ከሠቆጣ ሲሆን ከሠቆጣ የሚኖሩ ሰባት አገዎች ለአደን እንደመጡ ሲያድኑ ሲያድኑ ከቆዩ በኋላ ሀገራቸው የመጡበት መንገድ ሥለጠፋባቸው እዚያው ጫቃ ሲያድሩ ሲሂሂሩ እንደ አጋጣሚ እዚያው ጫቃ ውስጥ የምትኖር አዱግ የምትባል ሴት ያገኛሉ፡፡ ጫቃ ውስጥ ለሠባት ወር ነበር የቆዩ የነዚህ ሰባት አገዎች እናት ዛጎል ስትባል አባታቸው ደሞ አዴል ይባላል፡፡ ሠባቱ ወንድማማቾች ባንጃ፣ ኳክራ፣ ጫራ፣ ሻሽና፣መተከል ዳንግላ ናቸው፡፡

## ተረክ 10፡- የፈረስ ማህበር

የፈረስ ማህበር የመጣ ለኢትዮጵያ ሲል ጊዮርጊስ በፈረስ ተዋጋ ብሎ ነው፡፡ ታሪኩን አልለቅም ብሎ ነው፡፡

## ተረክ 11፡- ሰባቱ ወንድማቾች

አደን ሲመጡ አገሩን ለምለም መሆኑን አይተው ተመልሰው መጠው ኖሩ ነው ሚሉ፡፡ እንደገዝምድናችን ሁሉ ባላችን አንድን ነው፡፡ ግን ሰቆጣዎች ባላቸውን አልለቀቁም የኛዎች ናቸው የተዉ፡፡ ሰቆጣዎች እንዳለ ናቸው፡፡ የጸጉር አላላጭ ላይ ከፍ ያለች፣ ለትዳር የደረሰች፣

ያገባች፤ ያገባች እያሉ የኛዎች ግን እንዲህ የነበረውን ትተዋል አልነበረም ሚል ካለ ይምጣና ከኔ ጋር ይከራከር፡፡

## ተረክ 12፡- አግዚ እና ባክጻ

ባለግዚያር ማበር ባክፃ እና አግዚ የሚባሉ ወንድማማቾች ናቸው፡፡ በጣም ማክበር የጀመሩ፡፡ ጋን ላይ ጠላ ይሁን ወተት ተሹሞ አግኝተው ነው፡፡ እናታቸው ባመት ባመት ማንስ ባለግዜር ታከብራለች አሁን ማበሩ ሲደርስ ይጨንቃታል ጋኑን አጥባ ከድና ትታዋለች እና ፈጣሪ ሞልቶላታል፡፡ ‹‹እናታችንን ለካ በድለናታል›› ብለው እነሡ ተቀብለው ሲያከብሩ ሲያከብሩ ቆዩ፡፡ አሁን አንድ ሺ ማበርተኛ አለ ከግንባህ በታች፡፡ አሁን የነሡ ዘር ፈልሠው እዚ ዚገም በታች በኩል ማክበር ጀምረዋል፡፡ ይሔ የግዜር ማህበር ነው፡፡ እኛ ብዙ ሠው ነው አሁን ማበርተኛ ያለ፡፡

## ተረክ 13፡- ግንኙ

ግንኙ ምን መሠለሽ ወገኑን ወገኑ ሲያገባ ስለሚችል የናትም ያባትም ዘር ግንኙ አለ፡፡ አዊ እስከ ሠባት ትውልድ አይጋባም፡፡ ... ወገኑን ወገኑ ካገባ እማ ዘር አይባዛማ፡፡ ዝምድና ማስፋት እንጂ ዘሩ እና ዘሩ እየተጋባ ዘር ማሣነስ የለበትም፡፡ ግንኙ ወገናዊ ነው፡፡

## ተረክ 14፡- ዚገም

ዚገም አይደለም ወደዚ የወረደ፡፡ የዚገም ሚሽት ሰቆጣ እና ምኽንን ሁለቱን ወልዳ ስትሞት ጎንደር ላይ ሂዶ ማንስ ከሚባል አገር አመጣ፡፡ አዎ ንጉስ ሱሲንዮስ የሚባል ያለበት እንፍራዝ ከሚባል አገር አመጣ፡፡ እሷም ሁለት ልጆች የነበራት ናት፡፡ ይቺ ከጎንደር እንፍራዝ የመጣች ሴት የዚገምን ልጆች በብትር እየደበደበች ቆሎ ብቻ እየሰጠች በራብ ልትጨርስ ስትል ሁል ግዜ ያለቅሳሉ፡፡ ባዲ የሚባል በሬ ዳልጋው መሬት የሚደርስ በሬ ‹‹አይዟችሁ እኔ እናትም አባትም እሆናለሁ አምላክ እናንተን እንዳነጋግር አፌን የከፈተ አምላክ ያውቃል›› ይላል፡፡ በኋላ ሽንቱን ወተት እበቱን እርጎ እያረገ ሲያበላ እነዚ ልጆች በጣም አማረባቸው፡፡ በጣም በጣም ወፈሩ፡፡ አሁን በበረበሬ እያጠነች ስትጠይቅ ሴቷ ባዲ ይሔን አረገልን በማለት ተናገረች ወንዱ ዝም አለ፡፡ ጻጉሜ ሲደርስ ካልታረደ አልኖርም አለች፡፡ መኸንም በሽማግሌ ተይዞ ሲጠየቅ እሺ አርዳለሁ አለ፡፡ ከዚያን ጻጉሜ ሲደርስ ካራውም ተሳለ ‹‹ኧረ ባዲ ካራውስ ተሳለ ልትታረድብን ነው እውይ አሉ›› ወንዱን ትከሻው ላይ አረገ ከዚያ ‹‹አንቺ ሴት ነሽና ኋላ ሁኚ›› ብሎ ዋጅራ

አቦን አርጎ ሻሸና አፋፍ ይደርሳል፡፡ ከዚያ በዶንዶር አርጎ ቻጃ ሙካ ላይ ደርሶ እዚያው ያርፋል፡፡ አሁን እነዚያን ልጆች እበላቸው ካደጉ በኋላ ‹‹እናንተ ሽናሻ ጋር አትጋቡ›› ብሎ ቅዱስ ገብርኤል በብስራት ስለተናገረ በሬው እነዚህን ልጆች ያጋባል፡፡ አዳምም ከጎኑ ላይ የወጣችቱን ነው ያገባ፡፡ እናንተም እርስበርስ ተጋቡ እንጂ ሽናሻ ጋር አትጋቡ ብሎ አጋባ፡፡ ከዚያ ሰቆጣ ማንን ትወልዳለች? ቻንጋን፣ዓንጓን፣ ሚንጋን ወለደች ራሱ ሞራይ ሙኻንንም ወለደች እነዚህን ወልዳ ሞተች፡፡ አሁን ሙኻን ብቻውን ቀረ ‹‹አንተ ሙኻን ና እኔ መርቼ ልውሰድህ›› ልጆችህን ምታሳድግበት ቦታ ሲል ‹‹ሽናሽ አያሳልፈኝም›› ይላል እንግዲያስ ሂድና ‹‹የቀጋ ብትር ሳትፈቀፍቀው አምጣ›› አለው፡፡ ብትሩን ይዞ ልጆቹን ይዞ ሽናሻ ጋር ተቀላቅሎ ሲሄድ ‹‹ምንሜና ቋንቋ ማያውቅ መጣ ብለው ሽናሻ ሮጦ ሄደ፡፡ ‹‹ሂደህ ሽናሻ ንጉስ የተቀመጠበት ቦታ ላይ ሒደህ ይህን ብትር ተደብቀህ ሰክተህ ቀጥታ ሩጠህ ና›› ብሎ ባዲ ይናገራል፡፡ ከዚያ ሽናሻ መሀል ቆይቶ ጦሩን ሰክቶ ሩጦ ይመጣል ምንድን ነው ይሔን አይነት ነገር ይላል፡፡ የሽናሻ ንጉስ ‹‹እኛ እደዚ ያለ ጦርም አይተን አናውቅም አምላክ እንጂ እኛን የወጋ ሰው አልወጋም›› ብሎ ዱራ ማዶ ሒዶ ሽናሻ ይቀመጣል፡፡ እንገዲህ ቡክር የሚባል ዋና ሽናሻ ብቻ ይቀራል፡፡ እሱ ለዚገም ኩሲያ ቡክር ምትባል ልጁን ይድራል፡፡ እሷ ማንን ትወልዳለች አዋሻን፣ ጫራጃን አንባቂን ማለት ነው ናናን፣ ጎዛናጅን፣ (አሁን የቢምረው አባት ያለበትን) ጊዜን ትወልዳለች፡፡ ዘጠኝ ቤት ዚገም የሚባለውም ‹‹ ሴስቲ ግና ዚገም›› የሚባለው ይሔ ነው፡፡

ይሔን እኔ የፈጠርኩት ታሪክ አይደለም ቀኛዝማች በላይ ስዩም ከፊታውራሪ ደረሶ የሚበልጡ ናቸው፣ ፊታውራሪ ዘለቀ ተሰማ (ለኛ አጎት ናቸው አህቲ ላይ ነው የተቀበሩ) እና ፊታውራሪ ደረሶ ራሳቸው የነገሩኝ ነው፡፡ እና አዊ እንደዚሁ ዘሩ ብርር ብሎ የመጣ አደለም በአምላክ ፈቃድ በእግዜር የተመራ የመጣ አደለም የአዊ ታሪክ…

## ተረክ 15፡- ካድሪ

አንድ ካድሪ ነበረ፡፡ ኢሠፓ ነበረ፡፡፡ እኔ አሁን አገው ነኝ ዘሬን አልክድም እሡ አገውኛ አልናገርም አልችልም አለ፡፡ አፉ ሁላ እኮ ያስታወቅ ነበረ፡፡ እኛ ደንታም የለን ግማሹ አገው ግማሹ አማራ ነበርነ፡፡ እና በጣም እናማዋለን አናስጠጋውም እና በደርግ ግዜ ፆም መፆም አይቻልም ነበረ ፆም ፈተን ስጋ ልንበላ ስንል አሁን ያንን በሉ ብሎ ለኢሠፓ ነገረ፡፡ ኢሠፓውም ‹‹የጓድ መንግስቱ ሀይለማርያን ፎቶ ሲቀዱ ብታይ ምን ትላለህ?›› አለው ‹‹ለምን

በላችሁ ብዬ እጠይቃሁ›› አለው ‹‹ምናገባህ ይጠቅማል ካሉ ይበላሉ ካላሉ ይተዉ አንተ ምን አገባህ?›› ብሎ አሳፍሮ ላከ አልሻለሁ፡፡ እንዴት ያለ ወጣ ጎበዝ ካድሬ መሠለሽ፡፡ እኛ እንደፈለግነ እንድንሆን ነው ሚፈልግ፡፡

## ተረክ 16፡- አዱግ

የሠባቱ አገዎች እናት እናታቸው ናት ነበረ የምንል አሁን ግን ሞግዚት ናት አሉ ጓሲ ተራራ ነው የተቀበረች ማጣራው ነገር ግን አሉ ወደፊት፡፡ አሁንም መቃብሯ አለ፡፡ ድንጋይ ጥለን ነው የምናልፍ ‹‹ለምንድ ነው?›› ብንል ‹‹አፈር ማልበስ ነው›› አሉን፡፡ ሠው ማያልፍ ሁኖ ነው እንጂ እስካሁን ምንጥለው ድንጋይ ተራራ ያክል ነበር፡፡ እኔ ልክ እንዳንቺ ነኝ እርግጡን ነገር አጥቼ ነው፡፡ እና ማጣራው አለ፡፡ አንቺ እርግጡን ነገር አጠሽ አደለ ምትንከራተቺ፡፡

## ተረክ 17፡- ሰባቱ ወንድማማቾች

ሠባት አገዎች ለአደን መጠው ሲመለሡ ሲሉ ቦታው ጠፍቶባቸው ሳለ አዱክ ዛሒሪ ተራራ ላይ አግኝታቸው እንሔዳለን ሲሉ በዚያው ስለምትቀሩ አንድ ዋስ ስጡኝ ስትል አንከሻን ዋስ ሰጠው ሄዱ፡፡ እንደገና ስድስቱ ተመልሠው ባባይ ቃልቻ እየተመሩ መጡ፡፡

## ተረክ 18፡- ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ››

ዘጠኝ ወንድማማቾች አገዎች ከአንድ አማራ ጋር ተጣልተው ስምንቱ ከዛፍ ላይ ወጠው ሾላ ይሁን ምን ይሁን ይበላሉ፡፡ የተጣላው ብቻ ቁሞ እያለ ‹‹አንተ ወንድሞችህሳ?›› ቢለው ‹‹ሁሉም ሞተው እኔ ብቻ ቀረሁ›› ይላል፡፡ ከዚያ ሾላ ነው ምንድን ነው መሬት ላይ ዱብ ስትል ቀና ብሎ በያይ ስምንቱም ከላይ ናቸው፡፡ ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ ስምንቱን አኑሮ አንዱን አጫወተኝ›› ስምንቱ ከላይ አንደኛው ከታች ማለቱ ነው፡፡

## ተረክ 19፡- ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ››

አገው አሁንም ልቡ ዘጠኝ ነው! ጀግ ነው ልቡን አልሰጠም፡፡ እንዲህ የተባለ እንግዲህ በድሮ ግዜ አላምን ብሎ ነው አሉ፡፡ እና ጦርነት ላይ ጦር ገጥሞ እርቅ ያርግ ሲባል አገው የውነት እርቅ ነው ብሎ አላምን ብሎ ግማሹን ጦር ሸሽጎ እውነት እርቅ መሆኑን ሲያይ አወጣ ነው ሚባል፡፡ ሌላ ምናለ እና ሁልንም ጦር አውጥቶ ከማለቅ … ዋ ሞኝ ነሽ?

## ተረክ 20፡- ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ››

አገውና አማራ በድንበር ተጣልተው ነው እርቅ ይባልና ለድርድር ቀርበዋል፡፡ አገው ስምንት ወንድሞቹን ጫቃ ውስጥ ደብቆ አርጎ ብቻውን እሱ ይወጣል፡፡ ኋላ እርቁ የውነት መሆኑን ሲያረጋግጥ ጫቃ ውስጥ የተደበቁትን ይጠራል በዚ ግዜ አማራ "አገው ልቡ ዘጠኝ ስምንቱን አኑሮ ባንዱ አጫወተኝ" አለ፡፡ እንግዲ ይሄ ለብልሃት ነው እርቁ የውነት ካልሆነ ከወንድሞቹ ጋር ሁኖ ሊገጥም ነው፡፡

## ተረክ 21፡- አዱግ

አዱግ ጫቃ ውስጥ ምትበላው ሳማ ነው፡፡ በአዊ ‹‹ሴሪ›› ይባላል፡፡

## ተረክ 22

ከዚገም ውጪ ያለ የደጋ አገው በሙሉ ደመኛውን ሲገል እኔ ነኝ ማንገደለ ብላችሁ ሠው እንዳታስቸግሩ ብለው ነው አሉ ሚገሉ፡፡

## ተረክ 23፡- ሰባቱ ወንድማማቾች

የዋግህምራ ልጅ ዳግማዊ ዋግህምራ ሠቆጣ ንጉስ ዳዊት ከሠቆጣ ተነስቶ ከጉባያ እስከበላያ አገው ነው ካለ በኋላ እኔ በላያን ሣልይዝ አልሞትም ሠባቱ አገው ተሠደው እስከየት ይመጣሉ? ጃዊ ከዚያ የት ይቀመጣሉ ጃዊ ከዚያ ይቀመጣሉ፡፡ ጎጃም ላይ ቀመጣሉ፡፡ ደብረ ማርቆስ ላይ ጎጆ ሠርተው ተቀመጡ፡፡ ‹‹ያች ጎጆ የማናት?›› ይላሉ ‹‹የነዚ ጆሮ ቆራጭ አገው የሚባሉ ጆሮ በላ አደሉም›› ይላሉ፡፡ ‹‹ኦሯ አገው ጎጃም? በሉ እንሂድ እነዚማ ጆሮ ቆራጭ አገው ናቸው›› ብለው ጉሚ እየሱስ ዛዝበል ኩኒ ስላሴ … ዛዝበል ስጋዲ አቦን ኩፈር ማርያምን ተሻግረው ሸሹ ይባላል፡፡ ከደብረ ማርቆስ ከተቀመጡ በኋላ ደና ቦታ ሲፈልጉ በየቦታው ዝሆንም ጎሽም አንበሣ እየገደሉ ደብረ ማርቆስ ቆዩ፡፡ ‹‹እንግዲ እናታችን ብዙ ቦታ አይተናል አብረን እንሒድ›› ይሏታል፡፡ ‹‹እንግዲ ልጆቼ እኔ አልሔድም ላሜ አንዲት ስላ የሆነች አለች፡፡ ሲላዋ ቦታ ትመራለች፡፡ ወላዷም አውራ አስከትላ ትሂድ ሳሞች ይከተሉ››፡፡ ትላለች ከዚያ ቀጥ ብላ መጣ ወዴት ታርፋለች? ዳንጉላ ዮሐንስ ሚባል ሜዳ ላይ ዛሬ በሬ አሥሩ ተብለው የርሻ ቦታ ሆነኟ የሠባቱ አገው ዋሻ አለ እዚያ ታርፋለች፡፡ ከዚያ አሀ ብለው በሠረገላ መጠው ከዚያ ተነስተው ወዴት ይመጣሉ? ሠባቱም ጋሻና ሠባቱም ጦር ይዘው የት ይመጣሉ? ዳንጉላ

ዮሐንስ አንካሻ ወረደ ማነው ሚባለው? አምላክ ሠርቶላቸው ዋሻው ውስጥ ቆዩ ከዚያ እናታቸውን መሀል ኮረብታ ላይ ሁኚ ብለው አደን ሲገቡ ሽናሻ አላስገባም ይላል። አሁን ምን ይሆናል። እነዚህ ሽናሻ ተራራ ለተራራ ያሉትን በእሳት እስከላይ ድረስ ካቃጠሉ በኋላ ሣልደርስ አልቀርም ያልሁት እቺን ነው ብሎ በዳንግላ በጫራ አርጎ ወርቅ በሜዳ አርጎ መንገዱን ቀዶ የት ይገባል አንከሻ ገብሬል በበላይ አርጎ ይገባል። ቦታዋን ሲያይ እዚያ ይሆናል። ከዚያ ንጉስ ዳዊት የሚል ፅላት አስቀርጾ ሲሞት እዚያው ተቀበረ። ይሔ አሁን አስር አመትም አልሞላም ጽላት ተሠረቀ ብለው ህዝቡ አለቀ የወንድሙ ስም ጠፋ እንጂ ከጉባያ እስከ በላይ አገው ምድር ብሎ ዳግማይ ዳዊት ለሠባቱ አገው አስይዞ እሱ መቃብሩን ይዞ ሞተ።

## ተረክ 24፡- ሰባት አይን ያለው አባይ

ሠባቱ አገዎች ሠከላ ላይ ሠባት አይን ያለው አባይ ያገኛሉ። እቺ የኛ ያውልታችን ኋላ ማንስ መድሃኒያለም ሚል ተከሉ። በፊት በአሪት ሁለት መቶ ሀያ አራት አመት የተቀደሰበት ደብር ነው ከዚያ ዮዲት ምትባል ስቅንቅን ከምትባል አገር መጣ የዮዲትን አባት ጌድዮንን ስለገደሉ ከዚያ ቂም ይዛ ሰከላ ያለውን ደብር አቃጠለች።

## ተረክ 25፡- ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ ››

አገው ልቡ ዘጠኝ ያሉት እንዴው ብዙ ጊዜ መጠው አማራም ሆነ ትግሬ አገው ልቡ ዘጠኝ ያሉ ቋንቋው ስለማይገባቸው ነው እንጂ አገው ልቡ አንድ ነው። አዱግ ለአገው ሁሉ እናት ናት ዳንግላ ጫራ ቱምሃ አገው ናቸው።

## ተረክ 26፡- አገው

በድሮ ጊዜ ነው አሉ የጭቃ ሹም ነው ምንድነው ሚባል ግብር ሊያስከፍል ሂዶ ነው። ለአማራው ሹመኛ ግብር አንከፍልም ብለው እምቢ ብለዋል የግምጃ ቤት አገው ተሹሞ ይሔዳል። ሲሄድ ስንቅ የሚሆን ቋንጣ ከኪሱ ይዞ ነበር። ከዚያ ህዝቡን ይሰበስብና “እናንተ ለምንድ ነው ግብር ማትከፍሉ?” ቢላቸው “አልሰማንም” ሲሉ “ይሔ ጆሮ ለምንድነው ሚጠቅም?” ብሎ ሽክ ሽክ አርጎ ጣለ ጆሮአቸውን። ከኪሱ አውጥቶ ቋንጣ የበላውን ‹‹አገው ጆሮ በላ” አሉ።

## ተረክ 27፡- አገው

እሱማ ቋሪት ላይ ደርግ ላይ እኮ ነው። ደርግ ሲነሳ አልገዛም ሲል በተለይ በክርስትና የተነሳ ነው። ደርግ ክርስቲያን አይደለም አንገዛም ብለው ነው። እንዳሉት ጆሮ ቆርጧል ነው ሚባል። አንገዛም ሲል ጊዜ ጆሮ ቆርጦ ቆርጦ ጣለ አገው። ግን ጆሮ በላ የሚሉትን እውነት አትበይ ይሄ ሌላ አገር የመንግስት ጦርነት ላይ ተደረገ የሚባለውን ነው አገውን ጆሮ የበላ የሚሉት

## ተረክ 28፡- ማቺካና

እዚ ዚገም ማቺካና ምትባል ገበያ ነበረች ባሪያ ሁሉ እዚያ ነበረ ሚሸጥ በኋላ ሀይለ ስላሴ ባሪያ ሚባል አይሸጥም ብለው መሸጥ አስቆሙ።

## ተረክ 29፡- ቋራ

ቋራ ማለት ባገውኛ ፀሀይ ማለት ነው። በበላያ ቋንቋ ፀሀይ ማለት ነው። እናታቸው አይዱግ ነበረች። ዚገም በመጨረሻ ነው ወደዚ የመጣ።

## ተረክ 30፡- ኮሶ በር

ኮሦበር የተባለ ጃንሆይ በዚህ በፈረስ አልፈው ሲሔዱ ኮሦ በር ላይ ሲደርሱ ኮሦ እንጨት ነበር እና ኮሦበር አሉት።

## ተረክ 31፡- የአገውና ጉሙዝ ወዳጅነት

አሮጌው ዳንግላ ‹‹ጉምዝ›› ይሸጥ ነበር እና አገዎች ግን ጉምዝን ደብቀው ያስቀሩ ነበር በዚህ የተነሣ አገውና ‹‹ጉምዝ›› ወዳጅ ናቸው።

## ተረክ 32፡- እንጅባራ

ያዊ ዞን ዋና ከተማ እንጅባራ የሆነ ከማርቆስ መጠው ሠባት አገዎች እዚያ ስለሠፈሩ ነው። በኋላ ጣልያን መጣና ዳንግላን ዋና አረገ ጃንሆይ መጡና ዳንግላን አውራጃ፣ ደብረማርቆስን አውራጃ፣ ቻግኒን አውራጃ አደረጉ። ዋናው መናሀሪያ ከሠቆጣ መጦ የሠፈረው እዚያ ላይ ስለሆነ ያገው ዝሆን እንጅባራ ሆነ።

## ተረክ 33 ፡- አገውና እስራኤል

አገው የእስራኤል ዘር ነው ይላሉ ንግስት ሂዳ እዚያ አርግዛ መጣ ነው። ሌላ ታቦት ቢሠጥ አክሡም ፂዎንን ለውጠው አመጡ። ንጉሡ ሂዱ አምጡ ቢል ተሻግራለች ተሻግራ ያለችቱንማ ተዋት ብሎ ተወ።

## ተረክ 34፡- ቡዳ

ቡዳ መጀመሪያ ትግራይ ነበረ የነበረ። መንፈስ ነው ቡዳ የትግራይ ህዝብ ሀይማኖተኛ ስለሆነ በፀሎት ሲያባርረው ወሎ ገባ ወሎም ሲፀልይ ህዝቡ ጎጃም መጦ ቀረ።

## ተረክ 35፡- ንጉስ ሰለሞን

ንጉስ ሠለሞን ከገነት ክንፍ ባላው ፈረስ እየተመላለሠ ነው ጥበብ የተማረ። አንድ ቀን ፈረሡን አምደ ወርቁ ላይ አስሮ ሲገባ ፈረሡ በርግጎ የታሠረበትን አምደ ወርቅ ... በጠሠና መጣ ... ይሔ አምደ ወርቅ ሠለሞን ቤተ መንግስት ደጃፍ ላይ ነበረ ንግስተ ሳባ ተራምዳው ስትገባ ሸኮናው ሹልክ ብሎ ወደቀ ያንን ደንገጡሯ ናት ይላሉ የዛጉዬ እናት በመሀረብ ቋጥራ ያዘችው።

## ተረክ 36፡- አገውኛ

አገውኛን ሎሎ የሚባል ሰይጣን የፈጠረው ቋንቋ ነው። እግዚሃር አልፈጠረውም በሚል። የአባ ተክሃይኖት ስብከት ያገው መንግስት ለቅጣት የመጣ ነው በማስባል ጣሉት እንጂ አገው ለሰላሳ ሶስት አመት እዚያው ላስታ ላይ ነግሿል።

## ተረክ 37፡- ዚገም

ከሠባቱ አገዎች አንዱ ዚገም ነው። አዱግ እናትም ይላሉ ሞግዚትም ይላሉ። እንጅባራ ላይ ነው የተቀበረች። ዚገም ሰሜን ዚገም አካበቢ መኸን እንደሚባል ነው። ዚገም ዘጠኝ ልጆች አሉት መንግሀ፣ጠንግሀ፣ጫራጃ፣ጎሀናኸ አዋሻ እና ጊሣ የቀሩት አፌ ላይ ነበሩ ጠፋብኝ የሠው ስም አሁን የቦታ ስም ናቸው እነዚ በጠቅላላ። መተከል እንዳለ የአዊ ታሪክ ነው።

## ተረክ 38 ፦ አገው

ቅማንት፣ብሌን፣ዋግ፣አዊ እነዚ ባጠቃላይ አገው ነው ሚባሉ። ዋግህምራና አዊ ቦታ ሲበታተኑ ቦታ ሲቀያየሩ ቋንቋ እየተበታተነ መጣ።

## ተረክ 39፦ ሰባቱ ወንድማማቾች

ሠባቱ ቦታ ተከፋፍለው ትልቁ አንከሻ። ነው ባንጃ መተከል እና ጫራ ኳኩራ እና ቱምሃ ሚባሉ እና ዚገም ሠባቱ ወንድማማቾች አዊ ዞንን ተከፋፋለው ቦታ ያዙ። በአስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት ተጽኖ ተደርጓል ነው ሚባል። ግን ቋንቋችን ባህላችን የአዊ እና የዋግህምራ ባህል ሣይበረዝ ከዚህ ደርሷል። በኃዲግ ዘመን የራሡን ቋንቋ ከቀበር አውጥቶ ራሡን ጠርቶ የነበረ ነው። አማራና አገው ጥንተ ግንዳቸው አንድ ሆኖ ሣለ ብሔር ብሔረሰቡ ልዩነት የለውም በወቅቱ የነበረው መንግስት የፈጠረው ነው።

## ተረክ 40፦ ‹‹አዊ ገፎራ ብር ዜንጋ››

‹‹አዊ ገፎራ ብር ዜንጋ›› ማለት የአገው ልጅ የብረት ዘንግ ነው ማለት ነው። ይሔ መልከ መልካም ስለሆነ አዊ በአቋሙ ያለው... በአቋሙ ቀጥ ያለ ስለሆነ ነው።

## ተረክ 41፦ ‹‹አገው ሲሰለጥን በረቃ ጥላ ይዞ ይሄዳል››

በድሮ ጊዜ ነው። አገው ሙሽራ ሊያመጣ ወደ ሩቅ አገር ጥዋት የጀመረ ጥላውን ዘርግቶ ሲሄድ ሲሄድ የአገው ጥላ ስለማይታጠፍ ቀን የተዘረጋው እስከ ማታ ድረስ ሳይታጠፍ ዝም ብሎ ይጓዛል ይሄንን ያየ መንገደኛ “አገው ሲሰለጥን በጨረቃ ጥላ ይዞ ይሄዳል” አለ አሉ።

## ተረክ 42፦ ንግስተ ሳባ

ንግስተ ሳባ በአራት ሺ አመተ  አለም ነው ሠለሞን ዘንዳ የሔደች በዚያ ጊዜ አብራት የሄደችው ገረዷ ሳሁዬ ትባላለች። ግን የወለደችው ልጅ ሙቷል ሚሉ አሉ።

## ተረክ 43 ፡- ንግስተ ሳባ

ንግስተ ሳባ ... ንግስተ አዜብም ትባል ነበር ከዚያ ከምኒሊክ ግዜ በፊትም አገውኛ ነበር።

## ተረክ 44 ፡- ኩላ

ኩላ፣ ጫራጃ ጎሀናዥ ሦስቱ ደብር አንድ መቅደስ ነው። ሌላ ሦስት ደብር ደሞ አንድ መቅደስ ይሆናል። አሁን እኔ ኩሉ ነኝ ጫራጃ ነኝ። ያባቴ አገር ዚገም ነው። ያባቴ እናት ኩሊ ናት ያባቷ የፊታውራሪ ደረሦ ተሠማ ልጅ ናት። የኔ አባት እናት ከበቡሽ ተሠማ ናት። እኔ የዚገም ወረዳ ሹም ሁኜ ስሰራ የዚገምን ህዝብ እንዴት አርጌ እንደያዝኩ። ከአባይ ጀምሮ ወደዚ ሲመጣ ስንት ቀን እደሆነ አስጠንቼ ወረዳ እንድትሆን ብዙ ትግል ፈጅቻለሁ።

## ተረክ 45፡- ቋራ

ቋራ ማለት ባገውኛ ፀሀይ ማለት ነው። እናታቸው አዱግ ነበረች። አንከሻ፣ሻሽና፣ጫሪ ሚቲኪሲ ተብለው ተቀመጡ ዚገም ደሞ ዚገም መጨረሻ ነው ወደዚ የመጣ የዛን ጊዜ ሠለሞናውያን ነበር አገዛዙ። እዚ ዚገም ወሮሞ በዚያን ወቅት ነበር። እዚ ፊት ለፊት ማችካና የሚባል ዋሻ ነበር። ይሔን ታሪክ እንዳንቺ አዲሳባ ምትማር እንክስ ምትል ልጅ መጣ ነግሬ ሠድጃለሁ። እንዲያውም ፈረንጆችን ሁሉ ይጂ እመጣለሁ ብላ ነበረች የባህል መዳኒት እንዲገዙ ...

## ተረክ 46፡- ዚገም

ዚገም ‹‹እንዚግ ጌም›› ለም ነው ማለት ነው። ዚገም ዘጠኝ ልጅ አሉት አዋሻ፣ጎሃናጅ፣ጉንጋ፣ ጊሣ፣ዛልና፣ናና፣ጠንግሃ፣ጫራጃ፣መንግሃ እነዚ እንግዲ ዘጠኙ ናቸው። ዘጠኙ ቀበሌዎች አሁን እነዚ ናቸው። መተከል ወደ ጉምዝና ሽናሻ ሄደ እንጂ ያንድ ቀበሌ ያንድ ጎጥ ስም ነው።

## ተረክ 47፡- ላሊበላ

አፄ ላሊበላ ኮ አገው ነው። የላስታ አገው ነው። ግን ቅኔ የተማረ እዚህ ጎጃም ማርቆስ ነው። በጣም ቅኔ አዋቂ በጣም ስለነበረ ሁለት ተማሪዎች ይቀኑበት እና ለመምሩ ምግብ ሲሰራ ሳለ የሞተ የህፃን ልጅ እጅ ቆርጠው ወጡ ውስጥ ከተው ቡዳ ነው አስባሉ ከዚያ በኋላ ተመልሶ ላስታ ገባ.....

## ተረክ 48፡- አገው

ወሎ፣ጎንደር ትግሬ ያገው ህዝቦች ይኖሩ ነበር። ይሔ መፃፍ ላይም ግጥም ብሎ ተፅፎ ያለው ነው። ቋንቋውን በማጣጣል እና በሀይማኖት ተፅዕኖ በማድረግ ብስራቱ ለሠባት መቶ አመት እየተጣጣለ ቆየ አሁን ግን እንደገና እያቆጠቆጠ እያበበ መጧል።

## ተረክ 49፡- አጼ ቴዎድሮስ

አፄ ቴዎድሮስ የቋራ አገው ነው። "አዊ ቁሪኒ" ሚለው ላይ ነው አገሩን ቋራ ያሉት። አዊ ቁሪኒ" ማለት ፀሀይ ብቅ አለች ማለት ነው በአገውኛ። ዛሬ እሱን ማንም መጠቀሚያ አርጎታል ጎንደርም፣ ወሎም፣ ትግሬም የኛ ነው ይላሉ እንጂ አፄ ቴዎድሮስ ማ አገው ነው። በድሮ ጊዜ ነገስታት ጎንደር ነበር ሚነግሱ።

## ተረክ 50፡- ኖህ

ከጥፋት ሉሃ በኋላ የተገኙ ስምንት ናቸው። እግዚያር ኖህን አዘዘው ከእንጨት ጎፈር መርከብ እዲሠራ ቁመቱን ወርዱን ይህን ያል ብሎታል። ካም ከንዓንን ኩሽን ነው የወለደው ነምሩድን ነው የወለደ ነምሩድም አለምን አንቀጥቅጦ የገዛ ገዋና ነው። ‹‹ገዋና እንደ ነምሩድ›› ተብሎ በእግዚሀር ፊት ተመስክሮለታል። የፈረንጅ እናት የእኛ እናት አንድ ነው። እኛ ባባታችን ስለሣቅን ስለተረገምነ ባሪያዎች ሆንነ እንጂ አንድ ነን። አሁን ይሔን ትልቅ የብራና መፃፍ ነበረኝ እዚያ ላይ አሣይሻለሁ ሁሉንም ታሪክ ታነቢያለሽ። አንዱ መጣና ‹‹አንድ ሺ ብር ልግዛ›› አለኝ በጣም በሆዴ ተቀየምኩት ‹‹አሁን አንድ ሺ ብር ምን ዋጋ አለው›› መፃፉ ኮ ቢቀመጥ ቅርስ ነው። እነ ዶክተር ሀይለየሱስ ልጆቼ ሲመጡ እኔ አባታቸው እብድ ብሆን አላዋቂ ብሆን ጥሩ ሠው ብሆን ምስክሩ ይሔ መፃፍ ነው። እዚ ሚመጡ በደንብ ነው ሚያነቡ።

## ተረክ 51፡- አገውኛ

አለም ከተፈጠረ በኋላ ቋንቋ አንድ ነበረ ነገር ግን ከምድር ሰባት አፍ ከሰማይ ሰባት አፍ በሚደነግዝ ሰናኦድ በሚባል ሜዳ ትልቅ ግንብ በሰናኦድ ገነቡ በፀሀይ ምግብ አብስለው እስከመብላት ደርሰው ነበር አሁን ሰይጣን ሊፈትናቸው ሲፈልግ ጦር ወደ ሰማይ ወርውሩ ይልና "አሁን አብን ወጋችሁ"፣ አሁን ወልድን ወጋችሁ" "አሁን ደሞ መንፈስ ቅዱስን ወጋችሁ እያለ ጦሩን ደም ቀብቶ ወደ እነሱ ሲልክ እግዚአብሔር ተቆጣና በመካከላቸው

እንዳይግባቡ ቋንቋን ሰባ ሁለት አርጎ ለያየባቸው።... የለያየው የግዚአብሄር ቃል እንዲስፋፋ ነው ከሰባሁለቱ አንዱ አገውኛ እንደሆነ ነው እንግዲህ...

## ተረክ 52፡- ኖህ

አባታችን ኖህ ቀኝ ቀኙን ለሜም መሀል መሀሉን ለያፌት ግራግራውን ለኩሽ እግዚያብሔርን ዳኛ መላኩን ታዛቢ አርጎ አከፋፈለ በኋላ የኖህ ዘር እየበዛ መጦ ነው እኛ ሁሉ የኩሽ ዘር ነን።

## ተረክ 53፡- አገውና እስራኤል

አገው እንዲሁ ከእስራኤል ተገንጥለው መጠው ጎንደር ላይ ሠፈሩ... አዎ ንግስተ ሣባ በኢትዮጵያ ስትኖር የሠለሞንን ጥበብና ታሪክ ትሠማ ስለነበረ መጥቼ አገርህን ልይ ብላ አስፈቅዳ በኋላ ሲፈቅድላት ሂዳ ነው። እንዲያ ነው አያ አመጣጡ ተረደስቶኝ ነው። ገረድም አብራ ነበረች ለአዛገ እናትና ለንግስት ሣባ አልጋ ተሠጣቸው የጣመ ቅመም የበዛበት በልተዋል። ሌሊት ውሃ ጠማቻቸው። የሠለሞን ትራስ ላይ ቧንቧ አለ እንቅልፍ ሲወስድ ገርበብ አርጎ ሳለ አይታ ተኝቷል ብላ ስትነግር... ገረዷ ሣባ ልትጠጣ በሔደች ጊዜ የሠረቀ ይያዛል ብሎ ተገናኛት። እሷም ጠጥታ ስትመለስ ተገናኛት። ሁለቱም አርግዘው ወዳገራቸው ተመለሡ። ሁለቱም ወንድ ልጆችን ወለዱ።

## ተረክ 54፡- አክሱም

አክሡም ሚለው ውሃ ማለት ነው ‹‹አህ›› ማለት ውሃ ማለት ነው። ሹም ማለት በድሮ ግዜ አክሡም ውሃን ያስተዳድሩ ነበር። አገዎች ለሦስት መቶ ሠላሣ ስድስት አመት ገዝተዋል። መንግስታቸውን ለመጣል ብዙ ነገር ተደርጓል። ሀይማኖትን ተጠግተው።

## ተረክ 55፡- ትንቢት

የአሁኑ መንግስት ትንቢት አለው። ለአርባ አንድ አመት ይገዛል። ይህን መንግስት የእግዜር ህግጋት ነው የሚያስተዳድረው። ይቆያል። በስራው ነው የሰጠው። ይሄ መንግስት በሚወድቅ ሰዓት አገው ነው ቀጥሎ የሚገዛ። ዘሩ ነው እንዳለ ቀጥሎ የሚገዛ። ይሔ ዝምብሎ ነገር አደለም። ለአባቶቻችን የታዩ ትንቢት ነው እንጂ። የማንም አደለም።

## ተረክ 56 ፦ ‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ...››

‹‹አገው ልቡ ዘጠኝ ስምንቱን አኑሮ አንዱን አጫወተኝ›› የተባለ ወደ ዳሞት አካባቢ በድንበር ክርክር ላይ ለውይይት ሲቀርቡ ከተሥማማን እንቀራለን ካልተስማማን እጠራለሁ ብሎ ደብቆ ነው፡፡ ዘጠኝ ልብ ኑሮት አይደለም ሚስጥር ጠባቂነቱን እና ጀግና መሆኑን ሚያስረዳውን እነሡ ዘጠኝ ልብ አለው ብለው ሚናገሩት ነው፡፡

## ተረክ 57፦ ሰባቱ ወንድማማቾች

ሠባት ወንድማማቾች ከዋግ ሠቆጣ ጉዳያ እየሡስ ሚባል ፈልሠው ለአደን ምቹ የሆነ ነው ብለው ተከታትለው ሠባቱ እንደያዙ ነው፡፡ ዚገም አንድ ነው ከነዚህ ከሠባቱ ውስጥ ዚገም አንድ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ጎጃም ውስጥ አገው አልነበረም አልተባለም፡፡ ምስራቅ ጎጃም አካባቢ አገው ነበር፡፡

## ተረክ 58 ፦ አገው

በኢትዮጵያ የነገሠ አገው ነው፡፡ አማራ የነገሠ ከምኒሊክ በኋላ ነው፡፡ የአገው ዋናው አገር ወሎ ነው፡፡ ላሊበላ ያለበት አገር ያገው ቤተ መንግስት አደል? ሊቃውንት መፍጠሪያው ጎንደር ነው፡፡ ጎንደር ይሆናል ላሊበላ የተማረ እኔ ጎጃም አይመስለኝም፡፡ ጎጃምም ብዙ ታሪክ አለ ዲማ ደብረ ወርቅ ብዙ ታሪክ አለ፡፡

## ተረክ 59፦ ሰባቱ ወንድማማቾች

ሰባቱ ወንድማማቾች ከሰቆጣ ተነስተው አሁን አገው ምድር ተብሎ ወደ ሚጠራው ለአደን መጡ፡፡ የመጡበትም ሰፍራ ሰው የሌለበት ጠፍ መሆኑን አይተው ሰባት ወር ማርና የዱር እንስሳት እየበሉ ደህና አድርገው መረመሩና ተመልሰው ወደ ሀገራቸው ሄዱ፡፡ ሂደውም ለአባታቸው የነበሩበት ስፍራ መልካም መሆኑን ተናግረው ተመልሰው ወደ ስፍራው እንደሚሄዱ አስረዱት፡፡ ነገር ግን አባታቸው ፈቃደኛ አልነበረም በዚህ መካከል አባታችሁ ማሳመን ባለመቻሉ ሞግዚት ጨምሮ መርቆ ሸኛቸው፡፡ ሰባቱ ወንድማማቾችም ሚስቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውንና ከብቶቻውን ይዘው ተቀመጡ፡፡ ቦታውንም በሰባቱ ስም ማለትም አንኬሺ፣ ዚገሚ፣ ሚቲኪሊ፣ አዚኒ፣ በማለት ሰይመው ባለባት ሆኑበት፡፡

## ተረክ 60፡-

በድሮ ጊዜ የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ባልዬው በጠዋት ተነስቶ ወደ ሩቅ አገር ዘመዶቹን ሊጠይቅ ሲሄድ አንድ ሰው ያገኘዋል፡፡ ይህ ሰው ጋር ሰላምታ ሲለዋወጡ በባልዬው ኑግ በልቶ ነበርና ሳቅ ሲል ጥሩ ላይ የተለጠፈ ኑግ ይታይ ነበር፡፡ ይህን ያዬው መንገደኛ ባልዬውን ተሰናብቶ ወደ ሚስትዮው ቤት ይሔድ እና ‹‹ባልሽ ሲልሽ ማታ በኑግ የበላሁት ምልክት ይሁን ጠመንጃውን ላኪልኝ›› ሲላት እውቱን መስሏት የባሏን ጠመንጃ አውጥታ ሰጠች አሉ (አበራ የካቲት 12፡ 2004)፡፡ ይህን ተረክ የተረኩት አቶ አበራ አበበ ሲሆኑ ትረካውን በአገውኛ ተርከውት በረዳቴ ባይሞት አማካይነት ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው፡፡ ትረካውን ከሱቃቸው አጠገብ ተቀምጠን የሰጡኝ ሲሆን በትረካው ወቅት እሳቸውን ጨምሮ እኔ ባይሞት እና አንድ እሳቸውን የሚያውቅ ሰው ነበርን፡፡

## ትረካ 61፡-

ሰባቱ ወንድማማቾች ከሰቆጣ ተነስተው አሁን አገው ምድር ተብሎ ወደ ሚጠራው ሰፈር ለአደን መጡ፡፡ የመጡበትም ስፍራ ሰው የሌለበት ጠፍ መሆኑን አይተው ሰባት ወር ማርና የዱር እንስሳ እየበሉ ደህና አድረው ለአባታቸው የነበሩበት ስፍራ መልካም መሆኑን ተናግረው ተመልሰው ወደ ስፍራው እንደሚሄዱ አስረዱት፡፡ ነገር ግን አባታቸው ፈቃደኛ ስለነበረም በዚህ መካከል አባታችሁ ማሳመን ባለመቻሉ ሞግዚት ጨምሮ መርቆ ሸኛቸው፡፡ ሰባ ወንድማማቾችም ሚስታቸውን ልጆቻቸውንና ከብቶቻቸውን ይዘው ተቀመጡ፡፡ ቦታውንም በሰባቱ ሰይመው ባላባት ሆኑበት፡፡

## አባሪ 2

## 1. የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

### 1.1 ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ስራ | መረጃው የተወሰደበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወሬኛ ዘውዴ | ወንድ | 85 | የቤተ ክህነት አገልጋይ (ጡረተኛ) | በመኖሪያ ቤታቸው ጓሮ (ቅላጅ) |
| 2 | መልዓከህይወት ሀብተማርያም አላምረው | ወንድ | 37 | የቤተ ክህነት አገልጋይ | በመኖሪያ ቤታቸው በረንዳ (ቅላጅ) |
| 3 | ቆለጭ አድማስ አየል | ወንድ | 64 | የባህል ህክምና (ግብርና) | መኖሪያ ቤት ጓሮ (ቅላጅ) |
| 4 | አደመ ተስፋ ገንዘብ | ወንድ | 67 | እርሻ | ከመኖሪያ ቤት ውስጥ (ቅላጅ) |
| 5 | አበራ አበበ ይግዛው | ወንድ | 80 | ንግድ | የጣቃ ልብስ መሸጫ ሱቅ (ቅላጅ) |
| 6 | አያልነሽ በቀለ ጊዮን | ሴት | 37 | አስተማሪ | በአባቷ መኖሪያ ቤት ውስጥ (አይዋህ) |
| 7 | አዳሙ እንዳለው | ወንድ | 74 | ጡረተኛ | ገብርኤል ቤተክርስቲያ ቅጥር ግቢ ውስጥ (ቅላጅ) |

1.2 ሌሎች የመረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ስራ | መረጃው የተወሰደበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጊዮን አባ አቡና | ወንድ | 71 | ግብርና | መኖሪያ ቤት ውስጥ (አይዋህ) |
| 2 | ቢተውሽ አዳነ ሀጎስ | ሴት | 50 | የቤት እመቤት | መኖሪያ ቤት ውስጥ (ቅላጅ) |
| 3 | ይታይህ አለሙ | ወንድ | 86 | መነኩሴ | ቅላጅ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን |
| 4 | ወንዴ ተስፋ ገንዘብ | ወንድ | 60 | ግብርና | መኖሪያ ቤት ውስጥ (ዲሂ) |
| 5 | ማሴ መኩሪያ አስረስ | ወንድ | 60 | ሽመና | ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ቅላጅ) |
| 6 | ዘለቀ ወሰን ተሰማ | ወንድ | 72 | እርሻ | መኖሪያ ቤት ውስጥ |
| 7 | አስፈራው ተስፋ አጋኘሁ | ወንድ | 70 | እርሻ | መኖሪያ ቤት ውስጥ |
| 8 | ደመላሽ አላምረው ጓዴ | ወንድ | 60 | ጫኝ አውራጅ | ገብርኤል ቤተክርስቲያን ግቢው (ቅላጅ) |
| 9 | ፋንታሁን ይስማህ | ወንድ | 76 | ግብርና | መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ (ዲሐ) |
| 10 | ካሳዬ አስረስ | ወንድ | 74 | ግብርና | ቅላጅ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (አምቢቂ) |
| 11 | መምህር መንክር ይመር | ወንድ | 36 | የቤተክህነት አገልጋይ | ቅላጅ ገብርኤል ቤተክርስቲያን |
| 12 | ወንዳየሁ ምናሉ | ወንድ | 34 | መንግስተ ሰራተኛ | ቢሮ ውስጥ (ቅላጅ) |
| 13 | ባይሞት ምንይሉ | ወንድ | 29 | የቧንቧ ሰራተኛ | |

2.3 በቡድን ውይይቱ ላይ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር

1. ወሬኛ ዘውዴ
2. አደመ ተስፋ ገንዘብ
3. አበራ አበበ ይግዛው
4. ቆለጭ አድማስ አየል
5. ዘለቀ ወሰን ተሰማ
6. ቢተውሽ አዳነ ሀጎስ
7. ሞሴ መኩሪያ አስረስ
8. ደመላሽ አላምረው ጓዴ
9. አስፈራው ተስፋ አጋዥ
10. ወንዴ ተስፋ ገንዘብ
11. ግዮን አባ አቡና

የቡድን ውይይቱ የተካሔደበት ስፍራ ቅላጅ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ለመሰብሰቢያ እና መክሰፍት መብያነት እየተሰራ በሚገኘው አዳራሽ ጎን በሚገኝ ስፍራ ላይ ነው።

## አባሪ 3፡- የመረጃ አቀባዮች ፎቶግራፍ በከፊል



መልአከህይወት ሃብተማርያም



ቢተውሽ አዳነ



በቡድን ውይይቱ ከተሳተፉ መረጃ አቀባዮች በከፊል



አቶ ቆለጭ አየል

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜንና ፊርማዬን ያስቀመጥኩ የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሁፎችና ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ትእግስት አለማየሁ ጊዮን

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ